- እኛም ፍጹም አለመሆናችንን መረዳት ለፍጹምነት መሻታችን ትልቅ መልስ ነው።
- ትልቁ ፈረስ ላይ የምንቆናጠጠው ትንሿን እርካብ ረግጠን ነው።
- የምንችለውን ማድረግ የማንችለውን ወደ ማድረግ አቅም ይመራናል።
- ባለ ራእይ ከትንሽ ነገር ሥራውን የሚጀምር ሲሆን ለራሱ ትልቅነትም አይደክምም።
- ራእይ እኛ ብናልፍም የሚቀጥል እንጂ ከእኛ ጋር የሚያልፍ አይደለም።
- ፉሮ ያልሰደዱ ሁሉ ቢያምሩም በውበታቸው አይቆዩም።
- ራእይ እየገፋ እንጂ እየጠፋ አይመጣም።
- በራእያችን የምንሠራው የሠራን በማይመስለን ጊዜ ነው።

ምዕራፍ ሃያ ሁለት

ውስጣዊ ማዕበሎች

በዚህ ዓለም የተቀመጥንበት ዓላማ አድናቂ ሳይሆን ሠሪ ለመሆን፣ ታሪክ ተራኪ ሳይሆን ታሪክ ደጋሚ ለመሆን ነው። ድርሻቸውን ያወቁና ድርሻቸውን የተወጡ ጥቂት ከዋክብቶች በልባችን ላይ ያበራሉ። እማሆይ ትሬሣ፣ ማህተማ ጋንዲ እያልን የምናነሣሣቸው ያንን ያህል አኩሪ ተግባር በጥቂትነታቸው ከሠሩ፣ የሰው ዘር ሁሉ እንደ እነርሱ ድርሻውን አውቆ ቢፈጽም ከሚፈለገው በላይ መልካም ነገር በበዛልን ነበር። ከደህና መወለድን፣ ከጥበብ ጋር መወለድን የማይናፍቅ ራእይ ብቻ ነው። ደህና መሆንም፣ አዋቂ መሆንም ያልጠለቀ ፀሐይ፣ ዛሬም የታደልነው ጀምበር ነው። ስለ ራእይ የምናጠናበት ይህ መጽሐፍ ስለ ስልቶች፣ ስለ ድርጅታዊ ግዴታዎች የሚናገር ሳይሆን ስለ ተፈጠርንበት ዓላማ የሚናገር ለተፈጠርንበት ዓላማ እንድንኖር የሚያነቃቃን ነው። ከብዙ ባለ ራእዮች በረከት ተካፍለናል። ራእይን መድገም ደግሞ ያስፈልገናል። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የችግረኛ ልጆች በሚያድጉበት ተቋም ተገኝተው እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፦ «ሞግዚት ካሳደጋችሁ በኋላ እናንተም ሞግዚት መሆን አለባችሁ።»

መርከብ አቅጣጫውን በትክክልና በቀጥታ ከያዘ ደግሞም ሞተሩ ካልተበላሸ ከወደቡ ይደርሳል። ትክክለኛውን ራእይ እስከያዝን፣ ሞተሩ ፈሪሃ እግዚአብሔር እስካለ ድረስ ወደ ሕይወት ግብ መድረስ አይቀርም። ነገን የምናየው በራእይ ነው። ዛሬ ዘር፣ ነገ መኸር ነው። ነገን የምናየው በወጣቶች ነው። የነገ አባቶች እነርሱ ናቸውና። ነገን የምናየው በደቀ መዛሙርቶች ነው። የነገ መምህራን እነርሱ ናቸውና። ስለዚህ ዛሬን በትክክል መጠቀም፣ ወጣቶችንና ደቀ መዛሙርቶችን መኮትኮት ይገባናል። ዛሬ ልንሠራ የሚገባንን ነገ ማዘግየት በሕይወት ላይ ትልቅ ጥፋትን እንደሚያስከትል ማወቅ አለብን። እባካችሁ ወገኖቼ ምክርን አሁኑኑ በርካሽ ዋጋ ካልገዛችሁ ወደ ፊት በውድ ዋጋ ትገዛላችሁና አስተውሉ!

ስለ ራእይ ብዙ ተብሏል። ራእይ የለሽ ሰዎችም አስፈሪ መሆናቸው በብዙ ተገልጧል፦

❖ የአንድ ሰው የታመቀ ኃይል ያለው ራእዩ ውስጥ ነው። ራእይ የሌለው ግን ምንም የለውም።

- ❖ በሕይወት ትልቁ አስፈሪ ነገር ሞት ሳይሆን ያለ ራእይ መኖር ነው።
- ❖ የተበላሸ ራእይና የተበላሸ ሕይወት አንድ ናቸው።
- ❖ ዓይን ሊያይ ከሚችለው ባለፈ ሊመለከት የሚችለው ራእይ ነው።
- ❖ ዕይታ የዓይን ውጤት ሲሆን ራእይ ደግሞ የልብ ነው።
- ❖ ትውልዳዊ አስተሳሰብ በራእይ ውስጥ ይገለጻል።
- ❖ ራእይ ወደ ሙሉነት የምንመጣበት መንገድ ነው።
- ❖ እውነተኛ ራእይ ከማንኛውም እንቅፋት በላይ ነው።
- ❖ ስኬታማ መሆን ትፈልጋለህን? ራእይ ይኑርህ።
- ❖ ራእይ ካለህ ሁሉንም ከመሞከር ትቆጠባለህ።
- ❖ ትክክለኛ ራእይ ምንጊዜም ዋጋ ያስከፍላል።
- ❖ ራእይ አልባ እይታና ተስፋ ቢስ ሕይወት አንድ ናቸው።

ጉልበታችን፣ ሀብታችን፣ ቁመናችን የውስጣችን ባሪያዎች ናቸው። ውስጣችን ከውሳኔ ያለፈውን ራእይ ሲይዝ ኃይልን በትክክለኛው ቦታ ማዋል እንችላለን። ራእይ ጉልበትን ሲያዘው ነገሮች ሁሉ ውብ ፍጻሜ ያገኛሉ። ሰዎችን አጉል ነዋሪ የሚያደርግ ራእይ አልባነት ነው። ያለ ራእይ ከሚኖሩ ይልቅ በራእይ የሚሞቱ ሲታወሱ ይኖራሉ። ከሞት ይልቅ ልንፈራው የሚገባው ራእይ አልባነትን ነው። ራእይ ጉዞ ጀምሮ ሊበላሽ ይችላል። ያልተጨረሰ ራእይ ሕይወት ላይም ተጽእኖ ያመጣል። ራእያችንን ያስጣሉን ነገሮች የራእዩን ደስታ መተካት ስለማይችሉ ሀዘንተኛ ያደርጉናል።

ጮላ ጮላ ያሉ ዓይኖች፣ ርቀትን ማየት የሚችሉ ብሌኖች የሕይወትን ዋነኛ ነገር ማየት አይችሉም። የሕይወት አስኳል ያለው ከግዙፍ ይልቅ በረቂቅ ውስጥ ነው። ያንን የሚያየው ራእይ ነው። ራእይ የሌለው ለሚኖራት ሕይወት እንግዳ ሆኖ ዘመኑን የሚፈጽም ነው። በልብ ማየት ራእይ ይባላል። ለትውልድ ያለን መልካም አስተሳሰብ የሚገለጠው በራእያችን ነው። ለነገም የሚተርፈው፣ ሀብት ሳይሆን ራእይ ብቻ ነው። በሙሉነት ራእይን የጀመረ የለም። ራእይ ግን ወደ ሙሉነት የሚያደርስ፣ ለመንፈሳዊ አካለ መጠንም የሚያበቃ ነው። ራእይን የሚያስቆመው ራእይ አልባነት ብቻ ነው። ራእይ ከእንቅፋት በላይ ነው። ደስታ ያለው ስኬት የሚገኘው በራእይ ውስጥ ነው። የማያረካ ስኬት ግን ያለ ራእይም ሊገኝ ይችላል። እያየ

የማያዩ፣ እየሰሙ የማያስተውሉ ሰዎች ቢኖሩ ራእይ የሌላቸው ሰዎች ናቸው። ለመኖር ያለን ጉጉት በራእያችን ውስጥ ተቀምጧል። ሙከራዎች፡- ጉልበትንና ጊዜን የሚጨርሱ፣ ልብን የማያሳርፉ፣ መንገድን ለመጀመር ይለፍ የማይሰጡ ናቸው። ከብዙ ሙከራዎች የምንድነው ግን በራእይ ነው። ራእይ እንዳይኖረን ብንጥርም ሙከራ እንዳይኖረን መጣር ግን አይሆንልንም። ሕይወታችን በአሰሳ ብዙ ዙረት ታደርጋለች። ራእይ ካልተገኘ መንገዱ አይጀመርም። የራእይ እውነተኛነት አንዱ መለኪያው ብዙ ተቃዋሚ ሲያስነሣ ነው። ባለ ራእይነት በራእይ የለሾች ትገፋለች።

ራእይ በተፈጥሮ ላይ ተሰላለች። የባሕር ዓሦችን በማየት መርከብ የመሥራት ቅንዓት፣ የሰማይ አእዋፋትን በማየት አውሮፕላን የመሥራት ምኞት በሰው ልብ ተቀርጿል። ተፈጥሮ በራሱ የራእይ አማማቂ ናት። ያለ ራእይ የተገኙ መልካም ሥልጣኔዎች፣ ጠቃሚነታቸውን የቀጠሉ ግኝቶች የሉም። ጥይትን የሚሠራው እውቀት ሊሆን ይችላል። ራእይ ግን አይደለም። አቶሚክ ቦንብን የሚቀምመው ሳይንቲስትነት ሊሆን ይችላል። ራእይ ግን አይደለም። አውሮፕላንን የሠራ ግን ራእይ መሆኑ ጥርጥር የለውም።

የራእይ ዓላማው የግላችንን ምኞት ማሰብ፣ አሊያም የእኛ የሆኑትን ቤተሰቦቻችንን ነጻ ማውጣት አይደለም። ራእይ ድንበር የለሽ ዕቅድ ነው። ራስን በመካድ ብቻም የሚገኝ ነው። ከእኔ ጉዳት የሌሎች ጉዳት ይበልጣል በሚል ፍቅር የሚወለድ ነው።

በሕይወት ውስጥ ወደ መሆን የሚያመሩ ሦስት ምኞቶች አሉ።

1. እግዚአብሔር ያሰበልን
2. እኛ ለራሳችን ያለብነው
3. ሰዎች ያሰቡልን

ራእይ እግዚአብሔር ለእኛ ያሰበልን ነው። መተግበሪያውም ከአእምሮአችን አንሥቶ ያሉት የአካል ክፍሎቻችን ናቸው። እግዚአብሔር ያሰበልን ሲሆን እኛ ለእኛ ያለብነው፣ ሰዎች ያሰቡልንም በእግዚአብሔር አሳብ ውስጥ ተጠቃሎ እናገኘዋለን። ራእይ ላለው እቅዱ ባዶ ደመና አይሆንበትም። ከእግዚአብሔር ራእይ ጋር ተደባልቆ ይፈጸማል። ታሪክና እሴት የራእይ ኃይል አይሆንም። የራእይ ኃይል ከራእይ የሚወጣ መለኮታዊ ጸጋ ነው።

በራእይ ውስጥ ተስፋ የምንቆርጥበት ጊዜ ብዙ ነው። ራእይ ግን ከተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሌላ ተስፋ እንዲወለድ ያግዛል። ራእይ የመጀመሪያውን ቀን ፍቅር፣ ወደ ሩጫው የገባንበትን ቅንዓት በማሳሰብ ኃይልን ያድሳል። ወደ መጨረሻ የደረሱ ሥራዎች፣ የተንገዳገዱ ራእዮች የቀጠሉት የመጀመሪያውን ቀን በሚያሳስብ የራእይ መንፈስ ነው። ራእይ በመጀመሪያ የሚተምነው ኪሣራን በመሆኑ በጉድለቶች በመከራና በፈተና አይደነቅም። ራሱን የሰጠ ባለ ራእይም በችበረቱ መወረስ፣ በስሙ መጥፋት አይደናገጥም። ገና ብዙ ዋጋ እንደሚከፍል አያሰበ ይበረታል።

የውስጥ ማዕበሎች

በአንድ መርከብ ውስጥ ሊነሣ የሚችለው ማዕበል ሰላም ማጣት፣ በሽታ፣ ናፍቆት... ሊሆን ይችላል። ከመርከቡ ውጭ ደግሞ ሊነሣ የሚችለው ማዕበል አደገኛ ነፋስ፣ የባሕር ላይ ዘራፊዎች ...ሊሆኑ ይችላሉ። በራእይም ውስጥና ውጭ የተለያዩ ማዕበሎች አሉ። ሁሉንም መግለጽ ባንችል እንኳ የተወሰኑትን ማየት ግድ ይለናል።

1. በአንድ ጊዜ ፍጹምነትን መፈለግ

ቀስ በቀስ ማደግ የተፈጥሮ ሕግና ውበት ነው። ጌታችን ሰው በሆነ ጊዜ እንደ አምላክነቱ ዕለቱን ማደግና ዋጋ መክፈል ይቻለው ነበር። ነገር ግን የዕድገትን ሕግ ጠብቆ ቀስ በቀስ አደገ። ሁሉም ነገር በጊዜው እንዲሆን ተጠነቀቀ። ራእይም ቀስ በቀስ ያድጋል እንጂ በጅምሩ ፍጹም አይሆንም። ለእያንዳንዱ ቀን እንግዳ በሆንበት ዓለም ላይ የማናውቀው ነገር ብዙ ነው። የማናውቀው ፈተናም ስላለ የዛሬ ፍጹምነት ለነገ አይረዳም። ራእይ ገና በጅምሩ ፍጹም እንዲሆን መፈለግ ራእይን ሕልም አድርጎ የሚያስቀር ነው። ራእይን ከመግለጻችን በፊት እንዲገለጽልን መጸለይ ተገቢ ነው።

2. መጀመር ብቻ መውደድ

በመልካም ነገሮች በቶሎ የሚነኩ፣ በቶሎም ለመተግበር የሚቸኩሉ፣ ብዙዎችን ከኋላ ለማስከተል አቅም ያላቸው ነገር ግን ለመፈጸም ጉልበት የሌላቸው ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች በሰኔ ዘርተው በታህሣሥ ለማጨድ የሚታክቱ ገበሬዎችን ይመስላሉ። የሰሙትን መልካም ነገር ታግሦ መቀመጥ አይሆንላቸውም፣ ልብን ሁሉ ካነሣሡ በኋላ የሚሰወሩ መሪዎች ናቸው። ሁልጊዜ የሚገኙት

በምሥረታዎች ላይ ነው። ምርቃት ላይ የማይገኙ ጀማሪ ብቻ ናቸው። በራእይ ውስጥም ይህ ችግር ይታያል። አሁን የተሰማቸውንና የሰሙትን ራእዬ ነው ብለው የሚያስተጋቡ፣ ለፈጣን ውሳኔ የማይፈሩ፣ ሰዎችን ሰብስበው ይመራሉ ተብለው ሲጠበቁ ከአድራሻቸው የሚታጡ፣ ያንን ነገር ደግሞ የጠየቃቸውን ሰው የሚጠሉ፣ በስሜት ያበዱ ናቸው። እንዲህ ያለ ባሕርይ ለራእይ ትልቅ እንቅፋት ነው። መጀመር ብዙ ተግዳሮት የለውም፣ መፈጸም ግን ያታግላል። እነዚህ ሰዎች ወደ ኋላ የሚሉት ትግል ፈርተው ሳይሆን የራሳቸው ስልቹነት ከመንገድ እያስቀራቸው ነው። ትላንት የጀመርኩትን አልጨረስኩም መጀመሪያ እርሱን ልጨርስ ከማለት አሁንም የተጀመረ ካገኙ ማዳነቅ፣ በሰማበት ጣዱኝ ማለት ይወዳሉ። ዕቅዳቸው ብዙ ውጤታቸው ትንሽ ነው። አንዱን ሳያጣጥሙ ሌላውን ለመቅመስ የሚቅበጠበጡ የቅምሻ ሊቃውንቶች ናቸው። ይህ ባሕርይ ውሸታም ያደርጋቸዋል። ውሸትም ለሌብነት አሳልፎ ይሰጣቸዋል። የሚያያቸውን ሰው ልብ የማያሳርፉ፣ ዳቦን ሲሉት የሚኖሩ አመለኞች፣ ዳቦን ግን የማይጠግቡ የዘመናት ረሀብተኞች ናቸው። በራእይ ላይ የሚያሳዩት ይህ ቅብጥብጥነት በትዳራቸውና በማኅበራዊ ኑሮአቸው ላይም ተጽእኖ ያመጣባቸዋል። ለራእይ ብለን የምንለማመደው ባሕርይ ራእይን አይጠቅምም። ለራእይ የሚያስፈልገው መሠረታዊ ለውጥ እንጂ የቀለም ቅብ አይደለም።

3- ለመጀመር መፍራት

የጅማሬ ጎበዞች እንዳሉ ሁሉ የጅማሬ ፈሪዎችም አሉ። መጀመር ሞት የሚሆንባቸው፣ ከመቀመጫ መነሣት የሚያብረከርካቸው፣ የተጀመረ ካገኙ ለመንጎድ የሚጠባበቁ፣ በሩጫው መጀመሪያ ላይሆን መሐል ላይ መቀላቀል የሚፈልጉ፣ የጥገኝነትን ሙቀት ያልጠገቡ ሰዎች አሉ። ይህ ባሕርይ ለራእይ ትልቅ እንቅፋት፣ ውስጣዊ ማዕበልም ነው። እነዚህ ሰዎች በጥገኝነት መንፈስ ያደጉና የጥገኝነት ዕድገታቸውን ኑሮ አድርገው ለውጠው የሚጓዙ ናቸው። ሁል ጊዜ የሚፈልጉት ሰው፣ ይህን ደካማነት የሚሸፍንላቸውን እንጂ ከዚህ ደካማነት ለመውጣት ኃይል የላቸውም። ግንኙነቶች ግድ ሲሆኑባቸው በመጠጥና በሱስ ኃይል በመደፋፈር ይወጣሉ። የሚጠጉት ሰው ካላገኙ ሱሶችን ይጠጋሉ። ጠዋት ዓይናፋር፣ ማታ ማታ ንጉሥ የሚሆኑ ባለ ሁለት ገጽታ ሰሌዳ ናቸው። ስለ እነርሱ ሌሎች እንዲናገሩላቸው ሌሎች እንዲጀምሩላቸው ይፈልጋሉ። በእነዚህ ሰዎች ውስጥ ያለው የተፈጥሮ ጸጋ ትልቅ ነው። ሰይጣን ግን እንደ ተጋረዱ እንዲያልፉ በፍርሃት ይዋጋቸዋል። በነገሩ እውነትነት ያምኑበታል፣ ከዚህ ውጭም መፍትሔ እንደ ሌለ ተረድተዋል። ራእያቸውን ለማሳካት

ግን ከተቀመጡበት መቀመጫ አይነሡም። መጀመርን በመፍራት ተቀምጠዋል። «አሉ የሚባሉ መሣሪያዎችን አቀረብን... ልብ ማቅረብ ግን አንችልም» አሉ እንደ ተባለው ለእነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር ልብም ማቅረብ እንደሚችል እንነግራቸዋለን። በመጸለይ ትንሽ ትንሽ ልምምድ ማድረግ ይገባቸዋል። እነዚህ ሰዎች ከጀመሩ ለመጨረስ በቂ ጉልበትና የተፈጥሮ ጸጋ፣ የተዋበ ሥራ አላቸው። መኪና የሚሄደው በአንደኛ ማርሽ እንጂ በዜሮ አይደለም። ስለዚህ ጅምር ያስፈልጋል። የእስራኤል ልጆች ባሕር የተከፈለላቸው በግብፅ ሳሉ ሳይሆን ከግብፅ ለመውጣት ርምጃ ሲያደርጉ ነው። ርምጃ ባሕር ይከፍላል። መነሣት የራእይ ሕግ ነው።

4- ይሉኝታ

ምን ይሉኝ እያሉ መኖር ሌሎች ላመኑበት ነገር መኖር በመሆኑ ጉልበት ይጨርሳል። ሰዎች የሚወዱትን ብናደርግላቸውም ከማለት ግን ወደ ኋላ አይሉም። የሚኖሩት ለማለት ነውና። ስለዚህ የሚሉትን ለማሳጣት ያደረግነው እንቅስቃሴ ባለ ድል አያደርገንም። ማድረግ ያለበትን የማያውቅ ሰው የመንገድ ካርታውን የሚያስተካክለው በሰዎች ስሜት ነው። ነገር ግን ለእግዚአብሔርና ለነሢና ደስ የሚያሰኘውን ስናደርግ ያን ጊዜ ሰዎች የሚሉትን ማስቆም እንችላለን። ቋሚ የሆነው ውሳኔአችን የሰዎችን አሉታ ይዘጋል። እኛም የምናዳምጠው እግዚአብሔርና ጎሊና ስለሰን የሰዎችን ስሜት ያውም የማይሰማ ጉርምርምታ ከማዳመጥ እንድናለን። በተግባራችንም ደስተኞች እንሆናለን።

ልጅ ሳለን ንፍጣችንን ሲጠርጉልን፦ «ንፍጥ ቆሻሻ ነው፣ ንፍጥ ያስቀይማል» እያሉ ሳይሆን «የእገሌ ልጅ ንፍጣም ነው ይሉሃል» እያሉ ነው። ስለዚህ የምንበላውና የምንጠጣው ለራሳችን፣ የምንኖረው ለሰው ሆነ። ይሉኝታ ያደግንበት ራሳችንን ያነጽንበት ባሕላችን ነው። ይሉኝታ ሁልጊዜ እውነት አይደለም። መልካም የምናደርገው ሰዎች ስለሚያዩንና ስለሚሰሙን ከሆነ መልካም ተግባራችን ዋጋውን ያጣል።

ይሉኝታ ለራእይ እንቅፋት ነው። ሰዎች ራእያቸውን ከግብ ለማድረስ በይሉኝታ ይታሠራሉ። የቀድሞ ታሪካቸውን በማሰብ ይህን ራእይ ይዤ ብወጣ በቀድሞ ማንነቴ የሚያውቁኝ ምን ይላሉ? በማለት ይጨነቃሉ። የቀድሞ አለቆቻቸውንም በማሰብ እነርሱ ያልሠሩትን እኔ ስሠራ ምን ይላሉ? የሚል ይሉኝታ ያስራቸዋል። በዓለም ላይ ብዙ እስር ቤቶች አሉ። አንዱ ይሉኝታ ነው። የኋላውን ካልረሳን ወዴትም መራመድ አንችልም። ዛሬ ሌላ ሰው መሆናችንን

መቀበል ያስፈልጋል። የትላንት መልካምነትም ሆነ የትላንት ክፉነት ለዛሬ አይጠቅምም። ዛሬ የተሻለውን ማድረግ ይገባናል። እግዚአብሔር ታሪክን እንደሚለውጥ ከቃላችን ይልቅ ሕይወታችን ምስክር ሲሆን የማይገኝ መረጃ ነው።

5- ብልሹ ሥነ ምግባር

በተለያዩ አገራት በሚደረገው የገንዘብነት ምርጫ ሥነ-ምግባር ትልቁና ዋነኛው መለኪያ ነው። ቤተሰቡን በትክክል መምራት መቻሉና ትዳሩን ማክበሩ ጭምር ይታያል። ምክንያቱም ከመሪነቱ የመጀመሪያ ተጽእኖ «አርአያነቱ» ነውና። ባለ ራእይም መሪ ነው። ቀድሞ ያየ መሪ ይሆናልና በግድ መሪ ነው። ባለ ራእይ ከሚገነባው ቁሳቁስ፣ የሚገለጽበት ሥነ ምግባሩ ይታያል። ሥራው ከተቃወመው ደጋፊ ቢበዛለት እንኳ አያልፍም። ሰው ሁሉ ተቃውሞት ሥራው ከመሰከረለት ግን የማታ ድል አለው። ጠቃሚ ነገሮች ሁሉ ጠቃሚ የሚሆኑት በሥነ ምግባር ነው። ሀብት ጠቃሚ ነው፣ ሀብት ጠቃሚ የሚሆነው ሥነ ምግባር ሲኖር ነው። አሊያ የሞት ማፍጠኛ ነው። እውቀት ጠቃሚ ነው፣ እውቀት ጠቃሚ የሚሆነው በሥነ ምግባር ነው። አሊያ የእብደት በር ነው። በዓለም ካልተማረ ደንቆሮ የተማረ ደንቆሮ የተጠላ መሆኑ ብዙ ጊዜ ይነገራል። ሰዎች ቢማሩም ባይማሩም ሥነ ምግባራችንን ያያሉ። ሥነ ምግባርን ለመገምገም መማር አያስፈልግም። ሥነ ምግባር ሕይወት ነውና።

የራእይ ትልቅ እንቅፋት ብልሹ ሥነ ምግባር ነው። ባለ ራእይ አይሳሳትም አንልም። ነገር ግን ንስሐ ይገባል። የበደለውን የሌሎችን ጎሊና፣ በእርሱ ላይ የነበራቸውን ምኞት የጎዳባቸውን ወገኖች ይቅርታ ይጠይቃል። በጨለማ ውስጥ መብራት የበራባቸው የፎቅ ቢሮዎች በሩቅ ይታያሉ። ከሠራተኛ ኋላ ቀርቶ የሚሠራ አንድ ትጉህ ሰው እንዳለ ይታወቃል። ራእይ በሌለው በጨለማው ዓለም ባለ ራእዮች በሩቅ ይታያሉ።

6- ስልቹነት

ጀምሮ ያለ መጨረስ በሽታ ብዙዎችን ይጎዳል። ባለ ራእይነት ግን ይህንን ድንዛዜ ይሰብራል። መጨረሻ ላይ ቆሞ መጀመር የባለ ራእይ ባሕርይ ነውና። ስልቹነት አለመጀመር አይደለም። በግድ መጀመር በፍጹም ለመጨረስ አለመፈለግ ነው። ስልቹዎች የትጉሆችን ፍሬያማ ወይን ያደንቃሉ፣ ይበላሉ። የእኔ ወይን መቼ ይቀመሳል? የሚል እልህ ግን የላቸውም። ገና ሲያስቡት

የሚደክማቸው፣ የሚያፈሰውን ጣራ ከመድፈን ወደማያፈሰው መኝታቸውን የሚያስተካክሉ፣ በሚሮጡ ሰዎች የሚገረሙ፣ አገራቸው ገብተው መና የሚጠብቁ ናቸው። የእስራኤል ልጆች መና የወረደላቸው ማረስ፣ መቆፈር በማይችሉበት ምድረ በዳ ነው። አገራቸው ገብተው የምድሪቱን ፍሬ በበሉ ዕለት ግን መናው ቆሟል። ታካቾች ሳይሠሩ ይዝላሉ፣ መንገድ ጀምረው አይፈጽሙም። በሌላው ማጅያት የእነርሱ ፊት እንዲጠራ፣ በሌላው መሥዋዕትነት የእነርሱ ነጻነት እንዲበራ ይፈልጋሉ። ዕድሎች ወደ እነርሱ ቢመጡም አይጠቀሙባቸውም። ባለ ራእዮች ግን ዕድልን ይፈጥራሉ እንጂ አይጠብቁም። በራእይ ውስጥ ስልቹነት ትልቅ እንቅፋት ነው። ተግባራችንን የምንፈጽመው በሙያ ብቻ ሳይሆን በትዕግሥትም ነው። ራእይ በነጻ የምንቀበለው በዋጋ የምንፈጽመው ነው።

7- <u>መንፈሰ ቀዝቃዛነት</u>

የስሜታዊነት ሌላኛው ጽንፍ መንፈሰ ቀዝቃዛነት ነው። ሁሉን ነገር እኔ ላድርገው የሚል ተጨናቂነት እንዳለ ሁሉ ሁሉም ነገር ቢሆን ይሁን የሚል መንፈሰ ቀዝቃዛነትም አለ። መንፈሰ ቀዝቃዛነት የማድረግን ሳይሆን የማሰብን ዋጋ እንኳ መክፈል የማይፈልግ ነው። ብዙ መንፈሰ ቀዝቃዛ እናቶች አሉ። ልጆቻቸውን መንካት እንኳ የማይፈልጉ፣ ልጃችሁ ሲባሉ የሚደነግጡ፣ በበሉበት የሚተኙ፣ ልጁ ብለው ወደ ኋላ የማያዩ እናቶች አሉ። መንፈሰ ቀዝቃዛነት ጥንቃቄና ፍቅር የሚፈልገውን ልጅ እንኳ እንዲረሱ ያደርጋል። እነዚህ ሰዎች ሌላው ያድርግልን የሚል ብልጠት የላቸውም። ከሆነ ይሆናል ብለው የሚተኙ ናቸው። እነዚህ ሰዎች መኖራቸውን ስናይ ፍጥረቱን የሚያኖር ቸር ጌታ እንዳለ እናስታውሳለን። እነዚህ ሰዎች በአንደበታቸው የሚያስቀይሙ፣ በሰው ኑሮ ውስጥም ውሳኔ እንስጥ የሚሉ ስላልሆኑ ተወዳጅ ናቸው። ለአድማና ለተንኮል ስሜታቸው ቶሎ የማይግል ስለሆነ ለጠብ ደቦ አይመቹም። ስለዚህ ተንኰለኞች ይርቋቸዋል።

መንፈሰ ቀዝቃዛነት ራእይና ጸጋን ያጠፋል። የራእይ እሳት ለመቀጣጠል እንቅስቃሴና ጎብረት ይፈልጋል። መንፈሰ ቀዝቃዞች ግን ካሉበት የማይነቃነቁ ስለሆኑ ራእይን ያከስሙታል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- «መንፈስን አታጥፉ» ብሏል (1ተሰ. 5÷19)። መንፈሰ ያለው ጸጋን ነው። ጸጋን በእሳት መስሎታል። እሳት አፈር ሲበትኑበት፣ ውኃ ሲያፈሱበት ይጠፋል። ጸጋም ምውትነት በሆነው መንፈሰ ቀዝቃዛነት ደግሞም በአጉል ፍርሃት ይጠፋል። እግዚአብሔር በዓመፃ ምክንያት ጸጋን ይወስዳል። ጸጋን ባለ

መንከባከብ ደግሞ ራሱ ይሄዳል። ራእይም ጸጋ ነውና በመታፈን ይከስማል። መንፈሰ ቀዝቃዛነት የራእይን ግለት የሚያጠፋ የሞት መንፈስ ነው።

8- <u>መዘግየት</u>

እግዚአብሔር እንደ የዘመኑ ባለ ራእዮች ያስነሣል። ባለ ራእዮችና ራእዩ ጠቃሚ የሚሆኑት በጊዜው ነው። ከጊዜው በፊት የተነሡ ብዙ ጠላት ያተርፋሉ፣ ከጊዜው በኋላ የተነሡ አንዳች ተከታይ አያገኙም። በሚጓዘው መርከብ ውስጥ መስተንግዶ እንደሚያደርጉ ሠራተኞች እኛም በሚጓዝ ሕይወትና ዓለም ላይ የምንሠራ ባለ ራእዮች ነን። የመርከቡ ሠራተኞች የሚያስፈልጉት ባሕሩ መሐል ላይ እንጂ ወደቡ ላይ አይደለም። መርከቡ ወደቡ ላይ ሲደርስ ተሳፋሪው መሬት ለመርገጥ እንጂ ለመስተናገድ አይጓጓም። የምናስፈልገው እስካለንና ትውልድ እስካለ ብቻ ነው። በዘመናችን ዱዳ ሆነን ያለ ዘመናችን ተናጋሪ ብንሆን የምንባለው ወፈፌ፣ እብድ ነው። በዘመናችን ተቀምጠን ያለ ዘመናችን ለሥራ ብንነሣ የምናስተባብረው ጥቂት ነው።

ከራእይ እንቅፋቶች አንዱ መዘግየት ነው። መዘግየትን የሚወልደው ይደርሳል የሚል ተስፋ ነው። ጊዜ ተሰጥቶን ጊዜ መጠበቅ መዘግየትን ያመጣል። በወጣትነት ደስታ፣ በጊዜያዊ ምኞት መደለል መዘግየትን ይወልዳል። ራእይ ወቅታዊ መልእክት ነው። ዐፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ የማድረግ ራእይ ነበራቸው። ይህ ራእያቸው በዚያን ወቅት ዋነኛ ጉዳይ ነበር። ማርቲን ሉተር ኪንግ የጥቁሮች እኩልነትን ማየት ራእዩ ነበር። ይህ ራእይ ግን ለዛሬ የሚጠቅም አይደለም። ምክንያቱም የጥቁሮች መብት ተከብሯልና። ራእይ ጠቃሚ የሚሆነው ሠራተኛው፣ ሥራውና ተጠቃሚው ትውልድ ሲገናኙ ብቻ ነው። ስለዚህ መዘግየት አይገባንም።

ትውልድ እንደ ሐውልት ቆሞ የሚኖር አይደለም። ትውልድ ለማለፍ የሚቻኰል ነው። የእኛም ዕድሜ የተሰፈረ እንጂ በጉልበታችን የምንጨምረው አይደለም። ስንዘገይ ትውልድ ያመልጠናል፣ መሥራት የምንችልበት ጊዜም ያጥረናል። ለራእይ መዘግየት እንቅፋቱ ነው። መዘግየት መቅረትን ይወልዳልና መፍጠን ይገባናል።

9- ቍጭ ብሎ መቆጨት

በኑሮ ውስጥ አራት ዓይነት ሰዎች አሉ፡-

1- በሆነው ነገር እየተገረሙ የሚኖሩ ስሜታውያን፣
2- ገንዘብን አከማችተው በአጥር ተከልለው ለመኖር የሚሹ ቁሳውያን፣
3- እውቀትን አካብተው ለመኮፈስ የሚሰናዱ ድኩማን፣
4- ራእይን ይዘው ሰጪለማው ዓለም የሚያበሩ ልበ ብርሃን ናቸው።

«ቍጭ ብሎ መቆጨት» የሚወዱ በመጀመሪያው ምድብ ላይ የሚገኙ ስሜታውያን ናቸው። ስሜታውያን ተግባር የሌላቸው የጀበና ቁማታ ናቸው። ሁሉንም ነገር በማዘንና በወቅታዊ መቀጣጠል የሚፈጽሙት የሚመስላቸው፣ በሕይወት ውስጥ እየኖሩ ሕይወት ያልገባቸው ናቸው። «ምነው አቅም በኖረኝ» እያሉ ባላቸው ከመሥራት በሚኖራቸው አየር እየዘገኑ የሚቸሩ፣ ምነው ወንድ በተገኘ እያሉ መሥዋዕት የሚሆን ሰው የሚናፍቁ፣ እየሸለለ እንደማይዋጋ አዝማሪ የአዘ ዕንባ የሚያነቡ ናቸው። ራእይ ገና በጠዋቱ፣ ነፍሳችንን ሳንረዳት በሕፃንነት ዘመን የተቀበልነው ነው። ባለ ራእይ ለመሆን ትምህርት አስክንጨርስ መጠበቅ አያስፈልግም። ትምህርት ቤቶች ራእይ የመስጠት አቅም የላቸውም። እንደውም የፈሪና ቍጭ ብለው በምኞት የሚደክሙ ወይም ትችት የተሞሉ ሰዎች ማውጫ ናቸው። «መማር ሁሉ ማወቅ አይደለምና» መማር መደንቆር የሚሆንበትም ጊዜ ብዙ ነው። ራእይ ዘዴ ወይም የኑሮ ማቅለያም አይደለም። እግዚአብሔር ሰዎችን በሚያይበት ዓይን ማየት መቻል ነው። በምናየው ከመፍረድ በልብ የማየት ችሎታ ነው። ለራእይ ብዙ ሰው አያስፈልግም። ከግማሽ ሚሊየን በላይ የነበረውን ሕዝበ እስራኤልን ከግብፅ ያወጣ አንድ ሙሴ ነው። ከነዓንን ያወረሰ አንድ ኢያሱ ነው። ራእይ ብዙ አቅም አይፈልግም። በትርና ቃሉ በቂ ነው። ሙሴ በትርህን ያዝ ተባለ፣ ኢያሱ ቃል ተሰጠው (ኢያ. 1÷1-9)።

ቍጭ ብሎ መቆጨት የራእይ እንቅፋት ነው። ሌላውን እያነሣሡ መቅረት አላዋቂነት ነው። በሌላው መሥዋዕትነት ለመኖር ማቀድ ከንቱነት ነው።

10. ዕቅድ ማብዛት

እግዚአብሔር የፈጠረን ታዋቂ ሰው እንድንሆን ሳይሆን ጠቃሚ ሰው እንድንሆን ነው። እግዚአብሔር የፈጠረን ሁሉንም የዓለም ችግሮች እንድንፈታ አይደለም። የተሰጠንን ድርሻ እንድንፈጽም ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ ያሳየንን አርአያነት ማጤን ይገባናል። ኢየሱስ ክርክቶስ እየቻለ ያልሠራቸውን ነገሮች ስናስብ ሊሠራው የሚገባውን አነጣጥሮ ስላወቀ ነው። መድረሻውን ያየ በጎዳናው ይሄዳል እንጂ በመንገዶች ሁሉ አይሄድም። መፈጠርን ዋጋ ያለው የሚያደርገው ለምን እንደ ተፈጠርን ማወቅ ነው። የእውቀቱን ያህል ምክንያቱን ማወቅ የሰው ጥማት ነው። ለምን እንደ ተፈጠርን መረዳት አስደላች ነው።

አንድ አባባል አለ፡- ዕቅድህ 80% ከሆነ ውጤትህ 20% ነው፣ ዕቅድህ 20% ከሆነ ውጤትህ 80% ነው ይባላል። ዕቅድ ሲበዛ ውጤት ያንሣል፣ ዕቅድ ሲያንስ ውጤት ይበዛል ማለት ነው። ብዙዎች ብዙ ዕቅድ አላቸው። ሁሉንም ለመንካት ይሻሉ። የተዝረከረኩት ዕቅዶቻቸው የተዝረከረከ ሀብት ያፈራሉ። በመንገዶች ሁሉ ይሄዳሉ እንጂ ወደ ግቡ የሚደርሱበት መንገዱ አይታያቸውም። ሰው ውጤታማ የሚሆነው ብዙ በመጀመር አይደለም። አንዱን በብቃት በመወጣት ነው። ባለጠጋ ለመሆን ትልልቅ ሥራ መጀመር አያስፈልግም። መርፌ የሚያስመጡ ሚሊየነሮች፣ የቁልፎ አዝራር የሚሸጡ ባለጠጎች አሉ። ሁሉን መጀመር፣ ዕቅድ ማብዛት የራእይ እንቅፋት ነው።

11. ስሜታዊነት

አንድ ወጣት የሴት ጓደኛ እንደ ያዘ ነገረኝ። ያ ልጅ በሥጋዊ እውቀቱ የገፋ፣ የተማረ ነው። የእንጀራ እውቀት እንጂ የሕይወት እውቀቱ ግን ገና ነበር። ደመወዙም ዓለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ እንደ መሥራቱ ለእኛ አገር በጣም ሰፊ ነው። ይህ ወጣት ጓደኛውን በጣም እንደሚያፈቅራት መልካምነቷ ደግሞ ከቃል በላይ መሆኑን ነገረኝ፡- «ምን ያህል ጊዜ ሆናችሁ?» ስለው፡- «ሦስት ወር» አለኝ። በሦስት ወራት ይህን ያህል ሰፊና የተጠናቀቀ ምስክርነት መስጠቱ አሳሰበኝ። በመቀጠል የሚወልዱት ልጅ የሚለብሰውን ሹራብ መስፋት እንድትጀምር ተነጋግረው በቀይና በአረንጓዴ ክር እንዳልተስማሙ ሲነግረኝ እንደማይስነብቱ ገባኝ። ልጅነት ሳይጨርሱ ልጅ ለመውለድ ማሰብ አስገራሚ ነው። ከሁለት ወራት በኋላ ከዚያ

ወጣት ጋር ተገናኘን። የልጅቷን መጥፎነት እየተንቀጠቀጠ ነገረኝ። እንደተለያዩም ከነገረኝ በኋላ አሁን ደስታ እንዳለው ገለጸልኝ።

ስሜት ማየት የሚገባንን እንዳናይ የሚያደርግ፣ ነገሮችን በትክክለኛ መልካቸው ሳይሆን በስሜት መነጽር እንድናያቸው ስለሚያደርግ ያሳስታል። ስሜታዊነትን ትምህርት፣ ሀብት አያስቀረውም። ይህ የተፈጥሮ ሽለፈት የሚገረዘው በመንፈስ ቅዱስ ስለት፣ በኑሮ ጨንገር ነው። ስሜት ፈጥኖ ይመለክራል፣ ፈጥኖ ይፈርዳል። ትዝብትን እንኳ አይፈራም። የወደድኩትን ውደዱ ብሎ ይጫናል። የጠላኹትን ካልጠላችሁ ብሎ ይቀየማል።

ስሜት ብቻውን ነገሮችን ማሰላሰል የማይችል፣ ያለ ቡድን መኖርን እንደ ሞት የሚቆጥር ነው። እንደ ግመሬ ዝንጀሮ ተከብቦ መውጣትና መግባትን የሚፈልግ የአየር ላይ ንግሥና ነው።

ስሜት በራእይ ላይ ትልቅ እንቅፋት ይፈጥራል። ሳይገባን እንድንጀምር ሳይገባን እንድንተው ያደርገናል። ስሜት ሁልጊዜ ችግሩ ከእኔ ነው ከማለት በሁኔታዎች፣ በራእዩና፣ በሰዎች ማሳበብ ይወዳል። ስሜታውያን የሚታዘዙት ለእውነት ሳይሆን ለማለታቸው ነው። በስሜት ክፉ መናገር፣ በስሜት ቃል መግባት፣ በስሜት መጀመር ቀጥሎ ምን ሆኜ ነው በማለት መጸጸት የስሜታውያን ስቃይ ነው። ስሜት በጎ ቢያደርግም መልሶ ስለሚቆጭ በልቡ ደስታ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ የለውም። ከራእይ እንቅፋቶች አንዱ ስሜት ነው። ራእይ የሚጀምረው ስሜት ተንጠፍጥፎ ሲያልቅ ነው።

12. <u>መቍረጥ አለመቻል</u>

«በጊዜው የሆን እምቢታ የእሺታ ያህል ነው» ይባላል። እሺ እያሉ ሰውን ሲያሹ ከመኖር እምቢ ብሎ ቍርጡን መንገር የሰዎችን ጊዜና ተስፋ የሚያከብር ነውና ትልቅ ስጦታ ነው። እንደ ፖለቲከኛ፣ እንደ ዲፕሎማት እሺና እምቢ የሌለው የሚንቀዋለል ሕይወት በጣም አደገኛ ነው። «ቍርጥ ያጠግባል» ይባላል። ቍርጥ ሥጋው ሳይሆን ቍርጥ ውሳኔ አርኪ መሆኑን የሚገልጽ ነው። ሕይወት የራሳችንን ውሳኔ የምትጠይቅ ሂደት ናት። ከሰውነት ክብራችን አንዱ መወሰን መቻላችን ነው። መወሰን የማይችል ነጻ ሰው ሳይሆን ባሪያ ነው። ብዙ መወሰን የማይችሉ ሰዎች ሌሎች እንዲወስኑላቸው ይፈልጋሉ። ሌሎች በብዙ ነገሮች ሊወስኑልን ቢችሉ እንኳ ራእይንና ነፍሳችንን በተመለከተ ግን ሊወስኑልን አይችሉም።

ለውሳኔ የሚያስፈልገን በመጀመሪያ የእውነት እውቀት ነው። ቀጥሎ የቅኖችና የአስተዋዮች ምክር ነው። ከሁሉ በላይ በነገሩ ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅ ነው። አንዳንድ ጊዜ የእውነትን እውቀት አውቀን ለመወሰን እንቸገራለን። የሕይወት ለውጥ የሚጀምረው ግን ከውሳኔአችን ሰዓት አንሥቶ ነው።

በራእይ ላይ መቍረጥ አለመቻል ትልቅ እንቅፋት ነው። እውቀቱን ጠግበው ቆይ ዛሬ፣ ቆይ ነገ የሚሉ፣ ቀን ተሰጥቶአቸው ቀን የሚጠብቁ፣ ውሳኔ የሌላቸው ልፍስፍሶች፣ ዕድር ጥሩምባ ያልነፋባቸው ሙታኖች ብዙ ናቸው። በዚህ ዓለም ላይ ተመልሰን አንመጣም። እያለፍን እንጂ እየኖርን አይደለም። ዓለም የአቋራጭ መንገድ ናት። በውሳኔ ዓለም ላይ ካልወሰንን የት እንወስናለን? ሰማይማ የውሳኔአችን ደመወዝ ያለበት ስፍራ ነው።

13. <u>አቅም ሁሉን ይሠራል ብሎ ማመን</u>

ገንዘብ የሚመልሰው የገንዘብን ጥያቄ ብቻ ነው። ገንዘብ የሰላምን፣ የፍቅርን፣ የፍትሕን ጥያቄ ለመመለስ አይችልም። «ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ» ስለሚባል በገንዘብ መንግሥተ ሰማያትን እንኳ እንደሚወርሱ የሚያስቡ ሰዎች አሉ። በገንዘብ በአውሮፕላን መሄድ ይቻላል፣ ወደ ሰማይ ቤት መግባት ግን አይቻልም። ገንዘብ በምድር ላይም የማያሟላቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ብዙ ባለ ገንዘቦች በገንዘባቸው ዘበኛ መቅጠር ችለዋል፣ ውስጣዊ ድፍረትን ግን ማግኘት አልቻሉም። በገንዘባቸው ብዙ አወዳሽ ቀጥረዋል፣ የጎሊና ወቀሳን ግን ማራቅ አልቻሉም። ብዙ ሠራተኞችን ሰብስበዋል፣ ጥቂት የልብ ወዳጅ ግን ማትረፍ አልቻሉም። በገንዘባቸው በአውሮፕላን መብረር ችለዋል፣ በጎዳናው ላይ ግን በእግራቸው መሄድ አልቻሉም። ምቹ ፍራሽ መግዛት ችለዋል፣ እንቅልፍን ግን መግዛት አልቻሉም። እውቅ ሐኪሞችን ማግኘት ችለዋል፣ ጤናን ግን ማግኘት አልቻሉም። ገንዘብ የቁሳቁስ ጥያቄ እንጂ መንፈሳዊ ጥያቄን መመለስ አይችልም፤ አቅምም ብቃትም የለውም። አቅም ቢኖረኝ እንዲህ ዓይነት ራእይ ነበረኝ እያሉ የሚናገሩ ሰዎች አሉ። ራእይ ሊኖር የሚችለው በአቅም ብቻ እንደ ሆነ ያስባሉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትልቅ ባለ ራእይ ነበር። ነገር ግን ራሱን የሚያስጠጋበት ጎጆ እንኳ አልነበረውም። ደቀ መዛሙርቱን ያሰለጠነው በገበያ፣ በመስክ ላይ እያስተማረ ነው። ማስታወሻ ያዙ ብሎ እያውቅም ትምህርቱ ግን ከልብ አይጠፋም ነበር። የፕሮግራም መሪ አልነበረውም፣ መርሐ ግብሩ ግን ተበጥብጦ አያውቅም። አገልግሎት የሚመሠረተው በቁሳቁስ ላይ ሳይሆን በጸጋ ላይ ብቻ ነው። ራእይም አገልግሎትና እንድንሠራው የታቀደ ተግባር

ነው። መሠረቱ ጸጋ ብቻ ነው። አቅም ስላለ ራእይ አይመጣም፣ ብዙ ባለ አቅሞች ባለ ራእዮችን ለማጥፋት ሲሯሯጡ እናያለን። ባለ ራእዮች ግን ባለ አቅሞችን መንገድ ያሳያሉ።

14. ተጣዳፊነት

ካለፉት ትውልዶች ይልቅ የመብላት አምሮታችን አልጨመረም። እንደውም ቀንሰናል። ሐኪሞቻችን እንኳ የምግብ ዘበኞች ሆነው ስንት ገደብ ጥለውብናል። ግን ካለፈው ዘመን ይልቅ ጥድፊያ ውስጥ ነን። የሚበላው ትንሽ፣ ጭንቀቱ ግን ብዙ ነው። እልፍ እልፍ የሚሉት በቴሌቪዥን መስኮት የሚቀርቡት ማስታወቂያዎች የሰውን መንፈስ ከማያውቀው ሩጫ ውስጥ አስገብተውታል። በቤት ውስጥ የጋበዝናቸውን እንግዶች ለማጫወት ርእስ የሚሰጠን ቴሌቪዥኑ ነው። ብዙ ወገን ዓለሙ ሁሉ ቀድሞት እርሱ ብቻውን መነሻ መስመር ላይ የተቀመጠ መስሎ ይሰማዋል። መንፈሱ ይሮጣል፣ ነገር ግን የትም አልተንቀሳቀሰም። በቴሌቪዥን የሚታዩት ማስታወቂ ያዎች ዘጠና ዘጠኝ ከመቶ አንጠቀምባቸውም። ነገር ግን ከልባችን እንመለከታቸዋለን። በቤታችን ውስጥ እንኳ ራሳችንን ማየት አንችልም። በዚያች የዕረፍት ክፍል በመፀዳጃ ቤት ራሳችንን እንዳናይ እንኳ እዚያም ብዙ ጋዜጦች ወሬን ሰንቀው ይጠብቁናል። በትልልቅ ብረቶች ላይ የተወጠሩት የማስታወቂያ ሸራዎች በጎዳናው ላይ የማሰብ ነጻነታችንን ገፈውታል። ስለ ቢራ አስበን ሳንጨርስ ስለ ለስላሳ መጠጥ ቀጥሎ ስለ አየር መንገዶች እናያለን። የቀበሌው መታወቂያ አልታደሰም ስለ አየር መንገዶች ምኞት እናማርጣለን። የማይመለከቱን ግን አልለቃችሁም ያሉን የማሰብ ነጻነታችንን የገፈፉን ብዙ ዕይታዎች የውሸት ነዋሪዎች፣ ከራሳችን ጋር የመገናኘት ዕድል የሌሰን ምስኪን ሰዎች አድርገውናል። የእነዚህ ሁሉ ዕይታዎች ፍጻሜ ምንነቱ ወዳልገባን የጎሲና ፍልሚያ፣ የከፋ ጥድፊያ ውስጥ የሚከት ሆኖብናል። ልቡን ከአካሉ ጋር በአንድነት የምናገኘው ሰው እያነሰ ነው። የተረጋጋ ማንነት ያለው ሰው እያለቀ ነው። ስለዚህ የሁሉም ፊት ተጨማዷል። ላቅ እንጂ ደስታ ጠፍቷል።

ከራእይ እንቅፋቶች አንዱ ጥድፊያ ነው። በአገራችን፡- «ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል» ይባላል። ስለዚህ ከመሮጥ በፊት የመቆምን ዋጋ ከፍሎ በቅጡ መታጠቅ ይገባል። ደግመው ሳያስቡ ለመናገር የሚፋጠኑ፣ መልእክቱን በቅጡ ሳይሰሙ ለማድረስ የሚቻኮሉ፣ በአካላቸው ላይ የእግር የበላይነት እንጂ የራስ የበላይነትን ያጡ ወገኖች ብዙ ናቸው። ራእይ እግርን ሲመራ ፍጻሜው ያማረ

ነው። እግር ቀድሞ ራእይ ከመጣ ግን ኪሣራን መቀጠር ነው። የእግር ድርሻው ራእይን መተግበር እንጂ መፍጠር አይደለም። እግር መልእክተኛ፣ ራእይ ግን መልእክቱ ነው።

15. ጊዜያዊ ሞቅታ

በሰማበት ጣዱኛ የሚወዱ፣ የአዲስ ፖለቲካ፣ የአዲስ ሃይማኖት፣ የአዲስ ሰባኪ፣ የአዲስ ጠበል አድማቂዎች የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉ። ስለ ሩጫ ሲወራ የሩጫ ትጥቅ ገዝተው መሮጥ የሚጀምሩ፣ ፖለቲካ ሲጋጋል ጎዳና ዘግተው አላሳልፍም የሚሉ፣ ፍትሕን ፍለጋ የምግብ አድማ ሲደረግ እስከ ስድስት ሰዓት አድማ የሚመቱ፣ ከስድስት ሰዓት በኋላ፡- «ተስማምቶ መኖር ነው የሚሻለው» ብለው የሚሸመግሉ፣ የሃይማኖት ስብከት ሲጧጧፍ ባንዲራ ለብሰው የሚያስተናግዱ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ሲያዩ ዘለው ገብተው መፈክር የሚያሰሙ፣ ከሰልፉ መሐል ማኪያቶ አይተው የሚወጡ፣ ልቅሶ ሲገጥማቸው ጥቁር ለብሰው ዋይ ዋይ የሚሉ፣ ቀብር እስኪደርስ ብለው በዚያው ወጥተው መሸታ ቤት የሚያድሩ፣ ዘፋኝ ሲያስደስታቸው አንገታቸው ላይ ያለውን የሰው ወርቅ አውልቀው የሚሸልሙ፣ ሳይዋጉ እንዳሸነፉ የሚሰማቸው፣ በሰው ንብረት የሚቸሩ፣ ሙሽርነትን ለአምሮት የሚሞሸሩ፣ ትዳር ላይ የሚጠፉ፣ ሁሉ በሁሉ መሆን የሚያምራቸው፣ ላያቸው ሰው ማራኪዎች፣ አብሮአቸው ለሚኖር ሬሣዎች የሆኑ፣ በጊዜያዊ ሞቅታ የሚወዘወዙ፣ ወንዝ አድማቂዎች ብዙ ናቸው።

በዚሁ አመል ራእይ የሚጀምሩ ለመዝለቅ ግን የሚፈተኑ አያሌ ናቸው። ራእይ ቋሚ አድራሻ ይፈልጋል። ቋሚ ቢሮ ሳይሆን ቋሚ ልብ ይሻል። በየዕለቱ ፈርሰው የሚሠሩ ባለ ራእይ መሆን አይችሉም። በእውነት ጊዜያዊ ሞቅታ የራእይ እንቅፋት ነው። ሰው የሚሰክረው በመጠጥ ብቻ አይደለም። ሰው በስሜትም ይሰክራል። እነዚህ ሰዎች ምርጥ ምርጡ ለእኔ የሚሉ፣ ሁሉም ሰው ለእነርሱ የተፈጠረ አድርገው የሚንፈላሰሱበት፣ ውሃ ልትቀዳ እንደ ወረደች ጨው በሄዱበት ሚሙተው የሚቀሩ፣ ተስፋ የተሞሉ የሚመስሉ የተስፋቸው ኃይል ግን ደካማ የሆነባቸው ወገኖች ናቸው። ይህ ባሕርይ የራእይ ትልቅ እንቅፋት ነው።

16. ሰበበኛነት

በገነት የጀመረው የሰው ባሕርይ ሰበበኛነት ወይም ምክንያተኝነት ነው (ዘፍ. 3፥12-13)። ለተከሰቱ ጉድለቶች ኃላፊነት

አለመውሰድ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰው ባሕርይ ሆኗል። የሰው ልጅ ያልሠራውን በጎ ሥራ የራሱ አድርጎ ሲያወራ የሠራውን ክፉ ሥራ ግን ማከፋፈል ለራሱም ትንሽ ድርሻ መውሰድ ይወዳል። እንዲህ ያደረኩት ወጣትነቴ፣ ግፊቴ፣ ርእዮተ ዓለሙ... ይላል። በራእይ ላይ ስበበኛነት ትልቅ እንቅፋት ነው።

ብዙዎች ራእይ ለመጀመር ብሎም ለመዝለቅ ምክንያት መሰናክል ሆኖባቸዋል። ራእያቸውን ለመጀመር የሚያቀርቡት ሰበብ ጤናዬ፣ አቅም፣ ትዳሬ፣ ትምህርቴ፣ ተሽቀዳድሜ ጀምሬ ባቋርጥስ፣ ሰዎች ባይቀበሉኝስ፣ ... የሚል ነው። ራእያቸውን ለመፈጸምም የሚያቀርቡት ሰበብ እነ እገሌ ከእኛ በላይ ደክመው ምን አመጡ? ተቃዋሚዎቻችን ከእኛ ይልቅ እየበረቱ ነው፣ ችግሩ እየጨመረ ነው፣ የደከምንላቸው ምን ጥሩ ምላሽ ሰጡን?... የሚል ነው። በራእይ ውስጥ ምክንያታችን ራእዩን መፈጸም ብቻ እንጂ ላለመፈጸም ምክንያት ማቅረብ አንዳች ጠቀሜታ የለውም። በራእያችን ከታወቅን በኋላ ያለ ራእያችን ተቀባይነት አናገኝም። በዙሪያው ያለ ግፊት ቢጨምርም፣ አብረውን የሚሠሩ ታካቾች ቢሆኑ፣ እኛ ብቻ የምንሮጥ መስሎ ቢሰማን ወደ ፊት መገስገስ ብቻ ይገባናል። ራእይ እንኳን በሰበብ በሰይፍም አይቆምም።

17. <u>በትንሽ መርካት</u>

በራእይ ውስጥ ከሚገጥሙን ጋሬጣዎች አንዱ በትንሹ መርካት ነው። ትንሽ ግዛቶች ሲለቀቁ ባንዲራ ሰቅሎ ለመሠረግ ማሰብ፣ ጥቂት ሰዎች ሲቀበሉን በቂ ነው ብሎ ተዝናንቶ መቀመጥ፣ የተወሰኑ ወገኖችን ማኖር ስለ ቻልን ያንን እየተረኩ መቀመጥ ለራእይ እንቅፋት ነው። በትንሹ የሚረኩ ሰዎች ከጨለማ በመውጣታቸው ይረካሉ፣ ሙሉ በሙሉ ብርሃኑን ግን አልያዙም። ከግብፅ በመውጣታቸው ይዘምራሉ፣ ከነዓን ለመግባት ግን ይታክታሉ። በትንሹ ስንረካ ብርሃናችን ወደ ጨለማ ሊለወጥ፣ ነጻነታችንም ወደ ባርነት ሊቀየር ይችላል። በትንሹ የሚረኩ ሰዎች ከዚህ በኋላ መታገል አይፈልጉም። የበለጠ ለማየት አይጓጉም። ውጤቱ ግን በትንሹ ድል እየረኩ መዘለቅ ሲያቅታቸው ወደ መጡበት ለመመለስ ይፈልጋሉ። ቀላል መስሎ የሚሰማቸውን ብቻ ያደርጋሉ እንጂ እውነት የቱ ነው? አይሉም።

አንድ ጥቅስ ይዘው የሚዋጉ ተማሪዎች፣ ጥቂት እውቀት ጨብጠው አስተማሪዎቻቸውን የሚንቁ ደቀ መዛሙርቶች፣ ውስን ሀብት ዘግነው አለቆቻቸውን የሚያዋርዱ አዲስ ግልብጦች፣ አንድ

ቁና ሰፍተው ያንን ሲተርኩ የሚኖሩ ባለ ራእዮች በትንሹ የረኩ ናቸው። እነዚህ መርካታቸው ወደ መርጋት ይለውጥና ጎጂ ይሆናሉ። ታሪካቸውን፣ የዘመቱበትን ግንባር፣ ያሳለፉትን ሰቆቃ እየተረኩ አዲስ ጀሮን ሲያስደምሙ ይኖራሉ። ለለመዳቸው ግን ይሰለቻሉ። በትንሹ መርካት የራእይ እንቅፋት ነው።

18. <u>መቸገርን አለመፈለግ</u>

ለእውነት ሳይሆን ለምኞት እንደ ተፈጠሩ የሚያስቡ ሰዎች ብዙ ናቸው። እውነትን እንኳ የሚፈልጉት ምኞትን ለማስከበር ነው። በዛሬው ዘመን ብዙ አማንያን ወደ የአብያተ ክርስቲያናቱ ይጎርፋሉ። አብዛኞቹ የቁሳዊ ስብከቶች ተከታይ ናቸው። ዛሬን ለመርሳት እንጂ ከኃጢአት ለመፈወስ አሳብ እንኳ የላቸውም። የሚናገሩትም ሆነ ሊሰሙ የሚፈልጉት የመሞላቀቅ ወሬዎችን ነው። ጠንከር ያሉ የሕይወት እውነቶችን መናገርም ሆነ መስማት አይፈልጉም። ጠንከር ስላለ ነገር ከማውራት ላይ ላዩን መኖር፣ ሥጋውን ከመብላት መረቁን መጠጣት፣ ዳቦውን ከመጥገብ ዳቦውን መላስ፣ ወደ ግዛቱ ከመዝለቅ ድንበሩን መዞር ይፈልጋሉ። የሰዎችንም ችግር ለመስማት ስለማይፈልጉ መረዳት አይችሉም። የእንግሊዝ ንግሥት ልጅ ሰው ተራበ ቢሏት፦ «ለምን አይስክሬም አይበሉም፣ ቢጠፋ ቢጠፋ አይስክሬም ይጠፋል ወይ?» አለች ይባላል። እርሷ ጎድሎባት ስለማታውቅ ጉድለትን መረዳት አይሆንላትም። የእርስዎ ትንሽ ወጪ ዋ የአይስክሬም ወጪ ነው። ሁሉንም እንደ ራሷ በማየት ማዘን እንኳ አልቻለችም።

መቸገርን የማይፈልጉ ሰዎች ባለ ራእይ ለመሆን በፍጹም አይችሉም። ራእይንም ሆነ ማንኛውም ነገር የሚከተሉት፣ ዋጋ እስካላስከፈለ ድረስ ብቻ ነው። ራእይ ደግሞ በባሕርይው ዋጋ ያስከፍላል። የትኛውም የዘመን ሥልጣኔ የራእይን ዋጋ ሊያስቀረው አይችልም። ራእይን እየወደድን ዋጋውን መጥላት አይቻልም። «ወንድ ወደሽ ጢሙን ጠልተሽ» እንዲሉ። ወንድን ያለ ጢሙ ማማኘት ከባድ እንደ ሆነ ራእይንም ያለ ዋጋው ማግኘት እጅግ ከባድ ነው። መቸገርን የማይፈልጉ ሰዎች ባለ ራእይ መሆን አይችሉም።

19. <u>የኋላ ታሪክና ልምድ</u>

ክርስትና ወደ ፊት የምንጓዝበት የቆራጥነት ሂደት ነው። የሁላችንም የኋላ ታሪካችን የሚያኮራ፣ ብርሃን የለበሰ አይደለም። ብዙ የጽልመት መጋረጃዎች፣ ያለ ማወቅ ሸክሞች ያሉበት አንዳንዱም

አንገት የሚያስደፋ ታሪክ ነው። ታሪካችን ለራሳችን ብቻ ሳይሆን በዙሪያችን ላሉትም የተገለጠ ሊሆን ይችላል። እውነተኛ ነዋሪ ግን ከትላንት ይማራል እንጂ በትላንት ሲቆዝም አይኖርም። ታሪክ ላይ መቆየት አመድ ላይ መንከባለል ነው። የትላንቱን ቀን ወደ ኋላ መልሰን እንደ ገና መኖር ወይም ማስተካከል አንችልም። የዛሬ መለወጥ ግን የትላንትን ስህተት የሚክስ ነው። ይህን ታሪክ ይገፍ እንዴት ባለ ራእይ እሆናለሁ የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ሁሉም ሰው የሚያውቀው አዳፋ ታሪክ ካለን፣ የእኛን የአደባባይ ንስሐ ብዙዎች የሚጠብቁት ከሆነ፣ በግል ታሪካችን ራእያችን እንዳይሰናከል የአደባባይ ንስሐ ማድረግ ይገባናል። ራእይ ባይኖረን እንኳ ንስሐ መግባት አንዱ ራእያችን ሊሆን ይገባዋል።

ለራእያችን እንቅፋት የሚሆነው ታሪካችን ብቻ ሳይሆን ልምዳችንም ነው። እየተከበርን መኖርን የለመድን አክባሪዎች ልንሆን እንችላለን። መብታችንን ለማስከበር የኖርን ከማንም ጋር በመብታችንና በክብራችን ተደራድረን የማናውቅ ሰዎች ልንሆን እንችላለን። ደህና ደህና መብላትን የለመድን፣ እስክሞት ድረስ ከገበታዬ ላይ ይህ ምግብ አይጠፋም ብለን የምንፎክር ልንሆን እንችላለን። ራእይን ለመጀመር ግን መሞት እንደሚጠይቅ መገንዘብ አለብን።

20- ጊዜ አለመስጠት

ራእይ የማይፈልገው ነገር ብቻ ሳይሆን የሚፈልገውም ነገር አለ። እንቅፋትን መጠንቀቅ ብቻ አይበቃም፣ የምንሠዋው ነገርም አለ። ስለማይገቡ ነገሮች አጥንተን ስለሚገቡ ነገሮች ዝም ብንል ራእይ አይሟላም። መሆን ያለበት ከተረሳ ድካም ከንቱ ነው። ክፉን አጽድቶ በጎን ያላስገባ ባዶ ቤት ነው። በዓለም ላይ ደግሞ እንደ ባዶ ነገር የሚያስፈራ ምንም ነገር የለም (ማቴ. 12÷43-45)።

ራእይ የሚፈልገው ዋነኛ ነገር ጊዜ ነው። እግዚአብሔር ከሰጠን ትልቅ ስጦታዎች አንዱ ጊዜ ነው። ለራእይም ጊዜ መስጠት ትልቅ በጀት ነው። ጊዜ ሲኖር የምንሠራው ይታየናል፣ ይኖረናል። ጊዜ ሲኖር ራእዩን መመልከት ይቻለናል። የዚህ ዓለም ኑሮአችን በጊዜ የተለካ ነው። ሥራዎቻችንን የምናከናውነው በጊዜ ውስጥ ነው። ሥራዎቻችን ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኘውም በጊዜ ውስጥ ነው። ይልቁንም ኑሮአችን በሕይወትና በሞት መካከል ወይም በሰንጣቃ ዓለት ውስጥ እንደ ማለፍ በመሆኑ ጊዜ ለነዋሪው ትልቅ ነገር ነው። ጠቢቡ ሰሎሞን የዓለምን ተለዋዋጭነት በገለጸበት እንቀጽ፦ «ለሁሉ ዘመን አለው» (መክ. 3÷1) ብሏል። ለሁሉም ጊዜ ካለው፣ ለማንፈልገው ውድቀትና ስብራትም ጊዜ አለው።

ልንፈልገው ስለማንባው ራእይማ ጊዜ ወሳኝ ነው። ጊዜያችን ለራእይ ባይውል ለሌላ ክፉ ነገር መዋሉ ግድ ነው። ስለዚህ ጊዜን የምንቀድሰው ለዕድሜ ጣዕም ነው። በጊዜ ካልሠራንበት ጊዜ ራሱ ሠርቶብን ያልፋል።

ራእይ ሕይወታችንን፣ አገልግሎታችንን፣ ገንዘባችንን ይፈልጋል። ገንዘብ የአገልግሎት፣ አገልግሎትም የሕይወት ምትክ አይደለም። እነዚህ ተግባራት በተራቸው ያስፈልጉናል። አገልግሎት የምንለው ጊዜ መስጠት ነው። ለራእያችን ገንዘብ መድበን ጊዜ የምንነፍገው መሆን በፍጹም የለበትም። ይልቁንም በሚያልፍ ዕድሜ የማያልፈውን ነገር ለመሥራት መነሣት ያስፈልገናል።

ባለንበት ዘመን ብዙዎች የጊዜ ምስኪን ሆነዋል። የሚያስቡት እየበዛ ውጤቱ ያንስባቸዋል። ሁለት ሲያባርሩ አንዱን መያዝ አቅቷቸዋል። የጊዜን ክብርና አጠቃቀም ባለማወቅ ጊዜ ያልፋል። እንከን የሌለው የእግዚአብሔር ስጦታ ቢኖር ጊዜ ነው። ጊዜ ውድ መሆኑ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ብቻ የሚሰጠን ስጦታ ነው። ጊዜን መጠቀምም ሆነ ጊዜን ማድፋፋት ሁለቱም ይቻላል። ይህ በእጃችን ያለ ዕድልና ምርጫ ነው። ራእይ አለኝ ግን ጊዜ የለኝም የሚሉ ወገኖች ይኖራሉ። ጊዜ ስጥታቸውም ሲንቀዋለሉ የሚመሸባቸው የሠሩ እየመሰላቸው ራሳቸውን ሲያታልሉ የሚውሉ ይኖራሉ። ጊዜ ማጣቱም ጊዜ ማባክኑም ችግር ነው። ጊዜ ሙሉ የሆነ የእግዚአብሔር ስጦታ ከሆነ እንዴት ሊያጥረን ይችላል? ጊዜ የለኝም የሚለውስ እውነተኛ ድምፅ ነው ወይ? ወዳየነው ሁሉ በመሮጥ ያለ ዕረፍት መኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው? ብለን መጠየቅ ያስፈልገናል። ገንዘብን ከፍቅር ጋር፣ ራእይን ከቀኖቀኑስ ጋር የሚያወዳድሩ ቋንቋቸው ሁሉ ሂሳብ የሆነ ሰዎች ለፍቅርና ለራእይ ጊዜ ሊኖራቸው አይችልም። በእውነቱ እንደ መልካም ነገር ጊዜ የሚፈልግ ምንም ነገር የለም። በእጮኛነትና በትዳር ውስጥ እንኳ ክፍተት የሚፈጠረው ጊዜ ባለ መስጠት ነው። ራእይም ጊዜ በማጣት ስብራት ሊገጥመው ይችላል። በዛሬው ዘመን ሰይጣን ሰዎችን የጊዜ ምስኪን እያደረጋቸው ይገኛል። ዓለምም ጊዜን ስታዋቅር ሰተፈጠርንበት ዓላማ እንዳይተርፈን በማድረግ ነው። ስለዚህ ጊዜን የምናገኘው በተለመደው አካሄድ ብቻ ሳይሆን በመሥዋዕትነት ጭምር ነው።

ራእይ የሚጀምረው ገንዘብን ጉልበትን በማስቀመጥ ሳይሆን ሕይወትን በማስቀመጥ ነው። ስለዚህ ሕይወቱን ያስቀመጠ ጊዜውንና ጥቅሙን ለመተው አይፈተንም። ወርቅ የሰጠ በነሐስ

እንደማይጠረጠር የሚበልጠውን ያስቀመጠም በሚያንሰው አይጠረጠርም::

በጣም ጊዜ እንደ ሌላቸው የሚናገሩ ሰዎች አሉ:: አንዳንዶቹ:- «የድሃ ጉልበት በሳመንዘር ያልቃል» እንደሚባል በማይረባ ነገር ጊዜያቸውን በማባከን ነው:: ሌሎቹ ደግሞ ራሳቸውንና ድርሻቸውን ለይተው ባለማወቅና ጊዜ የለኝም ማለት ዘመናዊነት ስለሚመስላቸው ነው:: ሌሎችም ውሳኔ ባላደረጉበት ነገር ጊዜያቸው ያልቃል:: ጊዜ ካድፋፉት ያልቃል:: መች ይበቃል! ለሚጠቀሙበት ደግሞ ጊዜ ከአድማስ ይረዝማል፣ ከባሕር ይጠልቃል፣ ከሰማይ ይመጥቃል::

የምናስፈልግበትን ቦታ ለይቶ ማወቅና ለዚያም ጊዜ መመደብ እንዴት ያለ መታደል ነው! እኛ የምናስፈልግበትና ውጤታማ የምንሆንበት ጊዜ አለው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ:- *«ጌታ ሆይ፥ አስቀድሜ እንድሄድ አባቴን እንድቀብር ፍቀድልኝ»* ቢለው *«ተከተለኝ፥ ሙታናቸውንም እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው»* አለው (ማቴ. 8፥21-22):: ጌታችን:- «የልቅሶ ሥርዓትንና የሬሳ ሽኝት መርሐ ግብርን ካንተ በበለጠ የሚያውቁና የሚያስተናብሩ አሉ፣ ኖርክም አልኖርክም ውጤት በማታመጣበት ቦታ ላይ ጊዜ አታጥፋ፤ ይልቁንስ አንተ ከሌለህበት በውክልና የማይሠራውን የነፍስህን ሥራ አወቅበት» ማለቱ ነው:: በሌላ ስፍራም ጌታችን አየሱስ ክርስቶስ:- *«ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች»* (ዮሐ. 9፥4) ብሏል:: ቀን ያለው ዕድልን ነው:: ዕድልና ደግ ንጉሥ ሳሉ መትጋት ተገቢ ነው:: ንጉሥና የጊዜ ዕድልን መጠቀም ተገቢ ነው፤ ያልፋሉና:: ሥራ መሥራት የማይቻልበት ጊዜ ይመጣል:: የብዙዎች ቊጭት ማድረግ በሚችሉበት ጊዜ ያላደረጉትን ማድረግ በማይችሉበት ሰዓት ማሰብ ነው::

ስለ ጊዜ ስለ ሰዓትና ስለ ደቂቃ የማያስበው ወገን ስለ ዕድሜው በጣም ይጨነቃል:: ደቂቃና ሰዓት ተጠራቅመው ዕድሜ እንደሚሆኑ የሚያስብ ግን ጥቂት ነው:: ንጉሡም ሺህ ዓመት ንገሥ እንዲባል፣ ጎበዙም እንደ ማቱሳላ ዕድሜህ ይርዘም መባልን ይመኛል:: እንደውም የብዙ ሰው ምጽዋት ረጅም ዕድሜ የሚያሰጥ ምርቃት ለመስማት ነው:: ዕድሜ የሚመኙ ለመለወጥ የሚያስቡት በቀጠሮ እንጂ በውሳኔ አይደለም:: ዛሬ ማድረግ የሚችሉትን በወደፊት ዕድሜ ለማድረግ ይመኛሉ:: ኃጢአትን አልጠንብኩም ከማለት ዕድሜ ለንስሓ ስጠኝ እያሉ ይጸልያሉ:: ጊዜ በጣም ስለተንዛዛ አይሠራበትም፣ ስላጠረም ሳይሠራ አይቀርም:: ዛሬን

እንደ መጨረሻ ቀናችን አድርገን ስንኖር ግን የተፈጥሮ ግባችንን አሟልተን ጊዜ በቅቶን እናልፋለን:: ማቱሳላ 969 ዓመት ኖረ ቢባልም ይህን ሠራ ተብሎ ግን አልተጻፈም:: ወጣቱ እስጢፋኖስ ግን በወጣትነት ለጋ ዕድሜው መቅረዝ ሆኖ አልፏል:: ጌታችን ሞልቶ ከተረፈውና የራሱ ስጦታ ከሆነው ዕድሜ በዚህ ዓለም ላይ የኖረው ሠላሳ ሦስት ዓመታት ከሦስት ወራት ብቻ ነው:: ተልዕኮን ከፈጸሙ በዚህ ዓለም ብዙ ዘመን መቆየት ያን ያህል ጠቃሚ አይደለም::

ንጉሥ ሕዝቅያስ ዕድሜው እንዳበቃ በሰማ ጊዜ ምርር ብሎ አለቀሰ:: እግዚአብሔርም ራርቶ 15 ዓመት በዕድሜው ላይ ጨመረለት (ኢሳ. 38፥1-5):: ሕዝቅያስ አንድ ጊዜ ዕድሜ ተጨመረለት:: እኛ ግን ብዙ ጊዜ ዕድሜ ተጨምሮልናል:: በተጨመረ ዕድሜ የምንኖር ከሆነ የእኛ ባልሆነ ዕድሜ የምንኖር ነንና ዕድሜያችንን ለእግዚአብሔር ማስረከብ አለብን::

በእውነት ጊዜ የለንም ይሆን? የዓለማችን ቍጥር አንድ ባለጠጋ ቢልጌት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሠራተኞችን በዓለም ዙሪያ ያስተዳድራል:: ይህ ሰው የፈጠራ ሰው በመሆኑና ከሀብቱም ብዛት የተነሣ ጊዜ አለው ብሎ መገመት ይከብድ ይሆናል:: ለዚህ ነው ጋዜጠኞቹ:- «ጊዜ አለህ ወይ?» ብለው የጠየቁት:: እርሱ ግን ሲመልስ:- «ሥራዬን የምሠራበት፣ መጻሕፍት የማነብበት፣ በፀጥታ የምቀመጥበት፣ ከቤተሰቤ ጋር የማሳልፍበት፣ እንግዶቼን የማስተናግድበት፣ ሥራዬን የምቆጣጠርበት በቂ ጊዜ አለኝ?» ብሏል:: ጊዜ እንደሌለን የምናስብ ከዚህ ሰው የበለጠ ሩጫ ኖሮብን ይሆን?

ጊዜያችንን የምናወጣበት የጊዜ ቼክ ቢኖረንና በዓመቱ ላይ ማየት ብንችል ሰፊ ጊዜ የምናጠፋበት ነገር በልባችን ትልቅ ስፍራ የሰጠነው ነገር መሆኑን እንረዳ ነበር:: ሰፊ ጊዜያችንን የምናጠፋው ፊልም ላይ አሊያም ኪስ ጨዋታ ላይ ከሆነ በልባችን ትልቁን ስፍራ የወሰደው ይህ ነው ማለት ነው:: ራእያችን ሕይወታችንን ሲረከብ ጊዜያችንን በደንብ ያገኛል::

በአገራችን ያለንን የሰዓት አጠቃቀም ማየት ብንችል 24ቱ ሰዓት በምን እንደ ተያዘ መረዳት እንችላለን:-

8 ሰዓት ለሥራ
8 ሰዓት ለመኝታ
3 ሰዓት ለትራንስፖርት
1 ሰዓት ለመዋብ

2 ሰዓት ለምግብ (ቊርስ፣ ሻይ፣ ምሳ...)
30 ደቂቃ ዜና ለመስማት
30 ደቂቃ ከባልንጀሮቻችን ጋር ለመጫወት

ራርተን እዚህ ላይ ብናቆመው በአጠቃላይ 23 ሰዓት ፈጅተናል። ይህ ትንሽ ግምት ነው። ቢሆንም ለተፈጠርንበት ዓላማ የቀረን ስንት ሰዓት ነው? ስንል አንድ ሰዓት ብቻ ነው። ይህን በዓመት ውስጥ ስንደምረው 365 ሰዓት ይሰጠናል። ይህም ወደ ቀን ሲለወጥ በአንድ ዓመት ውስጥ 15 ቀን ከ20 ሰዓት አካባቢ ብቻ ይሆናል። በአንድ ዓመት ውስጥ 15 ቀን ካተረፍን በ40 ዓመት ውስጥ የምናተርፈው 600 ቀን ወይም ሁለት ዓመት ያልሞላ ነው። ነቢዩ በዘመኑ የነበረውን የዕድሜ ስፍር ሲናገር 80 ዓመት ነበር። እኛም እንደ ቸርነቱ 80 ዓመት ብንቆይ ለተፈጠርንበት ዓላማ የሚኖረን 4 ዓመት ብቻ ነው ማለት ነው። በሕይወታችን ለራሱ እንድንሆን ለፈጠረን ጌታና ለተፈጠርንበት ራእይ ያለን ጊዜ በጣም አነስተኛ ነው።

ጊዜ የለኝም ብለን ልናስብ እንችላለን። በርግጥም በማናውቀው ምክንያት ጊዜ አጥተን ተወጥረን ይሆናል። በጊዜ ውስጥ ያሉን ጉዳዮች ግን ሦስት ናቸው።

1. የማያስፈልግ የማያስቸኩል፤
2. የሚያስፈልግ የማያስቸኩል፤
3. የሚያስፈልግ የሚያስቸኩል፤

አንዳንዱ ጉዳያችን ፈጽሞ ልንጥለው የሚገባን የማያስፈልግና የማያስቸኩል ነው። ሌላው ደግሞ ቢያስፈልግም ጊዜ የሚሰጥ የማያስቸኩል ነው። ሦስተኛው ግን አንገብጋቢ የሆነና የሚያስፈልግ የሚያስቸኩል ነው። ብዙዎቻችን ጊዜያችንን የምናባክነው በተራ ቊጥር 1 እና 2 ላይ በተቀመጡት ጉዳዮች ላይ ነው። በማያስፈልግና በማያስቸኩል ደግሞም በሚያስፈልግና የማያስቸኩል ጉዳይ ላይ ጊዜአችንን እንጨርስና የሚያስፈልገውና የሚያስቸኩለው ትዝ ሲለን ወይኔ ጊዜ አጣሁ እንላለን። ስለዚህ በእነዚህ ሦስት ጉዳዮች ላይ ነጥቦችን መስጠት አለብን።

የማያስፈልግ የማያስቸኩል	X
የሚያስፈልግ የማያስቸኩል	½
የሚያስፈልግ የሚያስቸኩል	√

የማያስፈልግና የማያስቸኩለውን በቆራጥነት መሰረዝ፣ የሚያስፈልግ ግን የማያስቸኩለውን ለሌላ ቀጠሮ ማስተላለፍ፣ የሚያስፈልገውንና የሚያስቸኩለውን ዛሬ ስናከናውን ጊዜ በቅቶን ይተርፈናል። እንደውም ሰፊ የጊዜ ክፍተት ስለሚኖር የምንሞላበትን ነገር አስቀድመን ማሰብ ያስፈልገናል። ሌላው የጊዜ ስሌት የሚቀድመውን ካስቀደምን ለሚከተለው ጊዜ አለው የሚል ነው። ለዚህም የተለመደና ቀላል ምሳሌ ይቀርባል፦

- የከበረ ድንጋይ
- ኮረት
- አሸዋ
- ዱቄት
- ውኃ

እነዚህን ነገሮች በአንድ አፈ ሰፊ የውኃ ማቅረቢያ ውስጥ ማስቀመጥ ብንጀምር፦ የከበረ ድንጋዩ ከሥር ይቀመጣል፣ በመጠን የሚያንሰውን ኮረት ስንከተ ኮረቱ በከበረው ድንጋይ መሐል ይገባል፣ በኮረቱ ክፍተት ደግሞ የምንጨምረው አሸዋ ይሰርጋል፣ በአሸዋ ክፍተት ውስጥ ደግሞ የሚደቀው ዱቄት ሲገባ እሁን የሞላና ምንም መጨመር የማይቻል ይመስላል። ነገር ግን ከዱቄቱ ያነሰ መጠን ያለው ነገር መግባት ይችላል። እርሱም ውኃ ነው። ይህ ጠርሙስ ይህን ሁሉ ማስተናገድ የቻለው የሚቀድመው ስለ ቀደመ ነው። በሌላ ጠርሙስ ውስጥ ቀጥሎ በተጠቀሰው ተራ ብንከተ ሞልቶ ይፈሳል፦

- ውኃ
- ዱቄት
- አሸዋ
- ኮረት
- የከበረ ድንጋይ

በሕይወታችንም የሚቀድመው ሲቀድም ለሚከተለው ጊዜ ይኖረዋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፦ *«ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል»* (ማቴ. 6፥33) ብሏል። በሕይወታችን ጉድለት የሚያጠቃን ሁለተኛን አንደኛ፣ አንደኛን ሁለተኛ ላይ አድርገን ስለምንኖር ነው።

ሰይጣን በዛሬው ዘመን ሰዎችን ከበጎ ተግባራት ሁሉ የሚለየው ጊዜያቸውን በመዋጋት ነው። እርሱ ከበረከቶቻችን ጋር ትግል የለውም፣ ጊዜያችንን በሚመስል ነገር ፈጽመን ከሞት በኋላ ዘላለም የእርሱ እንድንሆን ግን ይታገለናል። በዓለም ዙሪያ ሁሉ

የሚኖሩ ሰዎች ጊዜን በማጣት ከራሳቸው፣ ከቤተሰባቸውና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት እየተሰበረ ነው። ጊዜ ማጣት ውስጥ ስንገባ የሰይጣን ዋነኛ የውጊያ ማዕከል ውስጥ ገብተናል ማለት ነው።

ሰይጣን ሰዎችን ጊዜ የለሽ የሚያደርጋቸው አእምሮአቸውን በመወጠር፣ ዕዳ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግና ዕዳውን ለመክፈል በማሯሯጥ፣ ተፈጥሮን በማድነቅ እግዚአብሔርን እንዳያዩ ዓይናቸውን በመጋረድ ሰው ሠራሹን ነገር አሳምሮ በማሳየት፣ በጨዋታና በቁማር፣ ተስፋ በመስጠትና በሚመስሉ ነገሮች በማሯሯጥ፣ ሥራ ሥራ በሚል ምክንያታዊነት ነው። የሰይጣን ዓላማ የሰከነ አእምሮ መንሣት፣ ቤተሰብን ማፍረስና ከእግዚአብሔር መለየት ነው።

በራእይ ውስጥም ሰይጣን ጊዜ የለሽ በማድረግ «የተወለደው እንዳያድግ» ሲዋጋን የማያሳድገውን ልጅ እንደ ወለደ ተወቃሽ አባት ሊያደርገን ይታገሰናል። ቀጥተኛ በሆነ ስልት፣ በሰይፍ ስለትና በሰማዕትነት ጽዋ ከእግዚአብሔርና ከራእያችን የመለየት ዘዴን ሰይጣን በዛሬው ዘመን አይጠቀምም። ይህን ሰዎች በቀላሉ ስለሚያውቁበት አላቡን አይፈጽምም። ስለዚህ በሚመስል ነገር ጊዜ የለሽ በማድረግ፣ ጊዜን በሚበላ ዘመናዊ ብል ወይም ነቀዝ ያሯሩጠናል። ያለንበት ሁኔታ ለአእምሮአችን ካሳመነን እግዚአብሔር እንደሚያምን አድርጎ ያቀርብልናል። በጣም የሚገርመው ጊዜ የለንም ይሉ የነበሩ ወገኖቻችን ዛሬ በሕይወት የሉም። እግዚአብሔር በሞት ሲጠራቸው ግን ጊዜ የለንም ብለው አልቀሩም።

ራእይ ጊዜ ይፈልጋል። ይልቁንም የዘመናት ስፍር እየተሟጠጠ ባለበት በዚህ በመጨረሻው ዘመን ጊዜ መስጠት ያስፈልገናል። ነገሮች ሁሉ በድንገት ቀጥ ይላሉ። ነገሥታት ስብሰባቸውን ሳይጨርሱ፣ አንዱ ንጉሥ ዐረፍተ ነገር ሊያጋጥም «እኔ» ሲል፣ አውሮፕላኖች የያዙትን መንገደኛ ለማድረስ በአየር ላይ ሳሉ፣ ሯጮች የሩጫውን ገመድ ሳይበጥሱ ገና እየሮጡ፣ ደራሲው አንቀጹን ሳያሟላ፣ ሌሊት ያደረው ጠባቂ እቤቱ ሳይመለስ፣ አንባቢው ወደሚቀጥለው ምዕራፍ ሳይሸጋገር፣ ከብቷን የሚያልበው ሁለተኛውን ግት ሳይጨብጥ፣ የሚዋጉ ወታደሮች አሸናፊና ተሸናፊ ሳይለይ . . . ሁሉም ነገር በድንገት ቀጥ ይላል። እግዚአብሔር ይቁም ሲል የሚቀጥል ይታጣል።

የራእይ እንቅፋቶች ብለን የጠቀስናቸው እነዚህ ወደ ሃያ የሚጠጉ ዝርዝሮች ዋና ዋናዎቹ እንጂ ሁሉም ሳይሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ከራእዩ በፊትና በኋላ ሊነሡ የሚችሉ ውስጣዊ ማዕበሎች ናቸው።

እናስተውል

- መርከብ አቅጣጫውን በትክክልና በቀጥታ ከያዘ ደግሞም ሞተሩ ካልተበላሸ ከወደቡ ይደርሳል።
- ዛሬ ልንሠራ የሚገባንን ነገ ማዘግየት በሕይወት ላይ ትልቅ ጥፋትን እንደሚያስከትል ማወቅ አለብን።
- ያለ ራእይ ከሚኖሩ ይልቅ በራእይ የሚሞቱ ሲታወሱ ይኖራሉ። ከሞት ይልቅ ልንፈራው የሚገባው ራእይ አልባነትን ነው።
- ደስታ ያለው ስኬት የሚገኘው በራእይ ውስጥ ነው። የማያረካ ስኬት ግን ያለ ራእይም ሊገኝ ይችላል።
- ባለ ራእይነት በራእይ የለሾች ትገፋለች።
- ታሪክና እሴት የራእይ ኃይል አይሆንም። የራእይ ኃይል ከራእይ የሚወጣ መለኮታዊ ጸጋ ነው።
- ለእያንዳንዱ ቀን እንግዳ በሆንበት ዓለም ላይ የማናውቀው ነገር ብዙ ነው። የማናውቀው ፈተናም ስላለ የዛሬ ፍጹምነት ለነገ አይረዳም።
- መኪና የሚሄደው በአንደኛ ማርሽ እንጂ በዜሮ አይደለም። ስለዚህ ጅምር ያስፈልጋል።
- ራእይ በሌለው በጨለማው ዓለም ባለ ራእዮች በሩቅ ይታያሉ።
- ባለ ራእዮች ግን ዕድልን ይፈጥራሉ እንጂ አይጠብቁም።
- ራእይ በነጻ የምንቀበለው በዋጋ የምንፈጽመው ነው።
- መንፈሰ ቀዝቃዛነት የራእይን ግለት የሚያጠፋ የሞት መንፈስ ነው።
- መድረሻውን ያየ በጎዳናው ይሄዳል እንጂ በመንገዶች ሁሉ አይሄድም።
- ራእይ የሚጀምረው ስሜት ተንጠፍጥፎ ሲያልቅ ነው።
- ራእይ እግርን ሲመራ ፍጻሜው ያማረ ነው። እግር ቀድሞ ራእይ ከመጣ ግን ኪሣራን መቀጠር ነው።
- ራእይ ቋሚ አድራሻ ይፈልጋል። ቋሚ ቢሮ ሳይሆን ቋሚ ልብ ይሻል።
- ራእይ የሚጀምረው ገንዘብን ጉልበትን በማስቀመጥ ሳይሆን ሕይወትን በማስቀመጥ ነው።

ምዕራፍ ሃያ ሦስት

ውጫዊ መሰናክሎች

አንድ ምሳሌ አለ፡- ደመና፣ ስስትና አሉ በአንድነት ሆነው ጉዞ ጀመሩ። ደመና ተራራ ሲያገኝ ማረፊያዬ እዚህ ነው ብሎ ስስትና አሉን ተሰናብቶ ቀረ። ስስትና አሉም አብረው ሲጓዙ፣ ሲጓዙ ደጀ ሰላምን አገኙ። ስስትም ማረፊያዬ እዚህ ነው ብሎ ቀረ። አሉ ግን ማረፊያ አጥቶ ከአንዱ አፍ ወደ አንዱ አፍ ሲንከራተት ይኖራል።

አሉ በጠቢባን ዘንድ የሚጠረጠር፣ በአላዋቂዎች ዘንድ የሚታመን ነው። አሉ በሰው ዓለም የከበረ፣ በእግዚአብሔር ፊት የረከሰ ነው። አሉ ረቂቅ ሳለ ግዙፉን የሚገድ፣ ፍጻሜ የሌለው ጅምር ነው። አሉ ጎሊናን የሚያረክስ፣ የተቀበሉትን ለመንፈሳዊ ሞት የሚያበቃ ነው። አሉ ጠቢባን በጆሮ የሚሰሙት አላዋቂዎች በልብ የሚያደምጡት ነው። አሉ ገለባው የሚያምር ውስጡ ፍሬ የሌለው ነው። አሉ በተግሳጽ ሰይፍ የሚወድቅ፣ ትዕግሥተኞችን የማይረታ ነው።

የአሉ ጨዋታ ሊኖር ይችላል፣ የአሉ እውነት ግን የለም። እውነተኛ እውነት ራስን ማየት ነውና። የአሉ አድማ ይኖራል፣ የአሉ ጎብረት ግን የለም። እውነተኛ ጎብረት መሠረቱ ሌላውን መጥላት ሳይሆን እርስ በርስ መዋደድ ነውና። የአሉ ክስ ሊኖር ይችላል። የአሉ ወቀሳ ግን የለም። ክስ ለባዕድ፣ ወቀሳ ግን ለባለቤቱ ነውና። የአሉ ነቀፋ ሊኖር ይችላል፣ የአሉ መስተዋት ግን የለም። እውነተኛ ዕይታ ራስን ማየት ነውና። በአሉ ወሬ ይራገባል፣ ፍርድ ግን አይፀናም። በአሉ ሐሜተኞች ሥራ ይበዛባቸዋል፣ በአሉ ግን ዙፋን አይመሠረትም። አሉ የቀላሎች ማስረጃ ነው፣ አስተዋዮችን አይመሠረትም። አሉ የቀላሎች ማስረጃ ነው፣ አስተዋዮችን ግን የማይገዛ የነፋስ ጭነት ነው። አሉ አየር እንደ ተሞላ ፊኛ የሚንሳሰል ነው፣ ሲጨብጡት ግን የሚሟሽሽ ነው። አሉ እውነቱ እስኪመጣ ሰው ሠራሹ ነው። እውነቱ ሲመጣ የሚሻር ጊዜያዊ ኃይል ነው። አሉ እውነትን እስከ ጊዜው የሚያስክድ ነው፣ ለዘላለም ግን የሚገሰጽ ነው። አሉ ለአፍ እንጂ ለመጽሐፍ የማይበቃ ነው። አሉን በጽሑፍ ማስፈር አስፈሪ ነው። አሉ ተማምነው የሚያወሩት፣ ተማምነው ግን የማይጽፉት ነው። አሉ ቀሎ የሚያቀል፣ ትልልቅ መሳዮችን ለትዝብት የሚጥል ነው። ከማየት ይልቅ በመስማት ለሚኖረው ለዛሬ ትውልድ፣ ለወሬ ጥመኞች አሉ ንጉሥ ነው። በእግዚአብሔር ፊት ግን አፀያፊ ነው።

አሉ ለሐሜተኞች ቅዱስ ሐሜት መሳይ፣ ለጋዜጠኞች የወሬ ናፍቆትን የሚጨምር ነው። አሉ ለማያስተውሉ ነገሥታት የጠብ ርእስ፣ መንፈስ ቅዱስ ለማይመራቸው የሃይማኖት መሪዎች መነሻና መድረሻ፣ ፍርድን ከፍርድ አደባባይ ማንሻ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛ ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ብዙ የሚነገርላቸው የተለየ ጠባይ ነበራቸው። አንድ ቀን አጋፋሪውን፡- «እገሌና እገሌ ሁለት ቀን በግብጣው ላይ ለምን አልተገኙም?» ብለው ከግብር ላይ የቀሩትን ሰዎች ጠየቁ። አጋፋሪውም፡- «እኔ እንዳይገኙ ከልክያቸው ነው» አለ። «ለምን ከለከልካቸው?» ቢሉት፡- «እነርሱ የእርስዎን ስም እያጠፉ እንዲህ ናቸው፣ ወልደዋል... እያሉ ስምዎን ሲያጠፉ ከለከልኳቸው» አለ። አቡነ ቴዎፍሎስም፡- «ይኸው አንተ በግልፁ እየሰደብከኝ አይደለም ወይ? እንዳትከለክላቸው» ብለው አዘዙት ይባላል። አዎ እነዚያ ሰዎች ቢያፍሩ በሩቁ ተናገሩ፣ እርሱ ግን በቅርብ እያወራው ነው። «ያማኝ አከበረኝ፣ የነገረኝ ናቀኝ» እንዲሉ።

ወሬኞችን የሚያነግሣቸው ጆሮ ነው። መልሰን ስንሰድባቸው ደስታቸው ወደር የለውም። እንዲህ አሉኝ እያልን ስንናገር ራሳችንን እንሰድባለን። «ባለጌን አንድ ጊዜ ሰደበው፣ እንዲህ ብሎ ሰደበኝ እያለ ሲያወራ ራሱን ሲሰድብ ይኖራል» ይባላል።

አንድ ሰባኪ ሲናገር የሰማሁትን ልንገራችሁ፡- ታሪኩ የተፈጸመው በፈረንጅ አገር ነው። ቁሱ ከሚያገለግልበት ቤተ ክርስቲያን ተዛውሮ ወደ ሌላ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል። እርሱ እንዲመጣ ግፊት ያደረጉና በመምጣቱ ደስ ያላቸው ወዳጆቹ ብዙ ናቸው። በአዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን የነበሩት ወዳጆቹ ስለ ቤተ ክርስቲያኗ እንቅስቃሴ በደንብ ገለፃ ካደረጉለትና ሁሉም ነገር በመልካም እየቀጠለ መሆኑን ከነገሩት በኋላ አንድ ልባቸውን የሚያስጨንቅ ጉዳይ እንዳለ አጫወቱት። ያ ልባቸውን ያስጨነቀው ጉዳይ አንዲት በጥባጭ ሴት በቤተ ክርስቲያኑ መኖሯ ነው። ይህች ሴት አገልጋዮችን ሁሉ ጎሊናን በሚነካ ንግግር ለመስበር የምትኖር ናት። እርስዋን ከታገሠ አገልግሎቱ መልካም እንደሚሆን ነገሩት። እርሱም፡- «ቀላል ነው፣ አትጨነቁ» ብሎ አረጋጋቸው። ከሕዝቡ ጋር በሚተዋወቅበትና የመጀመሪያውን ቀን ትምህርት በሰጠበት ለንበት ያችም ሴት ነበረች። ከጉባዔው በኋላ በትምህርቱ ደስ የተሰኘ ው ሕዝብ፡- «እንኳን ደህና መጣህልን» እያለ ሰላምታ ሲሰጠው ያችም ሴት ጠጋ ብላ ወደ ጆሮው በመቅረብ፡- «እንደዚህ ያለ አስቀያሚ ትምህርት ሰምቼ አላውቅም፣ ራስህን አሻሽል» አለችው።

እርሱም ያች ሴት መሆኗን አወቀ። እንዳልሰማ በመምሰል፦ «በጣም ደህና ነኝ፣ አንቺ እንደምን አለሽ?» ብሎ ሳማት። እርስዋም፦ «ባይሰማኝ ነው፣ ሳምንት እነግረዋለሁ» ብላ ሄደች። በሳምንቱ ጉባዔው አልቆ ሕዝቡን ሲያሰናብት ያች ሴት እንደ ልማዷ ወደ ጆሮው ቀረብ ብላ፦ «የዛሬው ትምህርት ትዕግሥት የሚያስጨርስ ነው፣ ምንም ደስ አይልም» አለችው። እርሱም ያልሰማ በመምሰል፦ «ልክ ነሽ ሰማዩ ጠቍሯል ዝናቡ ሳይመጣ በቶሎ መሄድ አለብን» አላት። እርስዋም በጣም ተበሳጭታ፦ «ለካ የምዳረቀው ከማይሰማ ደንቆሮ ጋር ነው» ብላ ነቀፋዋን አቆመች። ይህ ሰው ነቃፊዎችን የምናበረታታቸው በመስማት መሆኑን ተረድቷል። ድል መንሻቸው አለመስማት ብቻ ነው። ይህችን ሴት ብዙዎች ስለሰሟት አዝነውባት፣ ተሰደውባት ይሆናል። እርሷም ስለሰሟት ነቀፋዋን አላቆመችም። የሚሰማት ስታጣ ግን ታረመች።

የሚሠሩት ሥራ የሌላቸው ሰዎች የሚሠሩ ሰዎችን መንቀፍ ሥራቸው ያደርጉታል። ሌቦች ሥራዬ ብለው ጠዋት እንደሚወጡ፣ ለማኞች ሥራዬ ብለው በጠዋት በወንበራቸው እንደሚሰየሙ ነቃፊዎችም ሥራዬ ብለው ሲያነፈንፉ ይውላሉ። በሥነ ልቡናው ዓለም እንደሚታመነው ሐሜት የበታችነት መንፈስ የሚወልደው ነው። ሰዎች የበለጣቸው የሚመስላቸውን ሰው በሐሜት ዝቅ አድርገው ሲያጣጥሉት ከራሳቸው ጋር እኩል የሆነ ስለሚመስላቸው ዕረፍት ይሰማቸዋል፦ «እኛም አንተኛ ሰውም አናስተኛ» እንደሚባለው «እኛም አንሠራ ሰውም አናሠራ» የሚሉ ብዙ አዝማሪዎች አሉ። የተፈጠሩት ለወሬ እስኪመስል ካላወሩ ነርቫቸው የማይነቃቃላቸው የሐሜት ዋንጫ አሟሪዎች የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉ። ሐሜታቸውን ቅዱስ ለማድረግ ለሃይማኖት የቀኑ፣ ለእውነትና ለፍትሕ የተቆረቆሩ ይመስላሉ፣ እንዲህም ያወራሉ። በጸሎት የሚፀናውን የእግዚአብሔር ቤት በስለላ ለመጠበቅ የተነሡ፣ የመሥራትን እውነት እየሸሹ የማውራት እውነትን የሚፈልጉ፣ እነ እገሌ ገዳይ ናቸው እያሉ የሰውን ጎሊና የሚገድሉ በዙሪያችን አሉ። እነዚህን ሰዎች ያነገሣቸው ጆሮ ነው። ጆሮ የተነፈጉ ቀን ይከስማሉ።

በራእይ ውስጥ ከሚነሡ ውጫዊ እንቅፋቶች አንዱ ነቀፋ ነው። ጥሩውን ጥሩ ለማለት ያልታደሉ፣ ክፉውን ክፉ ለማለት ነቅተው የሚጠብቁ፣ የምስጋና ዱዳዎች የእርግማን አፈኞች በየዘመናቱ ነበሩ፣ ዛሬም አሉ። እነርሱ ስለማይሠሩ አይሳሳቱም፣ የሚሠሩ ግን ይሳሳታሉና ትንሹን ስህተት እያነሉ ተቆርቋሪ፣ ደራሲ፣ ሐቀኛ ይመስላሉ። እነዚህ ሰዎች አሉ ግን እየኖሩ አይደለም። በዚህ ዓለም ላይ ብዙ ቋጥኞች አሉ፣ ነገር ግን እየኖሩ

አይደለም። ቋጥኞች ባይኖሩም እየተንከባለሉ የሚኖሩ ሰዎችን ይገድላሉ። ለመኖር ብቃት ያጡ ለመግደል ግን ብቁ የሆኑ ሰዎች ስህተት ቢያጡም እንኳ በእውነቱ የሚከስሱ ናቸው። ለነገረኛ ሰው እንደምን አደሩ ነገር ነው። «ባድር ባላድር ምን አገባሽ?» ብለው የስድብን አፍ የሚያላቅቁበት ነው። ለእነዚህ ሰዎችም መልካም ነገርም ስህተት ነው። ባለ ራእዩን ሌባ፣ ትሑቱን አስመሳይ፣ ጎበዙን አምባገነን፣ ወሬ የማይቀበለውን ዘረኛ፣ አድማ የማይወደውን ፖለቲከኛ ... እያሉ ስም ማክፋት ያውቁበታል። ሕልውናቸው የተመሠረተው ግን በጆሮ ላይ ብቻ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጲላጦስ አደባባይ ስለ እውነቱ ተከሰሰ። ስለ ጥፋቱ ሳይሆን ስለ ሐቁ ተወነጀለ። የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ይላል በማለት በሊቀ ካህናቱ ፊት ተከሰሰ። በርግጥም የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ። ወልደ እግዚአብሔር ተብሎ መመስገን ሲገባው በመመስገኛው ተከሰሰ። ባለ ራእዮችም እንደ ጌታቸው ሊደነቁበት በሚገባው ነገር ስማቸው ይጠፋል። ሊመሰገኑበት በሚገባው ነገር ተከሰሰው በችሎት ፊት ይቆማሉ። ነቀፋን ሁሉ የናቀ ድል ነሥቶ በዙፋን የነገሠ ጌታን ስለምናመልክ ደስ ሊለን ይገባል።

ጌታችን ተቃዋሚዎቹ ለሊቀ ካህናቱ ሃይማኖታዊ ክስ፣ ለአገረ ገዥው ፖለቲካዊ ክስ አቀረቡበት። ተቃዋሚዎች ሁለት ዓይነት ሰይፍ ቢኖራቸውም ግባቸው ግን አንድ ብቻ ነው። እርሱም መግደል ነው። የማረም እቅድ የላቸውም። ዕቅዳቸው የመደምሰስ ብቻ ነው። ጥፋትን ሳይሆን አጥፊውን ማጥፋት፣ መልካም ነገርን ከመልካሙ ሰው ጋር መደምሰስ ዓላማቸው ነው። አጥፊን ሲገድሉ ጥፋት ግን እንድትኖር ይፈልጋሉ። መልካምን ግን ከነወዳጇ ህልውናዋን አይቀበሉም። የመልካም መኖር የመልካሞችም ህልውና እነርሱን የሚያሳጣቸው ይመስላቸዋል። ከጎሊና ወቀሳ ለመዳን መልካሞችን መንቀል የዘወትር ተግባራቸው ነው። ማዳን ብዙ ዋጋ ያስከፍላል፣ መግደል ግን ከሞት ውስጥ ከተቀበረም አስተሳሰብ ይወጣል። የሕይወትን ዋጋ የሚያውቅ የሚኖር ሰው ብቻ ነው። ጌታችን የማዳንን ራእይ የሥላሴንም እቅድ ይዞ ወደ ዓለም ሲመጣ ገና ከጠዋቱ ብዙ ተግዳሮት ገጥሞታል። *«የሚሰውጥ ፍቅር»* በሚለው መጽሐፍ ላይ ጠቃሚ ነገር ተጠቅሷል። ይህንንም አሳብ ያብራራልናል፦

«አንተ ሥራህን ሥራ! ሄሮድስ ገና በሕጻንነትህ ሊገድልህ ይነሣል፣ የዜግነት ክብርህም ሊገፈፍ ይችላል፣ ምንም የሌለህ ድሃ ልትሆን ወዳጆችህም የተከበሩት ሳይሆን የተናቁት ሰዎች

ሊሆኑ ይችላሉ፣ የገዛ ዘመዶችህ ሳይቀሩ ያለ መራራት ያቆስሉሃል፣ ለብዙዎች ሕሊና ሙግት ትሆናለህ፣ እንዳይርቁህ መልካም ሰው ነህ፣ እንዳይቀርቡህ የተነቀፍህ ነህ፣ አሳብህን ከሚስተሉ የሚያደንቁልህ ነገር ግን የማያረኩህ ብዙ ሰዎችን ልትሰበስብ ትችላለህ። የፈተና ነፋስ የሚበትናቸው ብዙ ገለባ ባልንጀሮች ይከቡሃል። የተማሩትም በሌሊት ይመጣሉ እንጂ በቀን ካንተ ጋር መታየት አይፈልጉም። በምትከሰስበት ሸንጐ አንዳንድ ደጋፊዎችን ታገኛለህ፣ ግን በቆራጥነት ስለ አንተ መከራከርን ይፈራሉ።

ያጐረስከው ይነክስሃል፣ አብሮህ የኖረው ይጠቁምብሃል ሥፍራህን የሚያውቀው እርሱ ነውና። ሆሳዕና ያለህ ሕዝብ ከአምስት ቀን በኋላ ይሰቀል ይልሃል። ሕዝብ አያስተውልምና። በዚህ ሁሉ መገለል ውስጥ እግዚአብሔር የተወህ ይመስልሃል፣ በፍርሃትም ትጸልያለህ፣ የጌቴሴማኒ ጫካ የሌሊቱ ግርማ በድንጋጤ ይሞላሃል። ረዳት በምትፈልግበት ሰዓት በሩቅ ፋናና መብራት ይታይሃል፣ ሲቀርብም የምታውቀው ይሁዳ ነው፣ ሲስመህ ትረካለህ ግን ከኋላው ጦር አስከትቶ መጥቷል። ይህ ሁሉ ለእኔ? ምን በድዬ? ትላለህ ግን ይይዙሃል።

ሸንጐው የድሃን ጩኸት ለመስማት በቀን አይገኝም፣ አንተ አንድ ቀን እንዳትኖር ግን በሌሊት ይሰበሰባል። የእግዚአብሔር ተወካይ ሊቀ ካህናቱም ይሰድብሃል፣ ፊራጁ ጲላጦስም ፍርድ ያጣምምብሃል። ተጣልተው የሚኖሩ ጲላጦስና ሄሮድስም በአንተ ሞት ይታረቃሉ። መስቀል አሸክመው ይነዱሃል። ጴጥሮስ ሲክድህ ዮሐንስ በሩቅ ይከተልሃል፣ ምንነትህን የማያውቀው የቀሬናው ሰው ግን መስቀሉን ያግዝሃል። <u>በክርስቶስ እንደሆነው ባንተም ይሆናል። ለአንተና ለጌታህ ክፍት ቦታ በረትና መስቀል ብቻ ነው</u>። ቢሆንም ሥራህን ሥራ እግዚአብሔር ያስነሣሃል።»
/የሚለውጥ ፍቅር፣ 1997 ዓ.ም. ገጽ 31-32/

ጌታችን እንኳ በዚህ ዓለም ሲኖር ወዳጆችን ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚዎችን፣ ተከታዮችን ብቻ ሳይሆን ከሳሾችን አስተናግዷል። ሁሉንም በትዕግሥትና በፍቅር ተቀብሏል። ታዲያ እኛ ከእርሱ በምን እንበልጣለን? ወዳጅ ብቻ ይኑረኝ፣ ሁሉስ ያመስግነኝ ለማለት እንዴት እንደፍራለን? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ነቀፋዎችን አስተናግዷል። ለተነሣሀያን/ንስሐ ለሚገቡ/ ጆሮውን ሲሰጥ ነቃፊዎችን ግን አላዳመጣቸውም። የእግዚአብሔር ልጅነቱን አስክደዋል። የሥልጣኑና የተአምራቱ ምንጭ ከአጋንንት አለቃ መሆኑን ተናግረዋል። የሃይማኖት መሪዎች የቅንዓት አገልጋይ

ሆነው አውግዘውታል። በመጨረሻም ለሞት አሳልፈው ሰጥተውታል። እርሱ ግን ከሥላሴ መንግሥት የወጣችውን የማዳን ተልእኮ ለመፈጸም ተጋ። የሰማዩን ተልእኮ በምድር ተግዳሮት ሊያቆመው አልፈቀደም። ከጠላት ተቃውሞ ይልቅ የሰማይ ተልእኮን ችላ ማለት የበለጠ ስህተት መሆኑን ያውቃል። ጌታችን ሌሎችን በማዳን ሥራ ለተጠመዱ አርአያነቱ ፍጹም ነው። ምክሩም በሚያታግሉ ቀኖች ጉልበት ነው። በተመረቀ መንገድ በነጻነት እንደሚፈስስ መንገደኛ ጌታችን በቀደመበት፣ የንጉሥ ፈታውራሪ በወጣበት ፍኖተ ራእይ በደስታ እንጓዛለን። ከሚቃወሙን የሚያድነን፣ ከሚነቅፉን የሚቀበለን ጌታ ይበልጣል። የሰው አሳብ በሥላሴ ፈቃድ ትገደባለች፣ የሥላሴ ፈቃድ ግን በሰው ፈቃድ አትገደብም።

የራእይ እንቅፋት ከውስጥና ከውጭ ነው። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ከውስጥና ከውጭ ነበሩ። ከክርስቶስ የሥጋ ዘመን ቆስጠንጢኖስ የሃይማኖትን ነጻነት እስካወጀበት እስከ 313 ዓ.ም. ድረስ ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን በሰይፍ ስለት፣ በእሳት ወላፈን፣ በብርቱ መከራ አጥታለች። እነዚህ የቤተ ክርስቲያን የውጭ ጠላቶች ብዙ አማንያንን ቢፈጁም የቤተ ክርስቲያንን አንድነትና ቅድስና ግን ጠብቀዋል። ጠላት ያለበት መንጋ አንድ ይሆናልና። መዘናጋትም ስለሌለ ቅድስና በጎብረት ውስጥ ያብባል። ቤተ ክርስቲያንን የጎዷት ግን የውስጥ ጠላቶቿ መናፍቃን ናቸው። እነዚህ ለጥቅማቸው ያደሩና በሹመት ፍቅር የሰከሩ የቤተ ክርስቲያን መምህራንና ጳጳላት ከዕረፍት ማግሥት ጀምረው ቤተ ክርስቲያንን ከፋፍለዋታል። አረመኔ ነገሥታት ከጎዷት ይልቅ እነዚህ የውስጥ ጠላቶች የጎዷት ጉዳት ብርቱ ነው።

በራእይ ውስጥም የውስጥና የውጭ እንቅፋቶች አሉ። የውስጥ እንቅፋት ያልነው ከራሳችንና ከስሜታችን የሚነሣው ከንቱ ነገር ሲሆን ውጫዊ እንቅፋቱ ግን በርቀት ከቆሙ የራእይ ባላጋሮች፣ ለጥቅማቸው ካደሩ ራእዩን ለጊዜው ከተጋሩ ሰዎች የሚነሣ እንቅፋት ነው። ከውጫዊ እንቅፋት ይልቅ የውስጥ እንቅፋት ከራሳችን የሚነሣው ወደብ ሰራእይ ትልቅ መሰናክል ነው። ዙሪያው ሁሉ ጦርነት ቢሆን ውስጣችን ግን ከጸና የራእይን ግብ ማሟላት ይቻላል። ውስጣችን ተፍረክርኮ ግን ዙሪያው ምቹ ቢሆንም ራእይ አይሟላም። የራእይ ውጫዊ እንቅፋቶች ብዙ ቢሆኑም የተወሰኑትን ግን ለማየት እንሞክራለን።

ነቀፋ

ተናግረን እስክንፈጽም፣ ገልጸን እስክንጨርስ እንኳ መታገሥ የማይችሉ ነቃፊዎች አሉ። የቃላችንን ጫፍ ይዘው ለመሮጥ የሚፈልጉ፣ ርእስ ካገኙ አብራርተው ማክፋፋት የሚችሉ፣ ብርሃኑን ጨለማ ጨለማውን ብርሃን በማለት ሚዛንን የሚጥሉ፣ ወተቱን አጥቁሮ ማሩን አምርሮ መናገር የሚያውቁበት ብዙ ነቃፊዎች በራእይ ፊት አሉ። ጌታችን፡- «*እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ*» (ሉቃ. 10÷3) ያለው ቃል አስደናቂ ነው። ተኩላዎች ሲያልቁ እልካችኋለሁ አላለም። በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ ብሏል። ነቃፊዎች በየትኛውም ዘመን ነበሩ። አወዳደቃቸው ግን የኋሊት ነው። ገጣሚው የአፍ ኃይል ያላቸውን ነቃፊዎች፣ የሥልጣን ኃይል አግኝተው የሚገድሉ ተቃዋሚዎችን ሲተች እንዲህ ብሏል፡-

ሾላ ምን ያፈራል ብለው ሳይጠይቁ
ዋርካ ምን ያፈራል ብለው ሳይጠይቁ
ዋንዛ ምን ያፈራል ብለው ሳይጠይቁ
ቆርጠው ቆርጠው ጣሉት እነጣዕም አያውቁ

ነቃፊዎች ፍሬውን መጠበቅ ተሰኗቸው ስንቱን ያማረ ቅጠል አረገፉት! ለአገር፣ ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ፍሬ የያዙትን ስንት ጎበዞችን አጨናገፏቸው። በማጎፀን በር ላይ እንደ ተቀመጠ ገና ሲወለዱ እንደሚያንቅ ሾተላይ ለአገር ለቤተ ክርስቲያን ገና ሲወለዱ ስንቶች ጨቅላዎች ተገደሉ። አገሩ ከጥንት ጀምሮ አዝማሪና ባንዳ የሚሸለምበት ለምድሩ ዋጋ የከፈለው ለማዕት የሚወገዝበት መሆኑ ያሳዝናል። ዘመን ተሻግሮም ይህ ጠባይ ዛሬም ይገዛናል። በሰላም ለመኖር አለማወቅ፣ አለማየት መልካም ነው እስኪባል ለዘመናት ጨለማ አንጋሽ ሥርዓት ተቆራኝቶናል። ጣልያን ከወጣ በኋላ ለአገራቸው ብዙ መሥዋዕትነት የከፈሉ አርበኞች የሚገባቸውን ክብርና ወሮታ አላገኙም ነበር። ከስደት የተመለሱት ንጉሥም ይህንን ማድረግ ስላልቻሉ ቅሬታው በዛ። ዮፍታሔ ንጉሤም ይህንን ሰቆቃ እንዲህ በማለት ገለፀው፡-

አገሬ ኢትዮጵያ ምኝ ነሽ ተላላ
የምተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ

ክብር ለክቡራን የሚሰጠው ከክብር ጌታ ከእግዚአብሔር ብቻ ነው። የሰው ዓለም ክብር ሰራቂ ነው። የተከበረውን ከተዋረደው የማይለይ፣ የእውነትን ሚዛን የጣለ ነው። ሌባው ቀማኛው በአገር መንደሩ ተፈርቶ፣ ጠንቋይ አስማተኛው በየደብሩ ተከብሮ ይኖራል። ጨዋው እየተናቀ ምሁሩ መናፍቅ እየተባለ ይኖራል። እውነተኛ ሥልጣኔ ሰውን በሚገባው ስፍራ ላይ የሚያስቀምጥና የሚያደላድል ነው። ሌቦች በገንዘባቸው እንደ መኪንንት እጅ ከተነሡ፣ አላዋቂዎች በጮሌነት አማኝ ከተባሉ እውነተኛ ሰላም ሊኖር አይችልም። እውነተኛ ሰላም የሚነጋው ከእውነተኛ ፍትሕ ነውና።

ምሁሩና መሃይሙ ተጣልተው፣ መሃይሙ የተማረውን ሰው፡- «አንተ መሃይም» እያለ ይሰድበዋል። ጠቡ እየከረረ ሳለ አለቃ ደረሱና ለመዳኘት ጥግ ይዘው ተቀመጡ። አንድ ሰውም በጎዳናው ሲያልፍ አለቃን አይቶ፡- «እንደምን አሉ አለቃ፣ ምን እያደረጉ ነው?» ቢላቸው፡- «ስድብ ቦታ ተሰዋውጦ እቦታ እቦታው እየመለስኩ ነው» አሉ ይባላል።

መሃይሙ ራሱን እንደ ምሁር ቆጥሮ፣ «መሃይም» እያለ ይሳደባል። ምሁሩም ዳኛ አጥቶ ለሰዳቢዎቹ የሚገባውን ስም ተሸክሟል። ዛሬም እንዲሁ ነው። አማኒው ከሃዲ፣ ምሁሩ መናፍቅ እየተባለ ይወገዛል። አላዋቂዎች በመጽሐፈ ባልቴት አንጋሽነት በሕዝቡ አናት ላይ ተቀምጠዋል። ባሕልና ሃይማኖትን፣ ወንጌልና አሪትን የማይለዩ አማንያን፣ አዋቂዎች ደግሞ ከሃድያን ተብለዋል። ዛሬም ስድብ ቦታ ተሰዋውጧል። እቦታ እቦታው የሚመልስ ዳኛ ብዙዎች ናፍቀዋል። «የመሸ በከንቱ» ስብከት ሰባኪዎች፣ የወዮታ አዋጅ ነጋሪዎች ባጣበቡት አደባባይ እውነተኞች ስፍራ አጥተው በየቤታቸው ተቀምጠዋል። እነርሱ ካላሰቁ አናርፍም የሚሉት ነቃፊዎች ከአደባባይ ብቻ ሳይሆን ከቤታቸው ሊነቅሏቸው ከተት ሲያውጁ ይውላሉ። ሰው በዜግነቱ እንኳ መኖር እንደሚችል የዘነጉ፣ እንደ ገደል ማሚቱ የገዛ ድንቁርናቸውን ሲሰሙ የሚውሉ ስንት የምድር አበሳዎችን አገሬ ተሸክማለች።

ዛሬ የምንነቅፋቸውን ትላንት አወድሰናቸዋል። ምስጋናና ርግማናችን የጊዜ ክፍተት እያጣ ተቀላቅሎብናል። የሰው ልጅ ከመጀመሪያው ፍቅሩ የኋላ ጥላቻው መጠንከሩ ያሳዝናል። «ሆሳዕና፣ ይንገሥ፣ ይገባዋል» ባለ አፉ «ይሰቀል» ሲል አይሰቀውም። ጳውሎስ ግዙፋኛ ሆኖ ወደ ሮም ሲሄድ በአንድ ስፍራ ለማደር ዐረፈ። ወቅቱ ብርድ ስለ ነበረ እሳት አንድደው መሞቅ ነበረባቸው። በድንገትም እሳቱ ሲሞቃት እፉኝቷ ከእሳቱ ውስጥ ወጥታ ጳውሎስን ነደፈችው። ሰዎቹም ባዩ ጊዜ፡- «*ይህ ሰው በርግጥ ነፍሰ ገዳይ ነው። ከባሕርም ሰንኳ በደህና ቢወጣ የእግዚአብሔር ፍርድ በሕይወት ይኖር ዘንድ አልተወውም*» አሉ። ጳውሎስ ግን እባቢቱን ከእጁ አራገፋት። አንዳች አልጎዳችውም። ያብጣል፣ አሁን

ሞቶ ይወድቃል ብለው ሲጠብቁ ምንም ለውጥ አላዩም። በዚህ ጊዜ፦ «*ይህስ አምላክ ነው*» አሉ (የሐዋ.ሥራ 28÷1-6)። በአንድ ጊዜ ከነፍሰ ገዳይነት ወደ አምላክነት አደረሱት።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እባቡንና ጊንጡን የመርገጥ ሥልጣን ሲሰጥ፦ «*ክሰዎች ተጠበቁ*» ብሏል (ማቴ. 10÷17)። ብቻውን የሆነ ሰይጣን ስመ እግዚአብሔር ሲጠሩበት ይሄዳል። በሰው ላይ ያደረ ሰይጣን ግን በቀላሉ አይሄድም። የሰዎች ምስጋናቸውም ሆነ ርግማናቸው ሊያስደንቀንና ሊያስደነግጠን አይገባም። ሁለቱንም በፍጹም ጥንቃቄ ማየት ይገባናል። ብዙዎች ትልቅ ራእያቸውን የጣሉት፣ ከሰልፉ የወጡት ከማይጠብቋቸው ሰዎች በደረሰባቸው ነቀፋ ምክንያት ነው።

የዚህ ዓለም ሰው ሲነጋ እንደ ባንዲራ ይሰቅላል፣ ሲመሽ ደግሞ ያወርዳል። ፍቅሩ ቅጥ እንደሌለው ጥላቻውም ቅጥ የለውም። ሰዎች ብዙዎች ከወደዱን ይወዱናል፣ ብዙዎች ከጠሉን ይጠሉናል። የዓለም ፍቅር በድምፅ ብልጫ ነው። ስለዚህ ሰዎች ሲወዱንም ባለማወቅ እንደሆነ ሁሉ ሲጠሉንም ባለ ማወቅ ነው። ዓለም ያመሰገነችውን ሰው መልሳ አስክትረግም እንቅልፍ አይዛትም። ከምስጋና ቀጥሎ ርግማን ይመጣልና። መፍራት ያለብን ሰዎች ስለ እኛ መልካም ሲናገሩ ነው። ዓለም ለሐሰት ስለምታደላ የምታመሰግነው ሐሰተኞችን ነው። ለክርስቶስ እንኳ ስፍራ ካልነበራት ዓለም ስፍራ መጠበቅ ሞኝነት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፦ «*ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ፥ ወዮላችሁ አባቶቻቸሁ ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲህ ያደርጉ ነበርና*» ብሏል (ሉቃ. 6÷26)።

በዕድሜአችን እንዳየነው ያመሰገነን ሕዝብ ሰድቦ እስኪጨርስ ወረፋው ረዝሞብን ነበር። የሚያውቁን ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ገበታችንን የበሉ፣ የቅርብ የምንላቸው፣ ስስ ብልታችንን የሚያውቁ ብዙ አቍስለውናል። እነርሱ ካደረሱብን መከራ ይልቅ የእኛ መደነቅ ትልቅ መከራ ሆኖብን እንደ ነበር እናስታውሳለን። ይህች አስመሳይ ዓለም የሞቱትን እውነተኞች ስታዘክር ያሉትን ጻድቃን ደግሞ ትገድላለች።

የበረዝኞቹ ተረት አለ፦ «ግመሉ ይሄዳል፣ ውሻው ይጮኻል!» ግመሉ መሄድ ሥራው ነው፣ ውሻውም መጮህ ሥራው ነው። ግመሉ ከውሻው ድምፅ የሚርቀው በሄደ ጊዜ ነው። ሲቆም ግን ይበልጥ ይሰማዋል። እኛም እንሄዳለን፣ ነቃፊዎቹም ይጮኻሉ። የተፈጠሩት ለመጮህ መሰሏቸው ይጮኻሉ። ስንቆም

እንሰማቸዋለን፣ ስንንዝ ግን ድምፃቸው እየሰለለ ይመጣል። መጮህ ሥራቸው ስለሆነ ብንቆምም ብንሄድም ይጮኻሉ። ብንሠራም ብናጠፋም ከመጮህ ወደ ኋላ አይሉም። እነርሱም ሥራቸውን ይሥሩ እኛም ልንሠራ ይገባናል።

በራእይ ውስጥ ብዙ ነቃፊዎችን እናስተናግዳለን። የምንሥራውን ካወቅን ግን አንዳች እንደናገርም። ሰዎች የሚነቅፉን ሥራችን ስህተት ሆኖ ሳይሆን እነርሱ ሊሠሩት የሚገባቸውን ሥራ በመሥራታችን በቅንዓት ተነሣሥተው ይሆናል። የሞቱት ሰዎችን ማንም አይወቅሳቸውምና ሰዎች የሚያነሡን ከሆነ በሕይወት አለን ማለት ነው። ሰዎች ስለ እኛ ሁልጊዜ አያወሩም። ስለምንሰለቻቸው ተረኛ ሰው እስኪመጣ ድረስ ያነሡናል፣ ከዚያም ይተዉናል። በእውነት ለጊዜያዊ ነቀፋ ዘላቂውን ዓላማ መተው ሞኝነት ነው።

ነቀፋ ከሰዎች የሚሰነዘር ገንቢ ያልሆነ ትችት ነው። እነርሱ የሚናገሩትን ነቀፋ መካሪዎቻችን ሊናገሩት ቢችሉም የነቃፊዎች ዓላማ ግን እኛን ማሳጣት እንጂ መልካምነታችንን መፈለግ አይደለምና ነቀፋ ኃጢአት ነው። የነቃፊዎች ነቀፋ ከእግዚአብሔር መንግሥት ሊያስወጣን አይችልም። የነቃፊዎች ዓላማ ከሰው ጎሊና እኛን ስፍራ ማሳጣት ቢሆንም ባለ ራእይ ግን የሚጨነቀው ከእግዚአብሔር ስፍራ ላለ ማጣት ነው።

ነቀፋ ለነቃፊዎች መልካም ባይሆንም ለብልህ ሰው ግን መልካም ትምህርት አለው። በተራራ ላይ ያለች መብራት ሁሉን ባታይም፣ ሁሉ ግን ያያታልና በዕይታ ውስጥ መሆናችንን ነቀፋው ያስረዳናል። ስለዚህ ጥንቃቄን እንወስዳለን። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፦ «*ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል?*» በማለት ጠይቋል (ማቴ. 16÷13)። ሰዎች የሚሉትን ለመስማት ድፍረት ነበረው። ሰዎች በእኛ ላይ ምንም እንዳያወሩ የማድረግ ሥልጣን የለንምና የምንባለውን መስማትና ስህተቱን ማረም ተገቢ ነው። የአገራችን የጥንት ነገሥታት እረኛና አዝማሪ ምን አለ? እያሉ ይጠይቁ ነበር። ራሳቸውን ከእረኛና ከአዝማሪ ለማግኘት መፈለጋቸው የሚገርም ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጲላጦስ አደባባይ ከሳሾቹ የሚናገሩበት በደል ቢያጡ፦ «*የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ይላል*» በማለት ከሰሱት። በርግጥም እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ክርስቲያን እንደ መምህሩ መከሰስ ያለበት ስለ እውነት ነው። በስንፍና፣ በሌብነት፣ በዝሙት መከሰስ የለበትም። መከሰስ የሚገባው እንደ ዮሴፍ ከኃጢአት ጋር አልተባበርም በማለት ነው

(ዘፍ. 39)። ነቃፊዎችና ከሳሾች ከስሰውን የሚያደርሱን በጌታ ፊት በመሆኑ ደስ ሊለን ይገባል (ዮሐ. 8÷1-11)። አንዳንድ ጊዜ ስህተታችንን የተናገሩ እየመሰላቸው ጽድቃችንን ሊያወሩት ይችላሉ። «የሚገርመው ደግሞ ፍቅራቸው ነው፣ የሰው ገንዘብ አይበሉም» እያሉ ሊከሱን ይችላሉ።

ጽጌረዳ ውብ ናት። ማንም ቀጥፎ እንዳይጨርሳት በእሾህ መካከል ተቀምጣለች። ነቃፊዎችም ቅድስናችንን እንድንጠብቅ በዙሪያችን እንደ እሾህ ተቀምጠዋል። ነቃፊዎቻችንን እግዚአብሔር ይጠቀምባቸዋል። ነቃፊዎች ባሉበት ተነቃፊ ራሱን ይጠብቃል።

በጎንደር መምህር ኤስድሮስ የሚባሉ ሊቅ ነበሩ። እኚህ ሊቅ ደቀ መዝሙራቸውን መምህር ወልደ ኢየሱስን ለብዙ ዘመናት ካስተማሩት በኋላ መርቀው ሊሸኙት ፈለጉ። የዚያን ጊዜ ምርቃት የዲፕሎምና የዲግሪ ወረቀት በመስጠት ሳይሆን ከተለያየ አገር የሚኖሩ ሊቃውንትን በመጥራት መርቆ መሸኘት ነበር። ልጁም በሄደበት አገር የአገሌ ተማሪ ነኝ በማለት መምህሩ ተለይተው የሚታወቁበትን ቅኔ በመጥቀስ ተቀባይነት ያገኝ ነበር። ታዲያ መምህር ኤስድሮስ ደቀ መዝሙራቸውን መምህር ወልደ ኢየሱስን ሊመርቁ ሲነሡ። «ልጄ እስከ ዛሬ ያልነገርኩህ ምሥጢር አለና አሁን ስማኝ» አሉት። እርሱ ግን፡- «ያልነገሩኝ ምሥጢር የለም ሁሉንም ነግረውኛል» አላቸው። ከየአገሩ የመጡት ሊቃውንትም «እስቲ ስማቸው አይ የልጅ ነገር» አሉት። እርሱም ተንበርክክ ለማዳመጥ ጆሮውን አሰላ። መምህር ኤስድሮስም፡- «ልጄ ሆይ! ከመሃይም አትጣላ፣ ደጋፊው ብዙ ነው ያሸንፍሃል» አሉት ይባላል።

አዋቂው አስተዋዩ ብዙ ጊዜ ስፍራ የለውም። ከፍ ብለው የማይጠየቁ፣ ዝቅ ብለው የማይጠይቁ አላዋቂዎች ግን ይከበራሉ። የግብፅ ጳጳሳት የሚያሞግሷቸውን አላዋቂዎች እየሾሙ፣ የማይሰግዱላቸውን ሊቃውንት ሲያወግዙ፣ ነገሥታቱም የሚገስጿቸውን ሊቃውንት ግዞት እየላኩ፣ አወዳሽ ደብተራን እያሳቁ ስለ ኖሩ በአገራችን መምህራን ፈርተው ደንግጠው ይኖራሉ። ሕዝቡም ሐሰተኛ መምህራንን ሲቀልብ አይደክመውም፣ ለእውነተኞቹ ግን ቍራሽ ነሥቶ ያሳድጻቸዋል። በራእያችንም ከማያስተውሱት ጋር ግጭት ሲፈጠርብን ደጋፊያቸው ብዙ ስለሆነ ስደት ይበዛብናል። ብቻ ሰዎች ጻድቅ ቢሉን ጻድቅ አንሆንም፣ ኃጥእ ስላሉንም ኃጢአተኛ አንሆንም። የምንሆነው የሆነውን ነው። ከሺህ ደጋፊ አንድ እውነት ነጻ ታወጣለች።

በአገራችን ከጥንት ጀምሮ የነበረው ባሕላችን ባዕዳንን ማክበር፣ የራሳችንን ልጆች ማዋረድ ነው። ዛሬም የአገራችን ፍሬዎች የሆኑትን አገልጋዮች፣ ደራሲዎች እያጣጣልን ባዕዳንን እናሞጋግሳለን። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡- «*ሃይማኖተ አበው ቀደምት*» በተባለው መጽሐፋቸው ግብፃውያን ጳጳሳት ያደረሱትን ጥፋትና የአገራችንን ጠባይ ሲገልጹ፡- «... ርሷም በጠባይዋ ከልጆቿ ይልቅ ባዕድ የንጀራ ልጅ የምቶድ ወረተኛ ባልቴት ስለኾነች፣ ኢትዮጵያን በየዘመኑና በየጊዜው እንደዚህ ያለ ይህን የመሰለ ልክ የሌለው ሐዘን ጥቃትና ውርደት የሰው መሣቂያነት አግኝቷታል...» ብለዋል /ገጽ 22/።

መልካም ራእይ ይዘን ስንነሣ የአገሩን ጠባይና ሊደርስብን የሚችለውን ግፊት አስቀድመን ማጤን አለብን። ሥራችንን የገዛ ወገኖቻችን ሊያናንቁት፣ ደረስንላችሁ የምንላቸው ሊደርሱብን፣ ለባዕዳን የተከፈተው በር ለእኛ ሊዘጋብን እንደሚችል ማሰብና መገመት አለብን። በሃይማኖት መሪዎች ስህተት ሃይማኖትን ጨርሶ መጥላት፣ በአገር መሪዎ ጥፋት አገርን መጥላት ተገቢ አይደለም። ሁሉንም ነገር በመጠኑ ማየት አለብን። አንድ ሰው ስለ ጎዳን መላው የሰው ዘር አድማ እንዳደረገብን ማሰብ፣ ከታች ፍርድ ቤት ፍርድ ስናጣ በሰማይ በምድር እንደተኰንን ማሰብ አይገባም። ከልጆችዋ ይልቅ ባዕድ የእንጀራ ልጆችን የምትወድ፣ ከባሕርይ ፍቅር ለወረት ፍቅር ዋጋ የምትሰጥ ብትሆንም አገራችንን መውደድ ይገባናል። የልጅ ፍቅር የባሕርይ ፍቅር፣ የባዕድ ፍቅር የወረት ፍቅር ነውና። በዚህም ከመጐዳት በቀር ጥቅም እንዳልተገኘ ታሪክም በጆሮ፣ ዓይንም በማስረጃ ይተርክልናል።

ነቃፊዎችን የምናበረታታቸው እኛው ነን። ወረኞችን ወረኛ የምናደርጋቸው ጆሮ በመስጠት ነው። የነቃፊዎች ነቀፋ ውስጣችን ገብቶ ያውከን ዘንድ መፍቀድ የለብንም። ነቃፊዎችን የምናሳድጋቸው እኛው ጆሮ በመስጠት ነው። አብዛኛው ራሱን የማያውቅ በመሆኑ እልፍ ተቃዋሚም ቢነሣ ሊያስደነግጠን አይገባም። ይልቁንም በአገራችን አዲስ የሚመስል ነገርን መቃወም ባሕል ስለሆነና ተረቱም፡- «ካለመዱት መንፈስ ቅዱስ የለመዱት ሰይጣን ይሻላል» የሚል ስለሆነ ራእያችን በአዲስነቱ ብዙ ነቀፋ ይመጣበታል። በመሠረቱ ምንም ባይለመድ ከመንፈስ ቅዱስ ሰይጣን አይመረጥም። የቆየው ሁሉ እውነት፣ አዲስ ሁሉ ሐሰት ሊሆን አይችልም። እኛ የማናውቀው ሁሉ አዲስ ነው ማለትም አይደለም። አዲስነቱ ባለማወቃችን እንጂ እውነትነቱ የጥንት ነው። እንኳን ራእያችን የጥንቱ ኢየሱስ እንኳ እንደ አዲስና እንግዳ እየታየ ነውና መደነቅ አይገባንም።

ጨለማና ብርሃን በመቀዋወም እንጂ በመስማማት ኖረው አያውቁም። ይህ አደጋ ሳይሆን ተፈጥሮአዊ ባሕርይ ነው። እንዲሁም የባለ ራእዩ ሩጫና የተቃዋሚዎቹ ተቃውሞ ተፈጥሮአዊ በመሆኑ ማስታረቅ፣ ዲፕሎማሲያዊ መፍትሔ ማግኘት አይቻልም። አዲሱ ትውልድ ግን ወደ ሰፊው መስክ ሁሉን ለማየት፣ የከበረውንም ለመምረጥ እንደሚወጣ እናምናለን። በራእያችንም ነቃፊዎች አያስፈሩንም። ከዚያ ይልቅ ሁለት ነገሮች ሊያስፈሩን ይገባል፦

1- ውዳሴ ከንቱ

2- ሳይገባቸው የሚደግሩን

ውዳሴ ከንቱ

በአንድ ወቅት በዚህ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈጸመ ታሪክ አለ። ሰንበት ተማሪዎቹ የሆሳዕናን በዓል ልዩ ለማድረግ ለቅዳሜ ገበያ ከመጡት የባላገሩ አህዮች አንዷን በሃያ ብር ተከራይተው ያስቀሯታል። እሑድ በማለዳው አይታ የማታውቀውን ግምጃ አልብሰዋት፣ አይታ የማታውቀውን ክብር ሰጥተዋታል። ከቅዳሴ በኋላም አንድ ቆንጆ ወጣት ካባ ለብሶ በአህያዋ ላይ ተቀምጦ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑን ሲዞር ምእመናኑ የእልልታ ግዴታቸውን ይወጣሉ። ሰንበት ተማሪዎቹም፦ *«ሆሳዕና በአርያም»* እያሉ ዘንባባ እያነጠፉ ዑደት ሲያደርጉ አንዱ ፈላስፋ የሆነ ደብተራ በነገሩ ተደንቆ ወደ ወጣቱ ጠጋ አለና፦ «ዛሬስ አምሮብሃል የዓርቡን መከራ ግን ትችለዋለህ ወይ?» አለው። ምክንያቱም ሆሳዕና ከተባለ ይሰቀል ማለት የሰው ተራ ነውና። እሑድ ሆሳዕና የተባለለት ጌታ ዓርብ ይሰቀል ተብሎ ሞቷልና።

የብዙ አገልጋዮች ትምክሕት ሥጋዊ ሆኗል። በጸጋ ሳይሆን በእውቀት ብቻ ለማገልገል ደፍረዋል። ለንስሐ ሳይሆን ለልብሳቸው ጥራት ይጨነቃሉ። ክርስቶስን ሳይሆን ፎቶአቸውን ለማሳየት ይጋደላሉ። የሕዝቡ ከበባ፣ የፕሮግራሙ ጥበት፣ የግብጣው ብዛት የመተንፈሻ ጊዜ አሳጥቷቸዋል። ጭብጨባውና እልልታው ልባቸውን አሸፍቷል። መልእክ ሆነው ውሰው ብቻቸውን ደግሞ ሰው ሆነው ያመሻሉ። ጊዜው ሲያልፍ ሰው ብቻ መሆናቸው ይታወቃል። መልእክ ብሎ ያመናቸው ግን እንደ ደነገጠ ይቀራል።

ለምላክን መስሎ ቴዎድሮስ
ንዑና ጉሩ ሲል አመሰ
ሰኖ መቅደላ ተጨነቀ
ሰው መሆኑ ታወቀ

ለማንም ሥጋ ለባሽ ይህ ከበባ ደስ ያሰኛል። እኔም ባገኝ አልጠላም ይሆናል። ከንቱ ልቤን ሳዳምጠው ይህን ይፈልጋል። ከንቱ ነኝና ጌታዬ ይቅር በለኝ! ብቻ እንደ ሊፍት ዘበኛ የወጣው ሰው ሲወርድ በመሬት መቀመጫዬ ሆኜ እጠብቀዋለሁ። የወጣ ሁሉ መውረዱ አይቀርምና የሥር ወዳጅ ሆኜ እኖራለሁ። በዚህ ሁሉ ግርግርና አድናቆት የኋላውን መከራ ያልተረዱ በጣም ያሳዝናሉ። *«ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር፡ ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር። ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና»* ተብሎ የተጻፈውን አላስተዋልንም (ዮሐ. 2÷24-25)። ዛሬ ሳይገባቸው ብዙዎች ይደግሩናል፣ ሳይገባቸውም ነገ ይነቅፉናል። በደጋፊዎች መተማመን በሰባራ ወንበር እንደ መደላደል ነው። ከዚያ ይልቅ የተነቀፉት፣ የተጠሉት፣ የተሰደዱት ወገኖች ወዳጅ መሆን ይሻላል። ሆሳዕና ብሎ ያከበረን ሕዝብ ይሰቀል ብሎ ይሙት በቃ ሲፈርድብን እንኳን ፈሪሀ እግዚአብሔር ይሉኝታም የለውም። በራእይ ላይ ውዳሴ ከንቱ ትልቅ ፈተና ነው። ውዳሴ ከንቱ እንደ ሰፈር ምጣድ ካንዱ ወዳንዱ ሲፋለስ ስንቱን ሞኝ ከእውነቱ ሲያፋልስ ይኖራል።

ሰባኪው ወደ መድረክ ከመውጣቱ በፊት የመርሐ ግብሩ መሪ ስለ ሰባኪው ስለተማረበት የሥነ መለኮት ኮሌጅ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ብቃቱ ብዙ ተናገረ። ሰባኪው ሲነሣ፦ «ጌታ ሆይ፣ ይህ ወንድሜ ከሆንኩት በላይ ስለ እኔ ስለ ተናገረ ይቅር በለው። እርሱ ሲናገር እኔም ልቤን ደስ፣ ደስ ይለው ነበርና እኔንም ይቅር በለኝ» ብሎ ጸለየ ይባላል።

ውዳሴ ከንቱ፦ ከሆንነው በላይ ሰዎች እኛን የሚክቡበት፣ ሁሉ ከእናንተ፣ ሁሉ በእናንተ፣ ሁሉ ለእናንተ ነው የሚሉበት፣ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ለእኛ የሚሰጡበት፣ መልእክቱን እየዘነጉ መልእክተኛውን የሚያደንቁበት፣ ሳመስግንህና አመስግነኝ የሚሉበት ከንቱ የሕይወት ዘይቤ ነው። ውዳሴ ከንቱ ማለት ከንቱ ውዳሴ ማለት ነው። እግዚአብሔር ሰዎች የሚሉንን አይለንም። የድጋፍ ፊርማም ወደ መንግሥቱ አያስገባንም። እግዚአብሔር የራሱ ሚዛን አለው። ውዳሴ ከንቱ የሚጎዳው የተቀበለውን ሰው ነው። ውዳሴ ከንቱን የተቀበለ ሰው ተግሣጽን ይጠላል፣ እውነተኞችን ይሸሻል። በአየር ላይ ይንሳፈፋል፣ ባልሆነው ነገር

በውሸት ደስ ይለዋል፣ ገንዘቡን ለሸንጋዮች ይበትናል፣ አዝማሪዎችን ይሸልማል፣ ከገሀዱ ዓለም ወጥቶ የራሱን ዓለም ያቋቁማል፣ ውሸቱን ተቀብሎ መልሶ ይናገራል፣ የውዳሴ ከንቱ ሱስ ተጠናውቶት አወድሱኝ እያለ ይቆሰቁሳል፣ ውዳሴ ሲቀርበት እንደ ሕፃን ያኰርፋል፣ ዓለም ሁሉ እያደነቀው መሆኑን ያስባል፣ በእውነት ሲገስጹት የቀኑበት መስሎ ይሰማዋል፣ የመመለክ እቅድ እያቀደ ከሞተ በኋላም ስሙን ለማንገሥ ይሠራል። በራእይ ላይ ውዳሴ ከንቱ ትልቅ እንቅፋት ነው። ወዳጅ የሚያሳጣ፣ ቀምተው ለመሮጥ ከሚለሳለሱ ጋር የሚያጣብቅ ክፉ ነገር ነው። ውዳሴ ከንቱ ከየትም ስፍራ ይልቅ በቤተ ክርስቲያን ነግሦአል። ማመልከቻም ሆኗል።

መልካሙን መልካም ማለት የትክክለኛ ሰው ባሕርይ ሲሆን ውዳሴ ማብዛት ግን ሁልጊዜ ትክክል አይደለም። ያደነቅነውን ነገር መከተል እንጂ ማወደስ አይበጀንም። ነቀፋን የምንሸሸውን ያህል ውዳሴ ከንቱንም መሸሽ አለብን። ውዳሴ ከንቱ ራስን የማያሳይ ድንግዝግዝ መስተዋት ነውና። ለጥፋታችን ራሳችንን ተጠያቂ ማድረግ፣ ለመልካምነታችን ግን ምክንያቱን እግዚአብሔር ማድረግ ልዩ ውበትን ያላብሰናል። በራእያችን ከሆነው በላይ የሚክቡንን መጠንቀቅ አለብን። ሥጋ በባሕርይው ውዳሴ ከንቱን ይወዳል። ሰይጣን በትልቁ ገደል በትዕቢት ውስጥ የሚጥለን በውዳሴ ከንቱ ከጠለፈን በኋላ ነው።

ራእያችንን በአገልጋይነት መንፈስ መፈጸም ይገባናል እንጂ ባለ ውለታነት ሊሰማን አይገባም። ጌታችን፦ «... *እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ፦ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን። ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ*» ያለውን የሁልጊዜ መመሪያችን ልናደርገው ይገባል (ሉቃ. 17÷10)።

ሳይገባቸው የሚደግፉን

ሰውዬው ያልተማረ እንደሚባለው ጨዋ ነበር። ታዲያ ባለ ቅኔው መምህር ቅኔአቸውን ሲያቀርቡ ሰምቶ፦ «የኔታ መልካም ነው» አላቸው። እርሳቸውም፦ «አንተ ደግሞ ምኑ ገብቶህ ነው መልካም ነው ያልከው?» ቢሉት «አይ የኔታ ከእርስዎ አፍ ክፉ አይወጣም ብዬ ነው» አለ ይባላል።

ቅኔ ሲቀርብ ቅኔውን የተረዱና የተመሰጡ ሰዎች «መልካም ነው፣ መልካም ነው» እያሉ ያደንቃሉ። ይህ ሰው የገባቸውን ሰዎች

ንግግር ተቀብሎ እንደ ገባው ሆኖ መልካም ነው አለ። ብዙዎች አልገባቸውም። ያልገባው ላለመባል እንደገባው ሰው ሲናገሩ ይሰማሉ። አንደበተ ትልቅ፣ ውስጠ ቀላል ይሆናሉ። ሳይጽፉ ደራሲ፣ ሳይማሩ መምህር ለመባል የሚፈልጉ፣ የሌላውን መሥዋዕትነት እንደ ራሳቸው ዋጋ አድርገው ማቅረብ የሚፈልጉ ብዙዎች ናቸው። የክብር ሽሚያ ባለበት ዓለም የክብር ሌብነትም አለ። ሳይገባቸው አንገት የሚነቀንቁ፣ ሳይሰሙ አዎ የሚሉ ብዙዎች ናቸው። በጸሪና አካባቢ ከአማርኛ «አዎ» የምትል ቃል ብቻ የሚያውቅ ገበሬ የደርግ ወታደሮች ይመጡና «በዚህ አካባቢ አሸባሪዎች ነበሩ?» ይሉታል። እርሱም «አዎ» አለ። «ሰው ሲገድሉ ነበረ?» አሉት። መልሶ «አዎ» አላቸው። «አንተም ከእነርሱ ጋር ነበርክ?» አሉት አሁንም «አዎ» አለ። «እየገደልክ ነበር?» ሲሉት መልሶ «አዎ» ሲል የሚናገሩትን እንደማይሰማ አውቀው ጥለውት ሄዱ። የሚጠየቁትን ሳይሰሙ መልስ የሚሰጡ፣ የሌለውን ነገር እንዳለ አድርገው ያቀርባሉ። ራሳቸውንም ላልተረዱት ነገር መሥዋዕት አድርገው ያቀርባሉ። መሥዋዕትነት ደስ የሚለው ለምን ዋጋ እንደምንከፍል ስናውቅ ብቻ ነው። በእውነት እንደ ገባው ሰው መንቀሳቀስና የገባው ሰው መሆን ልዩነት አለው።

የዓይን ቀለማችን አስጠልቷቸው የሚቃወሙንን ያህል ሳይገባቸው የሚከተሉንም ብዙዎች ናቸው። እኛን ስለወደዱን ብቻ እኛ የያዝነው ሁሉ ክፉ ሳይመስላቸው የሚጓዙ ወገኖች ብዙ ናቸው። በራእይ ላይ እነዚህ ሰዎች አስፈሪ ናቸው። ሳይገባቸው ከሚደግፉን የሚቃወሙን ይሻላሉ። እነዚህ ወዳጅነታችን ብቻ ያሰራቸው፣ ስለለመዱን የማይለዩን ሰዎች የማንጠብቃቸው ሰባሪዎቻችን ናቸው። ስለዚህ በራእያችን በውዳሴ ከንቱ የሚክቡንንና ሳይገባቸው የሚደግፉንን ሰዎች የነቃፊዎቻችን ያህል ልንጠነቀቃቸው የሚገቡ ናቸው።

እናስተውል

- በተመረቀ መንገድ በነጻነት እንደሚፈስስ መንገደኛ ጌታችን በቀደመበት፣ የንጉሥ ፊታውራሪ በወጣበት ፍኖተ ራእይ በደስታ እንጓዛለን።
- ዙሪያው ሁሉ ጦርነት ቢሆን ውስጣችን ግን ከጸና የራእይን ግብ ማሟላት ይቻላል።
- የሰው ዓለም ክብር ሰራቂ ነው። የተከበረውን ከተዋረደው የማይለይ፣ የእውነትን ሚዛን የጣለ ነው።

- እውነተኛ ሥልጣኔ ሰውን በሚገባው ስፍራ ላይ የሚያስቀምጥና የሚያደላድል ነው።
- ውዳሴ ከንቱ እንደ ሰፈር ምጣድ ካንዱ ወዳንዱ ሲፋለስ ስንቱን ሞኝ ከእውነቱ ሲያፋልስ ይኖራል።
- ውዳሴ ከንቱ የሚጎዳው የተቀበለውን ሰው ነው። ውዳሴ ከንቱን የተቀበለ ሰው ተግሣጽን ይጠላል፣ እውነተኞችን ይሸሻል።
- መሥዋዕትነት ደስ የሚለው ለምን ዋጋ እንደምንከፍል ስናውቅ ብቻ ነው።

ምዕራፍ ሃያ አራት

ተቃውሞ

የእንግሊዝ መሪ የነበሩት ዊንስተን ቸርችል በንግግር ችሎታቸው የተደነቁ እንደነበሩ እናውቃለን። ዊንስተን ቸርችል ንግግር ሲያደርጉ ብዙ ሺህ ሕዝብ ተሰብስቦ ያዳምጥ ነበር። አንድ ቀንም ጋዜጠኛው ዊንስተን ቸርችልን፡- «እርስዎ ንግግር ሲያደርጉ ብዙ ሕዝብ ለመስማት ይሰበሰባል፣ እንደው ምን ይሰማዎታል?» አላቸው። እርሳቸውም ሲመልሱ፡- «ተፈርዶብኝ ብሰቀል ደግሞ ከዚህ የበለጠ ሕዝብ እንደሚሰበሰብ ይሰማኛል» አሉ ይባላል።

ሕይወት ሲሆን ብቻ እንድናውቃት ሆና አልተሠራችም። ከመሆኗ በፊት የምናይበት ብዙ መነጽሮች አሉ። ትንቢት፣ ቅዱስ መንፈስ፣ ማስተዋል፣ እውቀት፣ ታሪክ፣ በመኖር የቀደሙን ወገኖች የኑሮ ልምድ፣ ያሳለፍነው ታሪክ ነገን የምናይበት መነጽር ነው። ሰዎች ከምስጋናቸው ርግማናቸው እንደሚበዛ፣ ከፍቅራቸው ጥላቻቸው እንደሚጠነክር፣ የማቀፍና የመገፍተር ጊዜ እንዳላቸው ካላወቅን እንጎዳለን። የድጋፍ ጩኸታቸው የውዳሴ ቃላቸው፣ የቅርበት ልስላሴአቸው፣ አፈር ልብላልህ እያሉ ማጉረሳቸው ቀጥሎ አፈር ያበሉኛል ብሎ ለመገመት ያስቸግራል። ነገር ግን አስብተው እንደ በሬ ያርዱናል። ይህን መከራ እኛ የምናሟሸው ሳይሆን ሲደረግ የነበረ፣ አሁንም በሌሎች የሚደረግ ነው። በእኛ ላይ ሲደርስ ዓለም አዲስ አመል ያመጣች ይመስለናል እንጂ ይህ የየዕለቱ ክንውን ነው። ዊንስተን ቸርችል በንግግራቸው የተደነቀ፣ በሐሰተኛ ፍርድ ሲሞቱም እንደሚደነቅ «ፐ» እያለ እንደሚመለስ ተረድተዋል። ሁልጊዜም መሰብሰብ፣ ሲናገሩ መሰብሰብ፣ ሲሰቀሉም መሰብሰብ፣ ተሰብስቦ ማለፍ የብዙዎች ኑሮ ነው። በዛሬው አድናቆት ውስጥ ነገን ማየት ትልቅነት ነው። ድንቅ ስንናገር ከወጣው በላይ ፍርድ አጥተን ስንሰቀል የበለጠ ሕዝብ ይወጣል።

ራእይ የልደት ዘመኑ ሲቃረብ ብዙ ምጥና ጭንቀት ይታይበታል። ከአጠገባችን የሚንሸራተቱትን የወዳጆች ብዛት ማየት ይሰለቻል። የወዳጅ አሥራት እስኪናፍቀን እገሌ እንኳ ምነው በቀረልኝ እስክንል ሁሉም ገለል ይላል። ራእይ ግን በዚህ ሁሉ ውስጥ አልፎ የሚሄድ መለኮታዊ ግብ ነው። ጳውሎስ ታላቅ ራእይ የነበረው፣ ዓለምን በወንጌል የመድረስ እምነት ይዞ የተነሣ፣ ሕይወቱንም ለዓላማው ብጽአት አድርጎ የሰጠ ሐዋርያ ነው።

በቆሮንቶስ ከተማ ሆኖ ሮምና ስፔን ይታዩት ነበር (ሮሜ 15÷24)። ከዚህ በፊት የማያውቃቸው አገሮችና ሕዝቦች ቢሆኑም ራእዩ ግን የምዕራቡን ጥግ ያይ ነበር። ጳውሎስ ይህንን የወንጌል ራእይ ለመድረስ ሲነሣ መንገዱ ምቹ አልሆነለትም። ብዙ መከራና ፈተናን ተቀብሏል። እነዚያ ሁሉ የሚቋቋሙ ትግሎች ጳውሎስን እንዳላሸነፉት እኛ ምስክር ነን። ራሱ ጳውሎስ መከራውን ዘርዝሮ ከጻፈ በኋላ የሚያሳስበው ራእዩ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን መሆኗን ገልጧል፦

«...በድካም አብዝቼ፥ በመገረፍ አብዝቼ፥ በመታሰር አትርፌ፥ በመሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ። አይሁድ አንድ ሲጕደል አርባ ግርፋትን አምስት ጊዜ ገረፉኝ። ሦስት ጊዜ በበትር ተመታሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወገርሁ፤ መርከቤ ሦስት ጊዜ ተሰበረ፤ ሌሊትና ቀን በባሕር ውስጥ ኖርሁ። ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤ በወንዝ ፍርሃት፥ በወንበዴዎች ፍርሃት፥ በወገኔ በኩል ፍርሃት፥ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፥ በከተማ ፍርሃት፥ በምድረ በዳ ፍርሃት፥ በባሕር ፍርሃት፥ በውሸተኛ ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ፥ ²በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፥ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ። የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፥ ዕለት ዕለት የሚከብደብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው» (2ቆሮ. 11÷23-28)።

ጳውሎስ የተመካው ባማረ ቀሚሱ፣ በተዋበ ቀፀላው፣ በተከበረው ካባ አይደለም። ጳውሎስ የተመካው ስለ ራእዩ በከፈለው ዋጋ ነው። እውነተኛ ባለ ራእይ በወርቁ ሳይሆን በጠባሳው ይመካል። የእውነተኛ ባለ ራእይ ምልክቱ ዘውድ ሳይሆን የእሾህ አክሊል ነው። ጳውሎስ ብዙ ፍርሃቶችን እንዳስተናገደ ጽፏል። እነዚህ ፍርሃቶች ስምንት ነበሩ። ለዛሬው ባለ ራእይ ጉልበት እንዲሆኑ እንዘረዝራቸዋለን፦

1. ወንዝ
2. ወንበዴዎች
3. ወገን
4. አረማውያን
5. ከተማ
6. ምድረ በዳ
7. ባሕር
8. ቢጽ ሐሳውያን

እነዚህ ፍርሃቶች ዛሬም አሉ። የሰው ሕይወት ተመሳሳይ ገጠመኝ ስላለው ነው ያንዱ ልምድ ላንዱ ትምህርት የሚሆነው። ጳውሎስን ያመመው እኛንም ያመናል።

1- <u>በወንዝ ፍርሃት</u>

ጳውሎስ ኑሮውን ለማቅናት ሳይሆን ወንጌልን ለፍጥረት ለማድረስ ሲጓዝ ብዙ ፍርሃቶች ገጥመውታል። ከፍርሃቶቹ አንዱ የወንዝ ፍርሃት ነው። ከወንዙ እስከ የብሱ ያለው ርቀት አጭር ቢሆንም አስጨናቂና አስፈሪ ነው። ዋና ለማይችል ጀልባ ሰሌሰው ምስኪን ይበልጥ ያስጨንቃል። ከወንዝ መሐል ሲደርሱ ደራሽ ውሃ፣ የውሃ ውስጥ አውሬ፣ የሚቆሙበት ስፍራ ማጣት፣ ካጠገብ የሚወሰደው ወዳጅ፣ አንዱ አንዱን መርዳት የማይችልበት ቅጽበት፣ የሞት ጥግ ፍርሃት ናቸው። ጳውሎስ እነዚህ ሁሉ ሳይገጥሙት አልቀሩም። እግዚአብሔር ግን በጎርፍ ከመወሰድ፣ በውሃ ከመስጠም፣ በአውሬ ከመበላት፣ ከሞት አድኖታል። ለመናገር መብቋቱ የመዳኑ ማረጋገጫ ነው።

ወንዝ ቀጥ ብሎ የሚፈስ፣ የማያቋርጥ፣ አጋጅ የሌለው ነው። እርጋታ ስለሌለው ዋናና ጀልባ ያን ያህል አይጠቅሙም። በጣም ጎበዝ ዋናተኞችና ቀዛፊዎች ካልሆኑ በቀር የወንዙን መንገድ ተከትለው ማምለጥ አይችሉም። የማያቋርጠው ወንዝ የኑሮ ፈተና ነው። የኑሮ ፈተና በየዕለቱ አዲስ ነው። እንደ ጅረት የተያያዘ፣ እንደ ሰንሰለት የተቀጣጠለ፣ እንደ ሐረግ የረዘመ ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ እንደ ደራሽ ውሃ ጠርጎ የሚወስድ ክፉ ቀን አለ። የዚህ ፈተና ፍላጎቱ ዕድሜን መቅጨት ነው። ጊዜው አጭር ቢሆንም የሞት ሽረት ትግል ነው። እግዚአብሔር ግን ከዚህም ያድናል። ሚዳቋ የማትዘለውን ጎዶሎ ቀን እግዚአብሔር ሲያሻግረን ብዙ ጊዜ አይተናል። በፈተናው መስጠምና ለኑሮ ፍርሃት የኃጢአት አገልጋይ መሆን አንዱ የሰው ገጽታ ነው። ጠብ ለማይል ኑሮ ስንቱን እንሆነዋለን። የምንቆምበት ስፍራ እስክናጣ ሁሉም ነገር የሚያጠራጥር፣ ሰው ሁሉ ተዋጊ መስሎ የሚታይበት ጊዜ አለ። ከአጠገብም ብዙ ወዳጆች ይንጠባጠባሉ።

ወዳጅ ለክፉ ቀን ይሆናል አትበለው፤
ስትያዝ ይሸዳል ሰው የጴጥሮስ ልጅ ነው፤

አንዱ አንዱን መርዳት የማይችልበት ሁሉም ቤት ልቅሶ የሚገባበት ጊዜም አለ። የወንዝ ፍርሃት በእኛም የሚደርስ ነው።

ልዩ ችሎታ ያላቸው የወንዙን አቅጣጫ ተከትለው መዋኘ ትና መቅዘፍ እንደሚችሉ የዘመኑንም ሽንገላና ቴክኖሎጂ አጥንተው እንደ እውነቱ ሳይሆን እንደ ዘመኑ የሚራመዱ ሰዎችን ሰናይ እንደ እነርሱ መሆን ባለመቻላችን እንፈራለን። የዘመናችን ትውልድ ለቴክኖሎጂው የተሰጠ፣ በራስ ወዳድነት የሚደርስበት የሌለ፣ በቁልምጫ ቃላት የተንቆጠቆጠ በልቡ ላይ ግን የእውነት ቀለም ጠብ ያላለበት ልበ ነጭ ትውልድ ነው። ወላጆች በእነዚህ ልጆች ፍጥነት ተማርከዋል። ትዳራችንን ምሩት ብለው አሳልፈው ሰጥተዋቸዋል። እነዚህ ልጆች የቴክኖሎጂ እንጂ የኑሮ እውቀት ፍጹም የላቸውም። ፍጥነታቸውም እግዚአብሔር የሌለበት በመሆኑ እንደ ጥላ ቶሎ ያልፋሉ። እንደ እነርሱ መሆን ባለመቻላችን የማንኖር እየመሰለን እንፈራለን። መኖር ግን በእግዚአብሔር ነው። ከዘመኑ ጋር ሰምና ወርቅ ነን ብለው የሚያስቡት ልጆች በምድር ላይ የሌሉ ሆነው በአየር ላይ ይንሳፈፋሉ። ለሞት ግን ሞኞች ሆነው የእሳት እራት ሆነዋል። ፍጥነታቸውም በድንገት ያልቃል።

ባለቅኔው፦

የቀድሞ ሰዎች ውኃ ዋና፣
ላይ ላዩን ነበር በጤና።
የዛሬ ልጆች ይበልጣሉ፣
ውሰጥ ለውሰጥም ይሄዳሉ።

ብለዋል። አሳቡ የጥንቱ ቅንነትና ግልጽነት ዕድሜን ሲያተርፍ የልጆች ተንኮል ግን ዕድሜን እንደሚያሳጥር ለመግለጽ ነው። የአገራችንም ሽማግሌዎች፦

የድሮ ሰው ልብሱ አዳፋ፣
ነገሩ ጎልዳፋ፣
ከዕድሜው የገፋ፣
የዛሬ ልጅ ልብሱ ነጭ፣
ነገሩ ምላጭ፣
ከዕድሜው ይቀጭ፣

ይላሉ። ዛሬ ያለው ትውልድ ይህን ተግሣጽ መቀበል ቢከብደው እንኳ በተግባር እየሆነና እያለቀ ነው። መጽሐፉ «*የደም ሰዎችና ሸንጋዮች ዘመናቸው ግማሽ አይሞላም*» (መዝ. 54/55/፥23) ይላል። የሰው ዕድሜ ቢበዛ ሰማንያ ነው (መዝ. 89/90/፥10) ስለተባለ የሸንጋይ ዕድሜ አርባ አይሞላም ማለት ነው። ዛሬ የዕድሜ መቀሱ አርባ ላይ መቆረጡን እያየን ነው። በራእይ ላይ አጭር የሆኑ ግን የሚከብዱ የፈተና ቀኖች ወይም የወንዝ ፍርሃቶች አሉ።

2- በወንበዴዎች ፍርሃት

ወንበዴ የምንለው ሌቦችን አይደለም። ከሌባ የከፉ ሰራቂዎችን ነው። ሌባ ሰው ባለበት የሚኖር ሰውዬውን እንደ ገቢ ምንጩ አድርጎ በመቍጠር የማይተናከል ሳይታወቅበት ወዳጅ፣ ከታወቀበት በኋላ ዓይናፋር የሚሆን ነው። ወንበዴ ግን ከሰውና ከመንግሥት ርቆ በዱር በገደል የሚኖር ሁሉን እንደ ጠላቱ አድርጎ የሚመለከት በዱር መንገድ ላይ አቍሞ የሚዘርፍ፣ ገንዘብን ብቻ ሳይሆን ሕይወትንም የሚሰርቅ እጹ በደም የተጨማለቀ ነው።

ሌቦች ማታለልን ይጠቀማሉ፣ ወንበዴዎች ግን ኃይልን ይጠቀማሉ። ሌቦች መኖርን በጣም ይፈልጋሉ። ወንበዴዎች ግን አጥፍቶ ጠፊ ናቸው። ሌቦች የወንዱን ኪስ ከሚስትዬው የበለጠ ያውቁታል። ሕዝቡ በባዶ ኪስ እንደሚዘንጥ ወይም ቋጥሮ እንደሚራቆት በደንብ የሚያውቁ፣ የአእምሮ ጉልበታቸውን ለመጥፎ ዓላማ የሚጠቀሙ ናቸው። ወንበዴዎች ግን የሕዝቡን ሥቃይ ለማወቅ የማይፈልጉ ሥቃይ እየጨመሩ በጭካኔ የሚረኩ ናቸው። ሌባ ሌባ መባሉን እንዳልሰማ ያልፈዋል እንጂ በመከራከር ራሱን አያጋልጥም። የሰውን ቋንቋ ደግማ ትናገራለች እንደምትባል ወፍ ተሰረቅሁ ብለው ሲጮኹ እርሱም አብሮ ይጮኻል። ሌባ ብለው ሲመቱት ሌባ ብሎ ይማታል። ወንበዴ ግን ቂመኛ ነው። እንኳን የሰደበውን ጠቦት ላክልኝ ብሎ የለኝም ያለውን ገበሬ ይገድላል። ሌቦች እነርሱን የሚጠብቁ ብዙ ሴቶች ስላሉ ሰርቀው ሄደው የአሰራረቁን ሂደት ቡናው እስኪያከትም ከተረኩ በኋላ ገንዘቡን አስቀምጠው ይሄዳሉ። የኃጢአት ገንዘብ በኃጢአት ያልቃል። ወንበዴዎች ግን ትዳርን የካዱ፣ ባልን እየገደሉ ሚስትን የሚሰርቁ ናቸው። ሌቦች ውሸታሞች ናቸው፣ ወንበዴዎች ለመዋሸትስ ማን ጠይቋቸው? ሌቦች በእርግጥ ሲነቃባቸው አጎንብሰው ይደበደባሉ እንጂ ኮርተው አይጣሉም። ወንበዴዎች ግን ሳይቀደሙ ይቀድማሉ። ሌቦች የሰረቁ ቀን ቀያይ ብር ለለማኝ ይመጸውታሉ። ወንበዴዎች ግን ለማንም አይራሩም። ሌቦች ከምግብ ይልቅ ለሱሳቸው ያደላሉ። ወንበዴዎች ግን በመብላት ያምናሉ። ሌቦች ከእናታቸው ቤት አይርቁም። ወንበዴዎች ግን ዱር ቤቴ ናቸው። ሌቦች ደረጃቸው ውሸት + ሌብነት + ነፍሰ ገዳይነት ነው። የወንበዴዎች ግን ነፍሰ ገዳይነት + ሌብነት + በጭካኔ መርካት ነው።

ጳውሎስ ወንጌልን ለማስተማር በረሃና ዱሩን ሲያቋርጥ ብዙ ጊዜ የወንበዴዎች ፍርሃት ገጥሞታል። ንብረትንና ሕይወትን

የሚሰርቁ ወንበዴዎች ቢገጥሙትም እግዚአብሔር ግን ብዙ ጊዜ አድኖታል።

ዓለም ዱር መስሏቸው የሰውን ሕይወት እየቀጠፉ ለመዝረፍ የሚተራመሱ ወንበዴዎች በኑሮአችን ይገጥሙናል። የበሉት ሁሉ የሚስማማቸው፣ ጉልበታቸውን ለማንሣት ሳይሆን ለመጣል የሚጠቀሙበት፣ እንደ ተበደለ ሰው እያፈጠጡ የሚኖሩ፣ በአፈ ጮሌነታቸው የታወቁ፣ ቀምቶ አዳሪዎች፣ ከአንድ ብርና ከአንድ ሰው ቢባሉ አንድ ብር ይበልጣል የሚሉ፣ የቁምነገርን ዋጋ የጣሉ ሰዎች በኑሮአችን ፍርሃት የሚሆኑብን ጊዜ ብዙ ነው። መፍራት ግን በሰልቱ የሚኖረውን ሰው ሳይሆን ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለውን ሰው ነው። ለራሱ የሚዋጋ ይሸነፋል። እግዚአብሔር የሚዋጋለት ግን አይሸነፍም። ኃይለኛ፣ ኃይለኛ የሚሆነው እግዚአብሔር እስኪነሣ ነው። እግዚአብሔር ሲነሣ ግን የሥጋ ብርታት አይቆምም። ነቢዩ፡- «እግዚአብሔር ይነሣ፥ ጠላቶቹም ይበተኑ» (መዝ. 67/68/፥1) እንዳለ። በራእይ ላይ ብዙ ጨካኞች ይገጥሙናል። የጨካኞች ብዛት ግን ራእይን ሊያቆመው አይችልም።

3- በወገኔ በኩል ፍርሃት

ወገን መደበቂያ ነው። የገዛ ወገን ግን ሲያሳድድ ከባድ ነው። ወገን ሲጨክን ከባዕድ ይከፋል። ጳውሎስ የገዛ ወገኖቹ ከሚሆኑ አይሁዳውያን ብዙ እንግልትና ስደት ደርሶበታል። ለባዕድም አሳልፈው ሰጥተውታል። ይህን ሁሉ ያደረጉት ለሃይማኖታቸው ቀንተው ይመስላል። ሃይማኖት ግን ሙቱ እንጂ ግደሉ አትልም። ጳውሎስ ቀድሞ አክራሪ አይሁዳዊ ስለነበር ይህን ሁሉ ጥሎ ክርስቲያን ሲሆን ወገኖቹ እንደ ከዳተኛ ቆጠሩት። ጠላትማ ጠላት ነው አስቀድሞ መግደል ጳውሎስን ነው አሉ። ስለዚህ በግፍ ከሚገሏቸው ሮማውያን ይልቅ እርሱን ጠልተውት ያሳደዱት ነበር። ሃይማኖታዊ አክራሪዎች የጠሉትን ሰው ከምድር ሊያጠፉት ይፈልጋሉ። በዜግነቱ እንኳ የመኖር መብት እንዳለው ይረሳሉ። እንደ እኔ ካላሰብክ ጥፋ ማለት የሃይማኖት ችግር ብቻ ሳይሆን የሰብአዊነትም አለመሟላት ነው። እግዚአብሔር እንኳ ይህን አላለም።

ጳውሎስ ድሮ ነፍስ ሲያጠፋ እውነተኛ አማኒ ይሉት ነበር። አሁን ግን ለመሞት ሲዘጋጅ ከሃዲ ይሉታል። የትላንቱን ኑሮ እርሱ ብላሽ ይለዋል፣ ወገኖቹ ደግሞ የዛሬውን ኑሮ የተበላሸ ይሉታል።

የሰው ሚዛን እንደ ዋለለ ነው። እግዚአብሔር ግን የእውነት መለኪያ ነው።

ከወገን በኩል ፍርሃት ዛሬም ብዙዎች የሚያልፉበት ነው። ሲለክር የነበረ ጨዋ ሲሆን ስም ይሰጠዋል። ጠንቋይና አስማተኛ ተከብሮ እየኖረ ወንጌልን የተሸከመ ይሰደዳሉ። አመንዝሮችና ቀማኞች የሚወቅሳቸው እንኳ አጥተው እውነተኛ ሰባክያን ግን ይከሰሳሉ። ትላንት ያስተማሩት ዛሬ ከሳሽ ሲሆን ትላንት ያላመኑት ዛሬ አንተ ከሃዲ ነህ ሲል ትላንት ያበሉት ዛሬ ሲነክስ የሚያስፈራ ቢመስልም እግዚአብሔር ግን ያድናል። የቀድሞውን አንድነታችንን በሚያውቁ አረማውያን ፊት መጣላት አሳፋሪ ነው። ነገር ግን እውነት ያመጣችውን ከመቀበል ውጭ የመከራውን ቅርጽ ማውጣት አይቻልም። ጳውሎስ ይህ ሁሉ ፍርሃት ቢደርስበትም ዛሬ የምናደንቀው እርሱን እንጂ አሳዳጆቹን አይደለም። የአሳዳጆቹ ኃይል ዛሬ የሰም። የጳውሎስ የመልእክቱ ኃይል ግን ዛሬም አለ።

ክርስቲያን ሊሰደድ ሲገባ አሳዳጅ ከሆነ፣ ሊሞት ሲገባ ገዳይ ከሆነ፣ መስቀል መሸከም ሲገባው መስቀል አሸካሚ ከሆነ በጣም ያሳዝናል። ከዚህ ሁሉ በላይ ክርስቶስ ቀድሞ አይሁድ ያባረሩት ከምኩራባቸው ነበር። በስሙ ከተጠራች ቤተ ክርስቲያን ከተባረረ ግን በጣም ያሳፍራል። በራእይ ላይም ከሚነሡ ውጫዊ ተቃውሞዎች አንዱ ከወገን የሚነሣው ተቃውሞ ነው።

የሩቅ ተቃዋሚዎች የገዛ ትዳራችንን፣ የገዛ ወላጆቻችንን ሳይቀር ተቃዋሚ አድርገው ያስነሡብናል። የእኛ የምንላቸው ሳይቀሩ እኛን ለባዕድ አሳልፈው በመስጠት ይረካሉ። በእኛ ሞትም ቀድሞ ከሚነቅፏቸው ሰዎች ጋር ይስማማሉ።

4- በአሕዛብ በኩል ፍርሃት

በብዙ ጣኦቶች የሚያምኑ ደግሞም ፈጽሞ እምነት የለሽ የሆኑ ሰዎች ለጳውሎስ ብቻ ሳይሆን ለብዙዎች ፍርሃት ናቸው። ሊውም የተባለ ፈላስፋ እግዚአብሔር የለም ብሎ ቢናገርም በሕይወቱ ግን ይፈራ የነበረው እግዚአብሔር የለሽ የሆኑ ሰዎችን ነበር። ይህ ፈላስፋ፡- «ሃይማኖት የለሽ ከሆኑ ሰዎች ተጠንቀቅ። እነዚህ ሰዎች በሕይወትህ ዘመን ካጋጠሙህ አራዊቶች በጥቂት ብቻ እንደሚለዩ እወቅ» ብሏል።

ጳውሎስ የአሕዛብ መምህር እንደ መሆኑ አገልግሎቱ ዱር መመንጠር በረሃ ማልማት በመሆኑ ከባድ ነበር። እግዚአብሔር ግን

በላከን ስፍራ ጸጋውን ያበዛልናል እንጂ ብቻችንን አይተወንምና ጳውሎስ በረታ። እነዚህ አረማውያን ትክክለኛ አምነት ስለ ሌላቸው ከሞራል ሕግ ውጭ ሆነው በሰይፍ የሚያሳምኑ ናቸው። ጳውሎስም በሚሰብከው ክርስቶስ አምነታቸው የጠፋ እየመሰላቸው መቆጣታቸው አልቀረም። ሁሉም በግዛቱ ጀግና ነውና ወደ ግዛታቸው ሲገባ ዛቻና ማስፈራሪያ ሳይልኩበት አልቀሩም። ጳውሎስም በአሕዛብ በኩል ፍርሃት ነበረበት። ዛሬ የዓለም ታላላቅ አገሮች ብሔራዊ ሃይማኖት የሆነችው ክርስትና እነ ጳውሎስ በእንዲህ ያለ አደጋ ውስጥ አያለፉ የሰበኳት መሆኗ ይገርማል።

አረማውያን ሰው ከነጻ አሳብ ጋር መፈጠሩን ስለማይገነዘቡ በሰይፍ ለማሳመን ይነሣሉ። የሰው ልጅ እኩልነት፣ የሴትና የወንድን የተፈጥሮ ክብር በቅጡ የማይረዱ የገንዘብና የሰይፍን ኃይል የሚጠቀሙ በመሆናቸው ብዙ ትምህርት መስጠት ግድ ይለናል። ዛሬም ያልተጠመቁ ወገኖች ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ስጋታችን ሆነዋል። እኛም ወንጌል የያዘውን ገፍተን እነርሱን ስናቀርብ ብንኖርም እንደ ወደድናቸው አልወደዱንም። «ይሻላሉ» እያንል ስንናገር ኖረናል። የመሻል መስፈርት ካነሣን በስመ ክርስትና የተጠራው ወገን አይሻለንም ወይ? ቢያንስ ይህ ወገን አያርደንም። ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ፈተና ከፊቷ ላይ ተደቅኗል። የክርስቲያኑ አርስ በርስ መለያየት እንዲጠነክሩ ያደረጋቸው አሕዛብ ዛሬ ሰባራ ቀን እየፈለጉ ነው። ቤተ ክርስቲያን ንስሓ ገብታ የወንጌልን ሥራ ካላፋጠነች እግዚአብሔር አሳልፎ እንደሚሰጠን እርግጥ ነው። በተዘዋወርንባቸው አካባቢዎች ሁሉ ቀሳውስትና መነኮሳት በገንዘብ እየተደለሉ የክርስትናን እምነት ሲክዱ እያየን ነው። የሚያሳዝነው ዛሬም አንድ ሕገ መንግሥት የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ የያዙ ክርስቲያኖች አንዱ አንዱን እንደ ከሃዲ እየቆጠረ በቃላት ይፋጃሉ እንጂ ሁሉም የወደፊቱን አደጋ ማየት አልቻሉም።

በራእይ ላይም በፈሪሃ እግዚአብሔር፣ በክርስቶስ ፍቅር የማይዳኙ አረማውያን ፍርሃት የሚሆኑብን ጊዜ ብዙ ነው። በመንገዳችን ላይ በመቆም አላሳልፍም ይሉናል። ሃይማኖት ስለሌላቸው የመግባቢያ ቋንቋ፣ የቅንነትን ጸጋ እያጣንባቸው ያታግሉናል። እግዚአብሔር ግን ከሚታየው ብቻ ሳይሆን ከማይታየውም ጠላት ያድናል።

5- <u>በከተማ ፍርሃት</u>

ከተሞች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚገኙ፣ ብዙ የሕዝብ እንቅስቃሴና በቂ ጥበቃ ያለባቸው፣ የሰለጠኑና ሕግ

የሚከበርባቸው፣ ለመረጃ ቅርብ የሆኑ ቢሆኑም ፖሊስ የማይቆጣጠራቸው ብዙ አስፈሪ ነገሮች ግን በከተማ ውስጥ አሉ። ከእነዚህ ፍርሃቶች አንዱ የኑሮ ፍርሃት ነው። ጳውሎስ በከተማ ፍርሃት ያለፈበት ጊዜ ነበር።

ሕዝብ እየተተራመሰ፣ ፖሊስ ጠንክሮ እየጠበቀ እንዴት በከተማ ውስጥ ፍርሃት ይኖራል? እንል ይሆናል። ይህ ግን በኑሮ ውስጥ የሚገጥም አንዱ ገጽታ ነው። ፍርሃት ሕመም አለው። ሁሉንም ነገር የምንፈራበት ጊዜ በኑሮ ላይ ይገጥመናል። ከቤታችን ለመውጣትና አድናቂዎቻችንን እንኳ ለማግኘት የምንፈራበት ጊዜ አለ። ለፍርሃት ከሸሹለት ግን ይገናል እንጂ አይበርድም። እንዲህ ያለ ወቅት ሲገጥመን በብዙዎች የነበረ በመሆኑ መደናገጥ አይገባንም። ቀስ ብለን በመጋፈጥ ረድኤትን ከነጻነት አምላክ በመለመን ልንወጣ ይገባናል። ብዙ አጃቢ እያለን የምንፈራበት፣ በትዳር መካከል በብቸኝነት የምንናጥበት ጊዜ ብዙ ነው። የሚያስፈራ ሳይኖር ብዙ ዘመን ፈርተናል። ሰው ሁሉ ፈሪ ነው። መሣሪያ የያዘን ሁሉም ይፈራል። እርሱም ፈርቶ መሣሪያ መያዙን ግን እግዚአብሔር ያውቃል። ይልቁንም ሥልጣንና ሀብት ድፍረት የሚሰጠን ቢመስለንም እነዚህ ነገሮች ግን ዋናው የፍርሃት መስክ ናቸው።

በማንኛውም ጊዜ የመፍራት ሥልጣን አለን። አሁንም ከፈለግን መፍራት እንችላለን። እንዲህ ቢሆንስ ብለን መንቀጥቀጥ እንችላለን። ሁልጊዜ ፍርሃታችን ትክክለኛ አይደለም። በቂ መረጃም የሌለው ጥርጣሬ ነው። አጠገባችን ያሉ ሰዎችና የጨበጥነው እሴት ቢሄድስ እያልን የምንፈራበት ጊዜ ብዙ ነው። የማይሄደውን ጌታ ካልያዝን የዚህ ዓለም ነገር ከፍርሃት አያድንም። በዚህ ዓለም ላይ የሚያስፈራው የመጨረሻው ነገር ሞት ነው። ሞት ስለ ፈራን አይቀርም። ሞት ርስት ነው። ፈርተን ዘጠኝ ጊዜ ከመሞት አንዱን ሞት አንድ ጊዜ መሞት የተፈጥሮ ጸጋ ነው። እምነታችን ሲደክም ፍርሃት በውስጣችን መበርታት ይጀምራል።

አጥሩ ጠብቋል፣ የመቆጣጠሪያ ቴሌቪዥን ተሰቅሏል፣ የጀርመን ውሻ ይንሳፈዳል፣ የጦር መሣሪያ ከትራስ ሥር ተቀምጧል። ሰውዬው ግን ሲያሯሩጡኝ አደሩ፣ ቅዥቱ አስቸገረኝ ይላል። ይህ ሁሉ ከፍርሃት አያድንም። ራሳችንንና ነገራችንን ሁሉ ለእግዚአብሔር በመተው ብቻ ጠንካራ ሰዎች እንሆናለን። ወዳጆቼ አጥሩ ከፍርሃት ካላዳነን፡- *«እኔ በዙሪያዋ የእሳት ቅጥር እሆንላታለሁ፥ በውስጥዋም ክብርን እሆናለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር»* (ዘካ. 2÷5) በሚለው ቃል ማረፍ አለብን። ዘቡም

አላሳርፍ ካለን፦ *«እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፥ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል»* (መዝ. 126÷1) የሚለውን ቃል ማመን አለብን። ሰው ፍርሃት ሲሆነን፦ *«በእግዚአብሔር ታመንሁ፥ አልፈራም፤ ሰው ምን ያደርገኛል?»* ልንል ይገባል (መዝ. 55÷11)። አንድ ደፋር የሆኑ ሰው ስለ ድፍረታቸው ሲናገሩ፦ «እኔ የምደፍረው በወንድነት አይደለም። ከጀርባዬ ያለው ጌታ አላስነካህም ስለሚለኝ ነው» ብለዋል። እንደ እርሳቸው የደፈረ ባላይም ምንም ሳይሆኑ በእግዚአብሔር እጅ አልፈዋል። ዓለሙ ፈሪ ሲሞትበት ካንጀቱ የደፈረ ሲከበርበት እናያለን።

በራእይ ላይ የከተማ ፍርሃት ይገጥመናል። ከነቀፋውና ከምንባለው የተነሣ ደጁን እስክንጠላ የምንታወክበት ጊዜ ብዙ ነው። የሚያስፈራ ነገር ሳይገጥመን ራሱ ፍርሃት የሚመጣብን ጊዜም ብዙ ነው። የምናምነው አምላክ ከብዙ ፍርሃቶች የሚያድን ነው። እኛ ችግራችንን ስም ስላጣንለት እንጨነቃለን። ስም የለሽ ከሆነውም ችግር እግዚአብሔር ያድናል።

6- <u>በምድረ በዳ ፍርሃት</u>

ምድረ በዳ ማለት የሚታይ ነገር የሌለበት ማለት ነው። የሚታይ ነገር የሌለበት ብቻ ሳይሆን ድምፅ የሌለበትም በመሆኑ አስፈሪ ነው። ጳውሎስ በምድረ በዳ ሲያቋርጥ ብዙ ነገር ገጥሞታል። ከግብፅ የወጡ እስራኤላውያን የገጠማቸው ነገር በረሃ ነው። በረሃው ለአርባ ዓመት ፈተናቸው ሆኗል። ባለማመናቸው የመጡበትን መንገድ መልሰው በመምጣት የበረሃ አዙሪት አድክሟቸዋል። ከኃጢአትና ከሞት ለዳኑ ክርስቲያኖችም ይህች ዓለም በረሃ ናት። የሚታይ፣ የሚያጠግብና የሚያረካ ነገር የለባትም። ነገር ግን በበረሃ ላይ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብዙ እንክብካቤ እንደ ነበረው ዛሬም ዓለም በረሃ ለሆነችባቸው ምእመናን መናና የዓሉቱ ውኃ አለው። እርሱም የእግዚአብሔር ቃል፣ መንፈሳዊ ጎበረትና ራሱ ክርስቶስ ነው። የምናየው የምንሰማው ስናጣ በፍርሃት እንሞላለን። ቤተ ክርስቲያን ላትቀር ምድረ በዳ የመሰለቻቸው ብዙ ክርስቲያኖች ቢኖሩም እግዚአብሔር ግን ሕዝቡን እንደሚይጥል ማሰብ ይገባቸዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ብቻ ሳይሆን ከፍርሃትም ሊያድነን ተወልዷል።

በራእይ ላይ ተደጋጋሚ የሆኑ ስህተቶች የሚገጥሙን ጊዜ ብዙ ነው። ካለንበት ቦታ፣ ከቀድሞ አድራሻችን መራቅ እያቃተን የምንዞርበት ጊዜ ጥቂት አይደለም። የምንኖርበት ከተማ መንገዱ

አልታይ እያለን በረሃ የምንዞርበት ዓመታት ብዙ ናቸው። ሰዎች ስለነቀፋት ሳይሆን ራሳችን የምንነቅፈው የራሳችን ባሕርይ አለ። ከዚህ ማንነት መቼ ነው የምላቀቀው? ከድብቅ ልቅሶዬስ መቼ ነው የምድነው? እያልን እንጨነቃለን። እግዚአብሔር ግን ከራሳችንም አድኖ መንገዱን ያሳየናል።

7- <u>በባሕር ፍርሃት</u>

የዚህ ዓለም መንገደኞች የብሱን ብቻ ሳይሆን ባሕሩንም ማቋረጥ አለባቸው። ዓለም የብስ ብቻ አይደለችምና። ባሕር በእግር የማይረገጥ በመርከብ የሚረገጥ ነው። ጳውሎስ በባሕር ላይ መርከቡ እየተሰበረ ብዙ ቀን ኖረ። ትልልቅ መርከቦችን ሳይቀር የሚያናውጥና አቅጣጫ የሚያስቀይር ደግሞም የሚያዳፍን ማዕበል አለ። መርከቦች በባሕር ላይ ማዕበሉ ያዳፍናቸዋል፣ ይሰብራቸዋል፣ ያሰጥማቸዋል። ማዕበል ሁሉ ግን ቢሰብርና ቢያዳፍን አንድ መርከብ በባሕር ላይ ባልታየ ነበር። ማዕበሉ ሲመጣ አቅጣጫ በመለወጥ፣ ሞልሕቅን በጽኑ ዓለት ላይ በመጣል፣ ወራቱን በማጤን ይድናሉ።

ዓለም ባሕር ናት። ባሕር የረጋ እንዳልሆነ ዓለምም ብዙ ነውጥ አለባት። በየዕለቱ የምንሰማው ዜና የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ እንደ በዛ ነው። በዚህ ሁሉ በፍርሃት የምንናጥበት ጊዜ ብዙ ነው። እምነት መልሕቃችንን ዓለት በሆነው ክርስቶስ ላይ በመጣል ይህን ኃላፊ ዓለም ማለፍ ያስፈልገናል። ማዕበል ባያልፍ የሚቆም ዛፍ፣ የሚኖር ቤት ባልኖረ ነበር። ለሚያልፍ ማዕበል የማያልፈውን እምነት እንዳንተው መጠንቀቅ አለብን።

በራእይ ላይም ወደኋላ እንዳንመለስ ያባከነው ጉልበት እየቆጨን፣ ወደፊት እንዳንል ማዕበል እያወከን የምንጨነቅበት ጊዜ ብዙ ነው። የጅማሬ አምላክ፣ የፍጻሜ አምላክም ነውና ልባችንን ማበርታት ይገባናል።

8- <u>በውሸተኛ ወንድሞች በኩል ፍርሃት</u>

ሐሰተኛ ወንድሞች የሚባሉት በክርስቲያኖች መካከል መለያየትንና ኑፋቄን የሚዘሩ ናቸው። እነዚህ ወገኖች የሐዋርያትን እግር እየተከተሉ ስህተትን የሚያስተምሩ፣ ልዩ ልዩ ወንጌልና የፈጠራ ተረቶችን የሚያስተምሩ ናቸው። ጳውሎስ እነዚህ ሰዎች የወንጌሉን ንጹሕ ዘር እምነት በሚመስል ተረት እንዳይበርዙት ይጨነቅ ነበር። አገልጋይ መሆን እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ነገር ግን

የሁልጊዜ ምጥ አለው። አንድ ልከኛ አገልጋይ ከእናት በላይ ያስባል። እናት ለልጇ ከምታስበው በላይ አገልጋይ ያስባል። እናት ለልጇ ለሥጋው ታስባለች። አገልጋይ ግን ለነፍስ ያስባል።

አገልጋዮች ሆነን ለምናገለግላቸው ብዙ ፍርሃቶችን እናስተናግዳለን። ነገር ግን በእውነተኛው የቃሉ መሠረት ላይ ከመሠረትናቸው፣ ተገቢውን የማነጽ አገልግሎት ካደረግንላቸው፣ ጉብኝታችንን ካላቋረጥን መፍራት የለብንም። ማላደግ የእግዚአብሔር ነውና።

በራእይ ላይ ከሚገጥሙን ፍርሃቶች አንዱ አጠገባችን ሆነው እያየናቸው ነገ ቢሄዱስ የምንላቸው ስሱቶቻችን የሆኑ ሰዎች ናቸው። የራእያችን የመጨረሻው ግብ ሰዎችን የእኛ አፍቃሪ ማድረግ አይደለም። ስለዚህ ሰዎቹ እውነቱን ይረዱት እንጂ የሰማነውን በኑሮአችን እናጣጥም እንሂድ ካሉ በደስታ ልንለቃቸው ይገባል እንጂ መፍራትና መታወክ አይገባንም። ተመላላሽ ከሆኑ ሰዎች ጋር ሕይወታችንን ማስተሳሰር አይገባንም። በምንም ነውር መተሳሰር የለብንም። በሕይወት እንዲማሩ መፍቀድ አለብን። የራእይ ኃይል የሚሆነው ፈቃድ እንጂ ማስገደጃ አይደለም። ብዙ ባለ ራእይ ነን የሚሉ ሰዎች የሰዎችን የነውር መረጃ በመያዝ አብረዋቸው እንዲኖሩ ያደርጋሉ። ይህ ግን የፖለቲካ እንጂ የራእይ መስመር አይደለምና ከዚህ መራቅ ይገባናል። ስለ እኛ ቢናገር የሚያምርበት እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሁሉም ደካማ መሆኑን እርሱ ያውቃል።

ጳውሎስ ብዙ ፍርሃቶች የከበቡት ሰው ነበር። በዚህ ሁሉ ፍርሃቶች ውስጥ ያሳስበው የነበረው የማጎበረ ምእመናን ህልውና ነበር። በራእይ ላይም ከጉዳታችን ይልቅ የምንደርስላቸው ወገኖቻችን ሊያሳስቡን ይገባል።

ተቃዋሚዎቻችን በጣም እየተጋጋሉ እንደ ሰደድ እሳት ብዙ አላዋቂዎችን ሊያስከትቱብን ይችላሉ። ተቃዋሚዎቻችን ክፋታቸውን ከቢሮ ወደ አደባባይ፣ ከቡድን ወደ አገር ያወጡታል። የዘመናት ናፍቆታቸው የሆነው በእኛ መቃብር ላይ ውስኪ ለመራጨት አሁን ሊያጠፉን ይነሣሉ። የዐባይ እንባ እንዲሉ ያለቅሳሉ፣ ሰዎችን ለማሳመን ድራማውን ሁሉ ይሠራሉ። ሐሰተኛ መረጃዎችን፣ የሃይማኖትና የምግባር ሕፀፅ የሚሉትን በክስ መልክ ያቀርቡብናል። ጎሊናቸውን የሸጡ ሰዎችንም ምስክር አድርገው ያስነሡብናል። የአገሩ ርእስ ሆነን ቡና መጠጫ እንሆናለን። መልካችንን፣ ድምጻችንን የማይለዩ ለእኛው የእኛን ማንነት ይነግሩናል። ፍሬኑ

እንደተበጠሰ መኪና የሚሄደውን ወሬ ማቆም እስኪያቅተን እንገረማለን። ጠላቶቻችን ሰይጣንን ያገለገሉትን ያህል ለክፋት እንቅልፍ ያጡትን ያህል እኛ መትጋት ባለመቻላችን ራሳችንን እንታዘበዋለን። አንዳንዱም የሠራነው አልታይ እያለን ጠላቴ ራሳዬን ነው የሚፈራው እስከማለት እንደርሳለን። ራእይ በነበረ ዘመን ሁሉ ተቃዋሚዎች ነበሩ። ራእይን ያለ ተቃዋሚዎች ማግኘት ከባድ ነው።

ተቃዋሚዎች በራሳቸው ጠቃሚ ናቸው። ጳውሎስ፡- *«ሥራ የምላበት ትልቅ በር ተከፍቶልኛልና ተቃዋሚዎችም ብዙ ናቸው»* (1ቆሮ. 16፥9) ብሏል። ተቃዋሚ እንዲሁ አይቃወምም፣ ያየውን አይቶ የሚቃወም ነው። ተቃዋሚ ከእኛ ይልቅ የእኛ መድረሻ ይታየዋል። መንገዳችንን ሊያሰናክልም በብርቱ ጩኸት ይወጣል። ሞት የማይገድበውን ራእይ ግን ጩኸት ይገድበዋል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው። የእኛን ራእይ ሁሉም ሰው የሰማው ወይም የሚቃወመው የሚመስለን ጊዜ ብዙ ነው። ራእያችንን ያልሰሙ በሩቅ ያሉ ሁሉ ከተቃዋሚዎቻችን ጩኸት ይሰማሉ። ስለዚህ ተቀቃዋሚዎቻችን በነጻ ማስታወቂያ ይሠሩልናል ማለት ነው። ተቃዋሚዎቻችን እንደዚህ ይላሉ እያሉ ሲከሱን እንደ እኛ ያለ አስተሳሰብ ያለው ሰው ወዳጄን አገኘሁ ብሎ ካለበት ይወጣል። ቤተ ዘመድን ለማገናኘት እንደ ተቃዋሚ የሚረዳ የለምና ተቃዋሚ መልካም ነው። ተቃዋሚዎች ከበዙ ሰፊ አገልግሎት መጥቷልና ስለ ተቃዋሚው ሳይሆን ስለ አገልግሎቱ ማሰብ አለብን።

ተቃዋሚ ሌላው ጠቀሜታው እንዳንዘናጋ ያደርገናል። ሥራችንንም ደግመን እንድናየውና በጥራት እንድንፈጽመው ይረዳናል። የዛሬ ትውልድ ባይቀበል ቀጣዩ ትውልድ ይቀበላል እያልን ለዐሥር፣ ለሃያ፣ ለመቶ ዓመታት እንድናቅድ ወደፊት ያስከነዱናል። ተቃዋሚዎችን እንደ ጥራት ተቆጣጣሪ መመልከት መልካም ነው። ተቃዋሚዎች በመጨረሻ እውነት ትፈርድባቸዋለች። ቃሉ፡- *«በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ፤ ይህም ለእነርሱ የጥፋት፥ ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው፥ ይህም ከእግዚአብሔር ነው፤ ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤ በእኔ ያያችሁት አሁንም በእኔ እንዳለ የምትሰሙት፣ ያው መጋደል ደርሶባችኋልና»* (ፊልጵ. 1፥28-30) ይላል። ተቃዋሚዎቼን የምረሳበት ሁልጊዜ እየዘመርኩት የምኖረው መዝሙር እንዲህ የሚለው ነው፡-

ከንድህን እጠፍ የሚልህ ማነው?
ማዳንህን ተው የሚልህ ማነው?
ቢከፉቸውም አሳዳጆቼ
እስካሁን አለሁ ባንተ ፀንቼ

ተቃውሞ

ሴትዬዋ አመድ በደፋች ቊጥር «የገብርኤሉንም አለቃ እንዲህ ድፋልኝ» ትላለች። ርግማኗን ሳታቋርጥ ለብዙ ጊዜ አደረገች። አንድ ቀን አመዱን ደፍታ «የገብርኤሉንም አለቃ እንዲህ ድፋልኝ» ብላ ስትመለስ የገብርኤሉ አለቃ ፊት ለፊቷ ቆመው አገኝ ቻቸው። እርሷም ሳታፍር፦ «አባቴ ይህንማ ካልቻሉ ምኑን አለቃ ሆኑት!» አለቻቸው ይባላል።

በራእይ ውስጥም ከሚነሡ የውጭ እንቅፋቶች አንዱ ተቃዋሚ ነው። ዛሬ የኃያላን አገሮች ብሔራዊ ሃይማኖት የሆነችው ወንጌል ብዙ ተቃውሞን ያስተናገደች ናት። በየትኛውም ዘመን እውነትንና ወንጌልን አበባ ይዞ የተቀበለ የለም። አንድ ሊቅ፦ «ወንጌል የትም አገር ስትገባ ጎንበስ ብላ ነው የምትገባው። ከዚያም የቤተ መንግሥት ሃይማኖት ትሆናለች» ብለዋል። ሌሎችን በሚታደገው ራእይ ውስጥ ተቃዋሚ አለ። ተቃውሞውን ካልቻልን ምኑን ባለ ራእይ ሆነው?

ተቃውሞ የከረረ ነቀፋ፣ ግልጽ የሆነ ጥላቻ፣ ከትግል ጋር የሆነ ማሳደድ ነው። ሰው በባሕርይው መቃወም ቢወድም ተቃዋሚዎች ግን ብዙ ጊዜ በመታለል ነው የሚቃወሙት። ጌታችን ስለዚህ ሲናገር፦ *«እንዳትሰናከሉ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። ከምኵራባቸው ያወጡአችኋል፤ ከዚህ በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል»* (ዮሐ. 16÷1-2) ብሏል።

ተቃዋሚዎች በየትኛውም ዘመን ነበሩ፣ ነገር ግን እውነትን ማጥፋት አልቻሉም። የምድር ኃይል ሁሉ በእጃቸው ገብቶ እውነተኞችን ቢያጠፋም እውነት ግን በልጆቿ ሞት እያሸነፈች ዛሬ ላይ ደርሳለች። ከእግዚአብሔር የመጣ ራእይን ማጥፋት አይቻልም። በራሳቸው ጉልበት የተነሡ ሊወድቁና የሚያነሣቸውም ሊያጡ ይችላሉ። እግዚአብሔር ያስነሣውን ግን ማንም አይጥለውም። የብሉይ ኪዳን አዋቂና የጳውሎስ መምህር የነበረው ታላቁ ገማልያል ስለ ጌታችን ደቀ መዛሙርት ለተቃዋሚዎች ሲናገር፦ *«ይህ ሰብ ወይም ይህ ሥራ ከሰው እንደሆነ ይጠፋልና፤ ከእግዚአብሔር እንደ*

ሆነ ግን ታጠፉአቸው ዘንድ አይቻላችሁም፥ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ» (የሐዋ.ሥራ 5÷38-39) ያለው ለዚህ ነው። «የሻማን እሳት የሚያጠፋ ነፋስ፣ የችቦን እሳት ግን ይበልጥ ያቀጣጥለዋል።» ተቃውሞ ስሜትን ሊያጠፋ ይችላል፣ ራእይን ግን ይበልጥ ያቀጣጥለዋል። በኮሚኒስት ሥርዓት በብዙ መከራ ክርስትናቸውን እንዲጥሉ የተገደዱ ክርስቲያኖች ነበሩ። ግን በቆራጥነት ተገኝተዋል። ኮሚኒስቶች ራሳቸው፦ «ክርስቲያንና ምስማር በተመታ ቊጥር ይጠብቃል» ብለው እስኪመስክሩ ክርስቲያኖች በጽናት ቆመዋል። ሰው አቅም ጨምሮ የሚቆመው ሲገፈተር ነው።

ሞት ለባለ ራእዩ መጨረሻ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ ረድም ዘመን በምድር ላይ መቆየት አልወደደም። በወጣትነት ዘመኑ ሞተ። በሕይወቱ ካዳናቸው ግን በሞቱ ያዳናቸው ይበልጣሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሶምሶን ሲናገር፦ *«ለምቱም የገደላቸው ሙታን ለሕይወት ሳለ ከገደላቸው በዙ»* (መሳ. 16÷30) ይላል። የትምህርታችን ከሚሳቡት በጽናታችን የሚሳቡትን ማንም እይነቀንቃቸውም። በዓላውያን ነገሥታት አደባባይ ክርስቲያኖች ፈሰየፉ ብዙ ሕዝብ እንዲፈራ ትርኢቱን ይመለከት ነበር። ነገር ግን ለሰማዕታቱ ጽናት ያ ሁሉ ሕዝብ ክርስትና እውነት ነው ብሎ ኒመሰክር ተይዞ ይታረድ ነበር። ከሚገድሉት ነገሥታት አልክድም ብሎ የተገደለው ክርስቲያን ድል አደረገ ይባል ነበር። ግን ሞቷል። ድል መኖር ሳይሆን በጽናት ማለፍም ነው። ስለዚህ ባለ ራእዩ ወደ ሞት እንኳ ቢቃረብ ትልቅ ሥራ ያለው ከእርሱ ሞት በኋላ መሆኑን ማመን አለበት። ይህ በዘመናት ሁሉ ያለ የእግዚአብሔር አሠራር ነው።

ዛሬም ብዙ የሚገፉ የቤተ ክርስቲያን ልጆችን ስናይ ቢያጠፉ እንኳ መመከር የለባቸውም ወይ? ከሳሽ ዳኛ ሆኖ እንዴት ይቀጣቸዋል? ብለን ልንጠይቅ ይገባናል። የምንወዳቸው ሲያጠፉ እያለፍን የማንወዳቸውን ሰዎች ስህተት ማጉላት እውነተኛ አያሰኝ ንም። እውነት ፊት አይታ አታደላምና። ደግሞም የራሳችን ምስሰ ኃጢአት አልታይ እያለን የሌሎችን ጉድፍ ማጋነናችን ተገቢ አይደለም። የሚብስ ስህተት እኛ ጋ አለ። ሌሎች እግዚአብሔርን ከበደሉት ይልቅ እኛ በድለነዋል። በጥላቻ፣ በቂም በቀላችን፣ በዝሙት በሐሜት ርኩሰታችን፣ በአስማት ጥንቆላችን ብዙዎችን ሳድተናል። ወገናችንን ሌሎች ከጎዱት ይልቅ እኛ የጎዳነው ይበልጣል። በእኛው እጅ ይሙት ካላልን በቀር እኛም ሕይወት የሚሰጠውን ነገር አላቀረብንለትም። ስለዚህ ቤታችንን መፈተሽ አለብን። በአሜሪካ አገር አንድ ሰባኪ «ቴሌቪዥን ማየት ኃጢአት

ነው፣ ስለዚህ በቤታችሁ ያለውን ቴሌቪዥን አስወግዱ» ብሎ ሰብክ ስለነበር ተከታዮቹ ወደየቤታቸው ሲመለሱ በሽጉጥ ጥይት ቴሌቪዥናቸውን ሰባበሩ። በቤታቸው ውስጥ ከቴሌቪዥን የሚበልጥ ኃጢአት ነበር። ዛሬም በስህተት ሊፈረድ ባለመቻሉ ስህተት ባልሆነው እየተፈረደ ይገኛል። ባለ ራእዩ ግን በዚህ ተቃውሞና ቲያትር መደነቅ የለበትም። የከሳሾች ክስና «ይሙት በቃ» ፍርዳቸውም ሊያስደነግጠው አይገባም። «በጅቦች ጉባዔ ለአህያ አይፈረድምና!» ባለ ራእዩ ሞትንም እንደ መጨረሻ መቊጠር የለበትም። መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ እስራኤልን አገለገለ፤ በሞቱ ዓለምን አዳነ። ሰባለ ራእዩ ሞት የሥራው መጀመሪያ ነው። ካልሞተ እንደማይኖር ባለ ራእዩ ሊያስብ ይገባዋል። ደግሞም ዮሐንስ አፈ ወርቅ፡- «ለምድር ሩቅ ለሰማይ ቅርብ ነን» ያለውን እያሰበ ባለ ራእዩ በመገፋቱ ሊደሰት ይገባዋል። ሰው ያለ አገሩ አይከብርምና ባለ ራእዩ አገሩ ሳይደርስ ክብርን መጠበቅ የለበትም። በዚህ ዓለም የሚከበሩ አገራቸው እዚሁ ነው። የባለ ራእይ አገሩ ግን በሰማይ ነው። ደግሞም ክፋዎች ደኅኖን የሚጠሉት ክፋታቸውን ይበልጥ ያጎሉባቸው ስለሚመስላቸው መሆኑንም ባለ ራእዩ መዘንጋት የለበትም።

ከሃይማኖት ሰዎች የሚነሣው ተቃውሞ ብቻ አይደለም። የእነርሱ ባልሆነ ጠብ የሚጣሉን፣ የሚያኮርፉንና የሚያሳድዱንም አሉ። የቅርብ ወዳጆቻችንም አንድ አንድ እያሉ ይሄዳሉ። ነገር ግን ከአጉል መብዛት የተባረከ መቀነስ ጥሩ ነው። መከራ እንደውም ራእይን ያግዛል። አስመሳዮችን አርቆ ጥርት ያሉ ሰዎችን ያስቀራል። በኮሚኒዝም ርእዮተ ዓለም ምክንያት በሩማንያ በነበረው አስከፊ የስደት ዓመታት ብዙ መብዛትና ብዙ መጉደሎች ተፈራርቀው ነበር። በአንድ ወቅት ታጣቂዎች ወደ አንድ የአምልኮ ስፍራ ገቡ። «በክርስቶስ አናምንም የምትሉ በሰላም መሄድ ትችላላችሁ» ሲሉ ግማሽ ያህሉ ወጥቶ ሄደ። ታጣቂዎቹም ለቀሩት ክርስቲያኖች፡- «እኛም እንደ እናንተ ክርስቲያኖች ነን፥ አሁን ማምለክ እንችላለን፣ ከወላዋዮች ጋር ግን ማምለክ ስለማንፈልግ ነው ያስወጣናቸው» አሉ። አዎ መከራ ለራእዩ ጥራት ይሰጣል።

ወላዋዮች ብቻ ሳይሆን ዓላማችን ሳይገባቸው የሚደግፉንም ከተቃዋሚዎች በላይ አስደንጋጭ ናቸው። ዓላማ የሌላቸው ሰዎች የጠላት የውስጥ አምባሳደሮችና የማንጠነቀቃቸው ሰባሪዎቻችን ናቸው። ሽባ እግር ለጤነኛው ሽክምና ጫና እንደ ሆነ ዓላማ የለሾችም ለራእይ ሽክም ናቸው። ሮማውያን በውጊያ ካሸነፉ በኋላ ምርኮኞች እንዳያመልጡ የሞተ ሬሳ አሸክመው ይነዷቸው ነበር ይባላል። ዓላማ የለሾችም ለራእይ የሬሳ ሸክም ናቸው። ባልገባው ነገር የሚደግፈን፣ ባልገባው ነገር ከሚቃወመን ብዙም አይለይም።

አንዳንድ ጊዜ ራእያችን በቤተ ዘመድ ቡድን ይያዛል። እኛን የሚወዱ ሰዎችም ስለ እኛ ራእያችንን ተቀብሰውት ይጓዛሉ። ይህ ወዳጅነት ክፉ ቀንን የማይሸገር ከመሆኑም በላይ ክፉ ቀንን ቢጋፈጥ እንኳ ክብር የለውም።

የወንጌል ፀሐይ በተቃዋሚዎች ብዛት አትጠልቅምና በዚህ ሁሉ መፍራትና መደንገጥ አይገባንም። ድል የክርስቲያን፣ ድል የእግዚአብሔር፣ ድል የባለ ራእይ ነው። ኮሚኒዝም መፈክር ሰውን እንደሚያነሣሣ ስለተረዳ በመፈክር ነበር ሰውን የገዛው። እኛም በራእያችን የምንፈክረው መለኮታዊ መፈክር ያስፈልገናል። መጽሐፍ ቅዱስ ለባለ ራእዮች የሚሆን የድል ቃል ተሞልቷል።

«አትፍሩ፥ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን ለዘላለም አታዩአቸውምና ቁሙ፥ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ። እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል፥ እናንተም ዝም ትላላችሁ» (ዘጸ. 14፥13-14)።

«እግዚአብሔር ተዋጊ ነው፥ ስሙ እግዚአብሔር ነው» (ዘጸ. 15፥3)።

«በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም ሊይቋቋምህም፤ ከሙሴ ጋር እንደሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ አልጥልህም፥ አልተውህም » (ኢያ. 1፥5)።

«የእግዚአብሔርና የጌዴዎን ሰይፍ ብለው ጮኹ» (መሳ. 7፥20)።

«ለዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን» (ሮሜ. 8፥37)።

እናስተውል

- ድንቅ ስንናገር ከወጣው በላይ ፍርድ አጥተን ስንሰቀል የበለጠ ሕዝብ ይወጣል።
- እውነተኛ ባለ ራእይ በወርቁ ሳይሆን በጠባሳው ይመካል። የእውነተኛ ባለ ራእይ ምልክቱ ዘውድ ሳይሆን የእሾህ አክሊል ነው።

- ክርስቲያን ሊሰደድ ሲገባ አሳዳጅ ከሆነ፣ ሊሞት ሲገባ ገዳይ ከሆነ፣ መስቀል መሸከም ሲገባው መስቀል አሸካሚ ከሆነ በጣም ያሳዝናል።
- ለፍርሃት ከሸሹለት ግን ይገናል እንጂ አይበርድም።
- የማይሄደውን ጌታ ካልያዝን የዚህ ዓለም ነገር ከፍርሃት አያድንም።
- የራእይ ኃይል የሚሆነው ፈቃድ እንጂ ማስገደጃ አይደለም።
- ራእያችንን ያልሰሙ በሩቅ ያሉ ሁሉ ከተቃዋሚዎቻችን ጨኸት ይሰማሉ። ስለዚህ ተቀቃዋሚዎቻችን በነጻ ማስታወቂያ ይሠሩልናል ማለት ነው።
- ተቃዋሚዎች በየትኛውም ዘመን ነበሩ፣ ነገር ግን እውነትን ማጥፋት አልቻሉም።
- ተቃውሞ ስሜትን ሊያጠፋ ይችላል፣ ራእይን ግን ይበልጥ ያቀጣጥለዋል።

ምዕራፍ ሃያ አምስት

መገፋት

ማርና ቅቤ ተከራከሩ ይባላል። ታዲያ ማር ቅቤን እንዲህ ብላ ጠየቀቻት፦ «የምጣፍጠው እኔ፣ ሰዎች ግን ራስ ላይ የሚያስቀምጡት አንቺን ነው፤ ምክንያቱ ምንድነው?» አለቻት። ቅቤም ስትመልስ፦ «እኔም ራስ ላይ የወጣሁት ወድጄ አይደለም፣ ሰዎች ገፍተው ገፍተው ነው ራስ ላይ ያወጡኝ» አለች ይባላል። ውተት ተንጦ ተንጦ አይደል ቅቤ የሚወጣው?

በተፈጥሮአችን እንድንረካ የታዘዝነውን ነገር አንረካበትም። የዕለት ጉርስ፣ የዓመት ልብስ ካለን እንዲበቃን ብንታዘዝም በስግብግብነት ገና እንኖራለን (1ጢሞ. 6፥6-10)። የሰውን ድንበር ገፊ፣ የእግዚአብሔርን አምልኮ አፍራሽ በመሆን ሰላም እናጣለን። እንዳንረካ የታዘዝነውን ነገር ደግሞ በቃኝ ብለን፣ በሠራነው አንድ መልካም ነገር ዘመናችንን በሙሉ ስንኩራራ እንኖራለን። በአንድ መልካም ነገር እንድንረካ፣ እንደ ዐፄ ቴዎድሮስ መድፍ አንድ ጊዜ ተሰምተን ፀጥ እንድንል አልተፈጠርንም። መድፉ የሰው ምኞትና ሥራ ነውና ፀጥ ይበል፣ እኛ ግን መልካምነቱ የማያልቀው የዘወትር ቸር የሆነው የእግዚአብሔር እቅዶች ነንና በአንዱ ፀጥ ልንል አይገባንም።

ያለንበት ቦታ፣ የያዝነው እውቀትና የሠራነው ምግባረ ሠናይ ሞቆን እርሱን እየተረከን፣ በአዝማሪ እርሱን እያስወደስን ለመኖር የምንወስንበት ጊዜ ብዙ ነው። እንደ ኪሎ ሜትር ድንጋይ ሁልጊዜ ሠላሳ ወይም ሃያ አያልን ባለንበት ቦታ፣ በአንድ ዜማ ዘመናችንን ለመፈጸም እንጨክናለን። እግዚአብሔር ግን በሰበር ገብቶ፣ እየሞትን ለመኖር ያቀድነውን የመቃብር ኪዳን አፍርሶ፣ በአንድ ቦታ ረግተን ለመበስበስ ያቀድነውን ኑሮ አስክዶን የበለጠ ይሠራብናል። *«ከዚህ የሚበልጥ ነገር ታያለህ»* (ዮሐ. 1፥51) ይለናል። ከኃይል ወደ ድካም ሳይሆን ከኃይል ወደ ኃይል የሕግ መምህር ያሻግረናል (መዝ. 83/84/፥7)። ካለንበት የሞቅታ ዓለምም ይገፋናል። መገፋት አይመችም፣ ክብርንም የጠበቀ አይደለም። እግዚአብሔር ግን ካሰበልን ቦታ የሚያደርሰን እየገፋን ነው። እኛ በማንገምታቸው፣ አንዳንዴም በክፉዎችም እየተጠቀመ ወደ በረከታችን ምድር ያደርሰናል። ፈርዖን ባያስጨንቃቸው እስራኤል የደለበ ባሪያ ለመሆን ተዘጋጅተው ነበር። እግዚአብሔር በማስጨነቅ

ወደ ነጻነታቸው ምድር መራቸው። ፈርዖንንም፦ *«ነገር ግን ኃይሌን አገልጥብህ ዘንድ ስሜም በምድር ሁሉ ላይ ይነገር ዘንድ ስለዚህ አስነሥቼሃለሁ»* ብሎታል (ዘፀ. 9÷16)።

በዘመናት ሁሉ ገፌ እንደሚያጠነክር አይተናል። መሬት ላይ ተክለን የምንቆመው ስንገፋ ነው። ያላየነውንም ዓለም የምናየው ስንገፋ ነው። ያለንበት የደስታ ዳርቻ መስሎን እንታለላለን። «ዐይጥ ከጮራዋ ውጭ ዓለም ያለ አይመስላትም» እንዲሉ እኛም እግዚአብሔርንና መልካምነታችንን ባለንበት ቦታ ወስነን ስንኖር እግዚአብሔር ገፍቶ ዓለም ያሳየናል። ገፌዎች አሳራፊ እንደሆኑ አይተናል። ከስፍራ ሲገፉን ወደ ተሻለ ስፍራ፣ ከምድር ሲገፉን ወደ መንግሥተ ሥላሴ ያስገቡናል።

ከተደበቅንበት የሚያወጡን፣ ከመርጋትና ከመሸተት አውጥተው እንደ ወንዝ ያለ ድንበር እንድንፈስስ የሚያደርጉን ገፌዎች ናቸው። ከማንም ላለመነካካት ያስቀመጥነውን የድንበር ድንጋይ በማንሣት ገፌዎች ይነኩናል። እኛም ሌሎችን በበረከት እጅ እንድንነካ፣ ለካ እንደ እኔ ፍርድ የጐደለባቸው አሉ ብለን ሰፍትሕ እንድንጮህ፣ የዓይን ቀለማቸው እየታየ የተጠሉ ሰዎችን እንደገና እንድናስባቸውና ወገን እንድናደርጋቸው ያደርጉናል። «የተኛውን በሬ ቆስቁሰው ቆስቁሰው አደረጉት አውሬ» እንዲሉ።

እግዚአብሔር እንደ ጳውሎስ አይሥራባቸው እንጂ እንደ ፈርዖን የሚሠራባቸው ገፌዎች ዛሬም አሉ። የሚነቀፍ ክፉ ያለቀባቸው ይመስል መልካምን የሚነቅፉ፣ ስንት ቀማኛና ጣየት አምላኪ ባለበት ምድር ወንጌል የያዘውን የሚገፉ፣ የዝሙት ጽሑፎችን እየታገሡ የማጽናናት መጻሕፍትን የሚያወግዙ፣ ዘፈንን የባሕልና የዘመናዊ እያሉ ጣፋጭ ለማድረግ የሚጨነቁ መዝሙርን ግን እንደ ሜልኮል የሚተቹ፣ ጨለማን አይቶ እንደሚወጣ አውሬ በአደባባይ የወጡ ብዙዎች ናቸው። ሰባኪው ብዙ እንዲሰብክ፣ ደራሲው ብዙ እንዲጽፍ እነዚህም ያስፈልጋሉና ደስ ሊለን ይገባል። የፈራው እንዲደፍር፣ ወገን አልባ የነበረው ወንድሙን እንዲተዋወቅ፣ የሚሸቃቅጠው የሐቅ ደቀ መዝሙር እንዲሆን ያደርጉታልና ገፌዎች አስፈላጊ ናቸው። ገፌዎች ስለማሩት እውነትን የጣለው ሰው፣ ሲገፉት እውነትን በውድ ዋጋ ይገዛታል። ነጻነትን ለመጠበቅና ነጻነትን ለመጐናፀፍ የሚደረገው ውጊያ ልዩነት አለው። ነጻነትን ለመጠበቅ አባቶቻችን በአንድ ቀን አድዋ ላይ ባለ ድል ሆኑ። ነጻነትን ለመጐናፀፍ ደቡብ አፍሪካውያን አራት መቶ

* «የአባ ደባደቦ ስልቻ ጤፍ ይቋጥራል፣ ባቄላ ያፈሳል!»

ዓመት ዳከሩ። የገፌዎችን ወዳጅነት ፈልጎ፣ ሰይጣን ወዳጅ የሚሆን መስሎት አውነትን የጣለ እንደገና አውነትን በውድ ዋጋ ገንዘቡ ያደርጋታል። አንድ ቀን መዋጋትና አራት መቶ ዓመት መዋጋት ማለት ይህ ነው።

ገፌዎች ሲገፉን ወደታች እያወረዱን እንደሆነ እያሰቡ ደስ ይላቸዋል፣ እኛም እናዝናለን። መግፋት ሲያቆሙ ግን በከፍታ ላይ ያገኙንና ለእነርሱ ትካዜ ለእኛ ዝማሬ ይሆናል። ገፌዎች አይገባችሁም ካሉን ስፍራ በላይ ስንገን፣ ኃላፊያቸው ሆነን በበላይ ስንመጣ ለሁሉም ድንቅ ሆኖ ሲተረክ ይኖራል። እግዚአብሔር ኃይሉንና ጥበቡን ሊያሳየን ገፌዎችን ቢያስነሣም የግብሩን ማዕረግ ግን በመጨረሻ ስናይ ደስ ይለናል። ክርስቲያን ግን ሁለት ደስታ ተመድቦለታል። ከመሆኑ በፊት በተስፋ፣ ከሆነ በኋላ በእምነት እንዲደሰት ከላይ ተፈቅዶለታልና ደስ ይበላችሁ! ክፉው ነገር መግፋት እንጂ መገፋት አይደለምና የተገፋችሁ ወደ ምድረ በረከት እየገባችሁ ነውና ደስ ይበላችሁ! ከዚህ በረሃ ቀጥሎ ማርና ወተት የምታፈሰውን ምድር ታያላችሁ!

ስማቸው የማይታወቅ የነበሩት ገናና የሆኑት ጣልን በሚሉ ገፌዎች ነው። ብቸኛ የነበሩት ብዙ ወዳጅ ያገኙት፣ እንደ ሙታን የተረሱት እንደገና ጉብኚ ያገኙት በገፌዎች ነውና እጅግ ደስ ሊለን ይገባል። እግዚአብሔር የሚሠራበትን ሰው ገፌዎች ይተነኪሉታል። ለበረከቱ እንዳይተኛም ሳያውቁ ያነቁታል። ስሙ የማይታወቀውን ርእሳቸው አድርገው ያሳውቁታል። እገሌ እንዲህ ነው እያሉ ሲያወሩ ቀድሞ የእነዚህን ገፌዎች በትር የቀመሱ ትልልቅ ሰዎች የታለ እያሉ ያን ሰው ይፈልጉታል። ገፌዎች ከጎዱት የጠቀሙት ይበዛል። ካፈረሱት ጎብረት ያቋቋሙትና ያጠናከሩት እንደሚበልጥ በዕድሜያችን አይተናል። ሁሉ መሣሪያው የሆነ፣ በበለዓም አህያ የሚናገር፣ በቢታንያ ድንጋዮች የሚዘመርለት ጌታ ስሙ ቡሩክ ይሁን!

አሞ እንደ ማር የጣፈጡ፣ ንግግር አዋቂዎች፣ መልከ - ቀናዎች ራስ ላይ አልወጡም። እንደ ቅቤ የተገፉ ግን ራስ ላይ ወጥተዋል። ይህን ስፍራ ለራሳቸው እንኳ አልተመኙትም። ጠላት ግን ገፍቶ ገፍቶ፣ ይገባችኋል ብሎ አደረሳቸው። ገጣሚው እንዲህ ብሏል፦

«መገፋት ጥሩ ነው እጅግም ሳይወድቁ፣
የተገፉት ቆመው የገፉት ወደቁ!»

ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ የዙፋን ዕንባ ጠባቂ ነበሩ ይባላል። ታዲያ መኳንንቱና መሳፍንቱ አቤቱታውን እየያዘ ወደ እርሳቸው ይቀርብ ነበር። አንድ ቀንም አንዱ መስፍን ወደ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ በመምጣት፦ «ተገፍቻለሁ፣ እነ እገሌ ገፍተውኛል የሚገባኝን ሹመት ተነፍጌአለሁ» አላቸው። እርሳቸውም ካዳመጡት በኋላ፦ «በትገፋማ ታድግ ነበር ልክስክስ ገፊ ነው የገፋህ» አሉት ይባላል። ገፊ እንደሚያሳድግ ከጥንት ጀምሮ ተፈትኖ የተረጋገጠ ነው።

ከመናብርትና ከሥልጣናት በላይ የገነነው ክርስቶስ በሰው የተጣለና የተገፋ ነበር (1ጴጥ. 2÷6-8)።

እኛ ምን እንደምንሆን ራሳችንን ከምናውቀው ይልቅ ጠላት በደንብ ያውቀዋል። ስለዚህ ፍጻሜአችን ላይ እንዳንደርስ መሰናክል ያበዛብናል። ቢሆንም የእንቅፋት ብዛት እግዚአብሔር ካሰበልን ነገር አያስቀረንም። የሞቱ ሰዎች ጠላት የለባቸውም ሞተዋልና። በሕይወት ያሉት ግን ጠላት አለባቸው። ሰዎች ጠላት ሲበዛባቸው የተናቁ ቢመስላቸውም በተቃራኒው ግን ተፈርተዋል።

ወጣቱ ዮሴፍን የገጠመው እንደዚህ ነበር። ወንድሞቹ ቢሸጡት የግብፅ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነ። ገፍተው፣ ገፍተው ዙፋን ላይ አወጡት። ሳያውቁት ቦታህ እዚህ አይደለም፣ የራእይህን ፍቺ ውረስ እያሉት ነበር። ባይሸጡት ግን የፍልስጤም ምድር በግ ጠባቂ ሆኖ በቀረ ነበር። እግዚአብሔር ግን ክፉ በሚመስለው በክፉዎች ተግባር ውስጥ የእርሱን መልካምነት ይሠራል። ራሱ ዮሴፍ እንደ መሰከረው፦ *«እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ፣ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው»* (ዘፍ. 50÷20)። በራእይ ውስጥም የሚደርስብን መገፋት ለመጥፋት ሳይሆን ለማፍራት የሚረዳን በመሆኑ ደስ ሊለን ይገባል። ሰው የወደደው እግዚአብሔር የወደደው ከሚለው ተረት ወጥተን ብዙ ሰው የጠላቸው እግዚአብሔር የተቀበላቸው መሆናቸውን በማስተዋል በመገፋታችን ግር ልንሰኝ አይገባም። የገፊዎችን ጠቃሚነት ከበደ ሚካኤል ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፦

ሰው ሲበድላቸሁ እስኪ አትናደዱ
ጠላትን አትጥሉ ክፉን ሰው ውደዱ
የክፉ ሰው ክፋት ጠቃሚ ነው ትርፉ
ያነቃቃችኋል እንዳታንቀላፉ

የጠላት ጊዜያዊ ድል

ተቃዋሚ የሚጠበቅ በመሆኑ የምንደነቅበት አይደለም። ካልጠበቅን ግን እንኳን ክፉ ነገር መልካሙም ነገር ያስደነግጠናል። እንቅፋት ነቃፊና ተቃዋሚ ብቻ አይደለም። የጠላት ጊዜያዊ ድልም አንዱ ልብ የሚያዝል እንቅፋት ነው። የዕብራውያን መልእክት ፀሐፊ ስለ መልከ ጼዴቅ ክህነት ሲናገር፦ *«በማያልፍ ሕይወት ኃይል»* (ዕብ. 7÷15) መሾሙን ይናገራል። የመልከ ጼዴቅ ክህነት የክርስቶስ ክህነት ምሳሌ ነው። ይህም ክህነት ከአሮን ክህነት የበለጠው፦ *«በማያልፍ ሕይወትና ኃይል»* የገነነ በመሆኑ ነው። የአሮን ክህነት ግን በተቃራኒው «በሚያልፍ ሕይወት ኃይል» የተዋቀረ ነበረ። አሮናውያን በ25 ዓመታቸው ወደ ክህነት አገልግሎት ይመጣሉ። በ55 ዓመት ገደማ አገልግሎታቸውን ይፈጽማሉ። ከዚያ በፊትም በሞት አገልግሎታቸው ሊቋረጥ ይችላል። በክህነት ልብሳቸው፣ በታላቅ ክብራቸው፣ በልዑል ቃላቸው ሲታዩ የሚደክሙ አይመስሉም ነበር። ነገር ግን የሚያልፍ ሕይወትና ኃይል ነበር።

እንዲሁም በራእያችን ትይዩ ቆመው የሚያሳድዱን ሰዎች ሕልውናቸው የማያልፍና ኃይላቸው የማይደክም ይመስላል። ነገር ግን እግዚአብሔር ክንድ ያልሆነለት የደካሞች ደካማ ነው። አሳዳጆቻችን ከንስር ሊፈጥኑ፣ ከአገር ከመንደሩ መድረሻ ሊያሳጡን፣ ሁሉ ሊሰማቸውና ሊከተላቸው፣ ዝናቸውና አስፈሪነታቸው ልክ ናቸው ሊያሰኛቸው ይችላል። እኛም ከዚህ ሕይወትና ኃይል የተነሣ ልንደነግጥ ራእያችንን ለመተው ሊዳዳን እንችላለን። ግን የሚያልፍ ሕይወትና ኃይል ነው። በመልከ ጼዴቅ ሹመት የዘላለም ካህን የሆነው የሚረዳን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በማያልፍ ሕይወትና ኃይል የሚኖር ነው።

አይሁድ ክርስቶስን የገደሉት ለሕጋቸው ቀንተው ቢመስልም ነገር ግን የገዛ ሕጋቸው ይቃወማቸው ነበር። እነርሱ ግን ቅንዓታቸውን ወደ ሃይማኖት አጠጋጉት። በሐሰት መመስከር ኃጢአት ሲሆን እግዚአብሔርን የኃጢአት ተባባሪ አድርጎ መቍጠር የበለጠ ኃጢአት ነው። እነዚህ አይሁዶች ክርስቶስን የጠሉት፦

1. ትምህርቱ ቀና፣ ሕይወቱ የተሟላ ስለነበር፣ ቅንነቱ ጠማማነታቸውን፣ ፍቅሩ ራስ ወዳድነታቸውን ስላጋለጠባቸው ነው።

2. የሚሰብከው የመጽናናት ወንጌል ብዙዎችን ስላሳረፈ፣ እያስፈራሩ የመበለቶችን ቤት መዝረፍ ስለቀረ ነው።

3. በነጻ ሕመማንን ሲያድን ሙታንን ሲያሳነሣ በሰው በሽታና ቀብር የሚያገኙትን ገቢ ስላሳጣቸው ነው።

4. ፍቅር ስለሆነ ብዙዎች ቢወዱት ሌላውን ሳይወዱ መወደድን መሻታቸው ስለከሰረባቸው ነው። በዚህ ምክንያት ጠሉት። የደስታቸውን ገበታ በመቃብሩ ላይ ካልሆነ በሕይወት እያለ መዘርጋት የማይችሉ መሆኑን በግልጥ ተናገሩ። ትልቅ መለኮታዊ ክብር ትቶ መምጣቱን ዘንግተው በሚለዋወጥ የዓለም ክብር ጠረጠሩት። ስለዚህ ለሞት አሳልፈው ሰጡት። በእውነትም ጊዜያዊ ድል አገኙ። ከዓርብ እስከ እሑድ በመቃብር ዘጉበት። ወዳጆቹ ከዱት፣ ያመኑት ተጠራጠሩት፣ የመሰከሩለት ተደበቁ። ከአይሁድ ግርማ የተነሣ ደቀ መዛሙርቱ በራቸውን ዘጉ። ያ ሁሉ ሕዝብ ተሰፋ ቆረጠበት። ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ ከሞቱ በፊት ስለ ትንሣኤው የነገራቸውን ቢረሱና ቢጠራጠሩም ጠላቶቹ ግን አልረሱም፣ አልተጠራጠሩም። ስለዚህ ሦስት ጥንቃቄዎችን አደረጉ፦

1- መቃብሩን በትልቅ ድንጋይ ገጠሙ፣
2- ወታደሮች አቆሙ፣
3- ቢነሣ እንኳ ትንሣኤውን የሚያስተባብሉ ሰዎችን በገንዘብ አዘጋጁ (ማቴ. 28÷1-15)።

ለካ ጠላት መከራና ስደት የሚያስነሣው ስለናቀን ሳይሆን ስለፈራን ነው። እኛ ራሳችንን እንደምናየው ጠላት አሳንሶ አያየንም። ጠላታችን ከእኛ ይልቅ እግዚአብሔር በእኛ ላይ ያለውን ዓላማ ያያል። በመቃብር ስፍራ ያሉ ጠላት የለባቸውም፣ ማንም ስማቸውን አያነሣም። ለምን? ስንል ሞተዋል። ጠላት ካለብን በሕይወት አለን ማለት ነው።

አይሁድ ይህን ሁሉ ቢያደርጉም በክርስቶስ ላይ ያገኙት ድል ከእሑድ አልዘለለም። መቃብር ክፈቱልኝ፣ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ከሞት ተነሣ። ዳግመኛ ሞት ላይዘው በዘላለማዊ ትንሣኤ ተነሣ። የተበተኑት ተሰባሰቡ፣ የተጠራጠሩት ዳግም አመኑበት። በራእያችንም የተቃዋሚዎች ጊዜያዊ ድል ሊያስደነግጠን አይገባም። ድላቸው ከሦስት ቀን አይበልጥም። በመጨረሻ የሚያሸንፈው እውነት ብቻ ነው። የነገሥታት ጉልበት ያላሰረውን የወንጌል እውነት የተቃዋሚዎች ብዛት አያስረውም። በተቃራኒው ግን ተቃዋሚዎች ጠንቃቃ እንድንሆን ሲያደርጉን፣ ዘወትርም ያነቁናል። ጉድለታችንን እንድናይ ይረዱናል። እግዚአብሔር በተቃዋሚዎችም ይጠቀማል።

የራእይ መከፈል

የውጭውን ስንከላከል በልቶ የሚጨርስን የውስጡ መሆኑን ብዙ ዘመን አይተናል። የውጭው በጠላትነት ይነሣል ብለን የምንጠብቀው፣ በመልካምነት ደግሞ የማንጠብቀው በመሆኑ ቀስቱ አካልን እንጂ መንፈስን አያገኘውም። የውስጡ ግን በጠላትነት ይነሣል ብለን የማንጠብቀው፣ በመልካምነት ግን የምንጠብቀው በመሆኑ ፍላጻው አካልን ሳይሆን ውስጥን የመጉዳት አቅም አለው። የወዳጅ ሞስል ብርቱ ነውና። ነገር ግን በዓለም ላይ የሚከለስ አንጂ አዲስ ነገር የለምና ደስ ሊለን ይገባል። እኛ የምናሚሸው መከራ የለም። እየሆነ ያለው ሲሆን የነበረ ነው። ነገር ግን ውሸት ያለ ማደሪያ ብዙዎችን አስከትታ ትጓዛለች። በመጨረሻም ውሸትን አምነው የተከተሉ ሁሉ በታላቅ ፀፀት ይመለሳሉ። ዋናው ነገር ከሄድንም በሩን ዘግቶ አለመሄድ፣ ለሄዱትም በሩን ዘግቶ አለመቀመጥ ነው። ውድቀት ያየ፣ ከድቶ የተመለሰ እንደ ጴጥሮስ ታማኝ ደቀ መዝሙር ይሆንልናል። የምናልፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባለፈበት ጉዳና ነው። የምናልፈው ብዙ ባለ ራእዮች፣ ብዙ ነቢያትና አገልጋዮች ባለፉበት የለማ ጉዳና ላይ ነውና አንፈራም። አልከዳህም ብሎ ጴጥሮስ ሲክደው፣ ለማስገደል ይሁዳ ሲስመው ጌታችን አይቷል። ሁሉን ግን በፍቅር በመፈጸሙ ጴጥሮስ ለንስሐ በቅቷል፣ ይሁዳ በሥጋዊ ፀፀት ራሱን ቀጥቷል። እኛም ከአጠገባችን ለሚንሸራተቱት ምላሻችን ፍቅር ብቻ ሲሆን አንዳንዶች ለንስሐ በቅተው ይመለሳሉ። ሌሎችም የእኛን ንጽሕና እያወጁ ራሳቸውን እየኮነኑ ይኖራሉ።

ራእይ ውጫዊ ብቻ ሳይሆን ውስጣዊ ተገዳዳሪዎችም አሉት። ራእይ የወዳጅ ጠላትን ያስተናግዳል። የጠላት ጠላትነት ፈተና አይደለም፣ የወዳጅ ጠላትነት ግን ፈተና ነው። ስለዚህ በብርቱ ልንፈተን እንችላለን። ራእይ በመጀመሪያ ላይ ብቻ ሳይሆን በመዳረሻው ላይም ፈተና ይገጥመዋል። የትግሉ ምዕራፍ ተጠናቀቀ ስንል ከውስጣችን ወዳጆቻችን በአድማ መነሣሣት ይጀምራሉ። የብዙ ሰዎች ባሕርይ በክፉ ቀን መክዳት ብቻ አይደለም፣ በመልካም ቀንም ጠላት ሆነው የሚነሡ ሰዎችም አሉ። ራእዩ ወደ ግቡ ሲቃረብ አብረው ያለቀሱ ሰዎች አብረው በረከቱን መብላት ያቅታቸዋል። ሰው በውስጡ እንዳለ ሳያውቅ ነገር ግን ይዞት የሚኖረው ጠባይ ቅንዓት ምቀኝነት ነው። ቅንዓት ምቀኝነት በልመና የሚያውቀውን ሰው በልመና ኖሮ የሞተ ቀን «አንተ ከርታታ» ብሎ ሊያለቅስለት ይመኛል። ቅንዓት ምቀኝነት መርዳት ቢፈልግም ያ ሰው ራሱን ሲችል ግን ይበሳጫል። ቅንዓት ምቀኝነት ያንን ሰው ይወደዋል ሌሎች ሲወዱትና ያ ሰውም ሌሎችን መውደድ ሲጀምር ጠላት ሆኖ

ይነሣል። ከዚህ ፈተና እንዲያወጣን በብርቱ መጸለይ አለብን። በሰው መልካም ዕድል ብስጩ እንዳልሆን ጠብቀኝ ማለት ትልቅ ጸሎት ነው። ቅንዓት ክፉ ገዢ ነውና የመጣብን ቀን ራሳችንን መቆጣጠር ያቅተናል። ቅንዓት አጥንትን የሚያነቅዝ መርዝ ነው። በራእይ ላይም የራእዩ መሪዎች የገነኑ ሲመስላቸው እኛ ተረሳን የሚሉ ብሶተኞች ከፊት ያለውን ሰው ጥለው እንደኛ ለመሆን ሩጫ ይጀምራሉ። ይህ በራእዩ ላይ መከፈል ይፈጥራል። ሁሉም ዘር አለውና ቅንዓተኞችም ዘራቸውን ይዘው መጋደል ይፈልጋሉ። እውነተኛው ሳይሆን ቀድሞ ያወራው እንደ እውነተኛ በሚታይበት ዓለም ባለ ራእዩ እንደ ጥፋተኛ ይቆጠራል።

እነዚህ ሰዎች በራእዩ ላይ የጥፋት ዓላማ ይዘው ሲነሡ «እኛ የቀናነው ለራእዩ ነው» እያሉ በዕንባ ጭምር ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ ይተጋሉ። ሊጥሉት ያሰቡትን ሰው እየሸለሙ በፊቱ መልካም እያወሩ ከኋላ ሆነው ሥራቸውን ይሠራሉ። የመለመሏቸው ሲጋደሉ እነርሱ እንደ አስታራቂ በመሆን ዙፋን ማደላደል ይጀምራሉ። ከባል የሚለዩ ውሸሞች ናቸውና ፍቅራቸው ግን ዕድሜ የለውም። ተጠቅመው የሚጥሉ አመንዝሮች የጠባይ ዘማዎች ናቸው። ነፋስ መሬት ላይ ተደላድሎ የተቀመጠውን ቀላል ዕቃ አንሥቶ በአየር ላይ እያንሳፈፈ ይወስደዋል። ሜዳ ሜዳውን ተሸክሞት ገደል ላይ ጥሎት ይሄዳል። እስከ መጨረሻው ላይሸከም ከመሬት ይለየዋል። እነዚህም ሰዎች የነፋስ ሰረገላዎች ናቸው። መንጋውን ከእረኛው ለይተው ኋላም ጥለውት ይሄዳሉ። አልወለዱምና አጋድሞ ለማረድ ይጨክናሉ።

እነዚህ ሰዎች ውስጣዊ ንቅናቄን የሚፈጥሩበት ምክንያቱ ብዙ ነው። ተቀባዮቻቸውም የተለያየ መልክ አላቸው። ውስጣዊ ንቅናቄን የሚያነሡበት ምክንያታቸው፦

1. <u>መምህሮቻቸውን በመናቅ ነው</u>፦ አዲስ ክርስቲያን ከጳጳስ አይበልጥም ነገር ግን የሚበልጥ ይመስለዋል። አዲስ ባለ ራእዮችም ባለ ራእዩ በዓይናቸው ፊት ያንስባቸውና እኛ የተሻለ እንመራለን ማለት ይጀምራሉ። ራስን መሾም የቅለት የመጀመሪያው ምዕራፍ መሆኑን ከእነዚህ ሰዎች እናያለን። ሹመት ይገባችኋል እንጂ ይገባኛል ስንለው ይጥለናል። «ክበሮ በሰው እጅ ያምር፣ ሲይዙት ያደናግር» እንደሚባለው በሩቅ ሲያዩ የባለ ራእዩ ድርሻ ቀላል ይመስላቸዋል። ስለዚህ ራእዩን ለመበጥበጥ የወንበር ግፊያ ይጀምራሉ። ራእይ ግን በጸጋ እንጂ በሙያ የሚሰምር አይደለም። ወረቀት የሚታይበት መሥሪያ ቤት ሳይሆን ሰማያዊ ቅባት ያለበት

አምባሳደርነት ነው። በሥጋ ቁመት የማንለካከበት ትንንሽ በሚመስሉ ሰዎች እግዚአብሔር ትልቅ ሥራ የሚሠራበት ነው።

2. <u>አብሮ መኖርና መቀራረብ ፈተና ይሆንባቸዋል</u>፦ አብሮ መኖር የመናናቅ ርዕስ ሊሆን በፍጹም አይችልም። የከረመ ወዳጅ እንደ ከረመ ወይን ጠጅ ዋጋው ውድ መሆኑን ቀላሎች አይገነዘቡም። የዛሬው ወዳጅ ከዛሬው ጥጋብ ተነሥቶ ሁሉን ይተነትናል። አለው እንጂ ያጣል ብሎ አያስብም። አብሮ የኖረው ግን የዛሬን ሳይሆን ያለፈውን መከራ ያስባል። መቀራረብ አያናንቅም። የሰዎችን ገመና ስናውቅ ይበልጥ ልንወዳቸው ይገባል። ቀላሎች ግን መቀራረብ መናናቅን ይፈጥርባቸዋል። ዝነኛ ሰዎች አድናቂ እንጂ ወዳጅ እንደሌላቸው የምናየው ለዚህ ነው።

3. <u>ቅንዓት ምቀኝነት በጠላትነት ያነሣሣቸዋል</u>፦ ሳይጣሉ መጣላትን የሚወልድ፣ ያለ በደል ቂምን የሚወልድ ቅንዓት ምቀኝነት ነው። እነዚህ ሰዎች በከንቱ ጥላቻ ይነሣሣሉ። ወቃሽ ሀሊና በማጣት ያለ ይሉኝታ ጠላት በመሆን ይሰየማሉ። ያ ሰው ካልሞተ እኔ አልኖርም የሚል ሰይጣናዊ መንፈስን ይሞላሉ። ፎቶውን የሳሙትን ሰው ህልውናው ይደምሰስ እያሉ ያሳድማሉ። ከአጠገባችን የማናጣቸው ሰዎች ከእነዚህ ሰዎች ጋር መለለፋቸውን ስንሰማ ልባችን ይቀልጣል። ነገር ግን ከመጋረጃው ጀርባ ጴጥሮስና ይሁዳ ከመጋረጃው ውጭ ቀያፋና ሐና እንዳሉ ማሰብ ተገቢ ነው። ያልጠበቁት ክፉ ነገር ሰባሪ ነውና።

4. <u>ራእዩ ፍርሃት ሆነ በሚል ሥጋዊ ጀግንነት ይነሣሣሉ</u>፦ ራእይ በሥጋ ኃይል ሳይሆን በመንፈስ ኃይል ከግቡ የሚደርስ ነው። ራእይ በሰው ጊዜ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጊዜ የሚፈጸም ነው። እነዚህ ሰዎች ግን ማባበል የለብንም፣ በቊርጥ እንውጣ በማለት ተዉ የሚሏቸውን ባለ ራእዩች እንደ ጠላት ማየት ይጀምራሉ። «ካልደፈረሰ አይጠራም» ይላሉ። እኛ ያደፈረስነው ግን ሲጠራ አይቼም አላውቅም። እግዚአብሔር ግን አደፍርሶ እንደሚያጠራ እናውቃለን። ሳያደፈርስም ማጥራት እንደሚችል እናውቃለን። ባበጠ ይፈንዳ መርህ የሚጓዙ ሰዎች ግን የእነርሱ ብጥበጣ ሰላምን የሚያመጣ ይመስላቸዋል። በእነዚህ ምክንያቶች ራእይን ለመክፈል ሰዎች ይነሣሣሉ። በዚህ ሰዓት ላይ የብዙኃኑ ጎራ በተለያየ መንገድ መከፈል ይጀምራል። ጎራውም የተለያየ መልክ አለው። የተወሰኑትን ቀጥሎ እናያለን፦

➢ <u>ፍጹም ጠላት የሚሆነው ጎራ</u>፦ ጠብን ከፈለሰፈው ሰው ይልቅ የተቀበለው ሰውዬ ይጠናበታል። ከዋናው ተቃዋሚያችን

ይልቅ ወዳጆቻችን የነበሩ አዲስ ምልምሎች ተጋፍጠው ይሰድቡናል። እገሌማ ምን አለኝ? እስክንል ከመምህሩ የደቀ መዝሙሩ ተግባር ይብስብናል። ከዋናዎቹ ተቃዋሚዎቻችን የማንሰማውን በወኪሎቹ ተላላኪዎች፣ ጃስ በተባሉ የራሳቸው ጠብ በሌላቸው የጠባይ ከለባት ልብ የሚሰብር ንግግር እንሰማለን። የዚህ መድኃኒቱ ሊሰብረን ለሚፈልግ አለመስበር ብቻ ነው። አም ከሠራን ጠላት አለ ካልሠራን ግን ጠላት የለብንም። ነገር ግን ጠላት አለ ብለን ሞተን አንጠብቀውም። እንከን ሊኖርብን ይችላል። ካለመሥራት ፍጹምነት ይልቅ የመሥራት ስህተት የተሻለ ነው። አንድ ሰው፡- «F ለማግኘትም መማር ያስፈልጋል» ብሏል። ለመነቀፍም መሥራት ግድ ይላል ማለቱ ነው። የባላጋሮቻችን የበኩር ልጆች ፍጹም ጠላት ሆነው ይነሡብናል። ባላጋሮቻችንን ስንጠባበቅ ምልምሎቻቸው ከፊት ሆነው እንደ ይሁዳ ይመጡብናል። ባለ ራእዩን የሚደፍረው እንጀራውን የበላ ነውና።

➢ <u>ባለማወቅ ተቃዋሚ የሚሆነው ጎራ</u>፡- ባለማወቅ የሚወዱን ሰዎች ባለማወቅም ይጠሉናል። እነዚህ ሰዎች በስማ በለው የሚነዱ እንጂ ወጥቶ ለመግባት የሕይወት ኮምፓስ የሌላቸው፣ የቀደመ የሚወስዳቸው፣ እንደ በረሃ ሸምበቆ በነፈሰበት የሚወዘወዙ ናቸው። ብረት ድስት እሳት ላይ ሲያወጡት ቶሎ ይግላል፣ ሲያወርዱት ቶሎ ይበርዳል። እነዚህም ሰዎች ስሜታውያን ሆነው ይቃወሙናል። የመጀመሪያዎቹን በጽናት ልንጠብቃቸው ሲገባ እነዚህን ግን በይቅርታ ልብ ልንጠብቃቸው ይገባል። እነዚህ ሰዎች ቢቆዩም መሄዳቸው አይቀርምና በመሄዳቸው ልናዝን አይገባም። በድምፅ ብልጫ የሚወደን በድምፅ ብልጫ ይጠላናል።

➢ <u>በአስተካሽነት እኛ ጋ የሚቀረው ጎራ</u>፡- እንዳይሄዱ የእኛ ፍቅር ግድ እያላቸው እንዳይቀሩ ዓላማ ቢስነታቸው እየታገላቸው ልባቸው ሸፍቶ አካላቸው እኛ ጋ የሚቀር ወገኖች አሉ። እነዚህ ሰዎች እኛ ጋ እየበሉ ጠላት ጋ የሚውጡ፣ ከጠላት ሰፈር በሬዲዮ እየተነጋገሩ በመካከላችን ቦምብ የሚያስጥሉብን አስተኪሾች ናቸው። ጥርሳቸውን እያሳመሩ፣ መልካቸውን እያስዋቡ፣ ያገናኘንን ትልቅ ዓላማ ዘንግተው በትንሽ ውለታ ይሉኝታ ይዟቸው የሚቀሩ፣ ወዳጆች የማይሆኑ ፍሬ አልባ በለሶች ናቸው።

➢ <u>በሌላው አድማ ልባቸው በደስታ ድቤ የሚመታ ጎራ</u>፡- እነዚህ ሰዎች ከጠላቶቻችን ጋር አይሄዱም። የማንም ወገንተኛ አይደለሁም ይላሉ። ከፊት ሆነው መጋፈጥ አይፈልጉም። ጥቅማቸውን አስከብረው ለመኖር ይሻሉ። በሞኝ ማሳ የሚበሉ

እየመሰላቸው ይደሰታሉ። ከሁሉ በላይ የሚያስደስታቸው ራእዩ ሲታወክ «ይበላቸው» እያሉ በደስታ ይዘላሉ። አለቃ ገብረ ሃና የሚስታቸው ውሽማ የነበረ ሰው የሞተ ቀን ስሙ ደስታ ይባል ነበርና በስሙ አስመስለው «ደስታዬ፣ ደስታዬ» ብለው አለቀሱ ይባላል። ደስታዬ እያሉ የሚያለቅሱ ሰዎችን በራእይ ውስጥ እናስተናግዳለን።

ሲጽፉትና ሲናገሩት ቀላል ቢሆንም ለኑሮና ለራእይ እንግዳ በሆንበት ዘመን የውስጥ ባላጋሮች ያስተክዙናል። ጊዜ ካለፈ በኋላ ግን በእነርሱ ተንኰል ሳይሆን በከፈልነው የብስጭት ዋጋ እናዝናለን። ሁሉም ነገር ሲመጣ ላያልፍ የመጣ ይመስላል። ነገር ግን አላልፍም ብሎ ያስቸገረ ክፉ እስከ ዛሬ አላየንምና ደስ ሊለን ይገባል። ጥቂት መታገሥ ከቻልን በእኛ ላይ የተነሡ እርስ በርሳቸው ሲጠፋፉ እናያለን። የሌባ ስምምነት አስኪሰርቅ ነው ይባላል። ሲከፋፈል ይጣላል።

ሁሉም ዘር አለውና ቅንዓተኞችም ዘር አላቸው። መንፈስ የሆነው ሰይጣን እንኳ ዘር አለው ተብሏል (ዘፍ. 3÷15)። ስለዚህ ከቅንዓተኞችና ከዘሮቻቸው ጋር ያለንን ፍልሚያ እንደ ድንቅ መቀጠር የለብንም። ምላሻችን ሁሉ እንደ ቃሉ ከሆነ በመጨረሻ ጎሊናችንን እናተርፋለን። ሰውን ከማትረፍ ይልቅ ጎሊናን ማትረፍ ደስታ አለውና። ባለ ራእዩ ይህ ሁሉ ሲሆን ዋነኛ ጠንሳሾችንና የጠብ ደቦኞችን/ጂጊዎችን/ በእርጋታ ማነጋገር አለበት። የሚሰማው ሊሰማ የሚፈልግ ነውና ላለመስማት ሊሰሙት እንደሚችሉ መገመት አለበት። ነገር ግን የሚተርፉ ሰዎች ስለሚኖሩ ማነጋገሩ ወሳኝ ነው። ከእነዚህ ሰዎች አድማ ይልቅ የሚጥለው የግል ቅድስናን ማጣት፣ ጸሎትን ትቶ በሥጋ መዋጋት፣ መበሳጨትና ከንቱ ንግግር በመሆኑ መጠንቀቅ ይገባዋል። «እንዲህ ብትሉት ይጣላችኋል» ብለው የአድማ መሪዎቹ ስለሚልኳቸው መልእክተኞቻቸውን በትዕግሥት ማስተናገድ ይገባል። «ከእናንተ ጋር የማያኖር ጠባይ ካለኝ ከሌሎች ጋርም አያኖረኝምና ስህተቴን ንገሩኝ» ማለት ይገባዋል። የሰሙ ሰዎች ሁሉ እንደ አዲስ ሊተነትኑለት፣ ያበረዱ እየመሰላቸው እሳት ሊጭሩበት ይመጣሉና ባለ ራእዩ በትዕግሥት ማስተናገድ ይገባዋል።

ሌባ የሚያሳድደው ወርቅ የያዘውን ነው። ባዶ እጁን የሆነውን ሌባም አይፈልገውም። ይህ ሁሉ ስደት የታወጀበት የከበረ ነገር ቢኖረው ነውና ባለ ራእዩ ደስ ሊለው ይገባል። ከቀናተኞች የተሻለ ምላሽ በመስጠትም አእምሮን መማረክ ይገባዋል። ልክ ቢሆንም ብስጭቱ ልክነቱን እንዳይሸፍንበት ማሰብ ያስፈልገዋል።

በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ፣ የብርሃን ድንኳን በሆነው በራእይ ውስጥ ሊለያየን የሚችለው የግል ፍላጎታችን ብቻ ነው። የሁላችንም አሳብ እግዚአብሔርን ማክበር ከሆነ አንለያይም። እንደሚመስለኝ ሳይሆን ቃሉ እንደሚለው የሚል መመሪያ ካለን አንድነታችን የጠበቀ ነው። የሚለያዩን የሚመስሉን ነገሮች ናቸውና። የአሳብ ግጭቶች እንደ ጠላት ሊያስተያዩን አይገባም። ማዕከላችን እውነትና ፍቅር እስከሆነ ድረስ የአሳብ ግጭቶች ወደ ጠበቀ አንድነት ያደርሱናል። ሰዎች አሳባቸውን በሰላም እስከገለጡልን ድረስ ማስተናገድ ይገባናል። አሳቡ ደካማም ቢሆን በአሳብ መልኩ ከቀረበ አቅራቢውን ወገን እንደ ጠላት ልንመለከተው አይገባም። ሰላም የሌሰባቸው ሰላም የሚመስሉ ራእዮች አሳቦችን የማያንሸራሽሩ ቤተ ራእዮች ናቸው። የአሳብ ግጭቶችን በጣም ስለምንፈራ አፍነን እንኖራለን። የታፈነ አሳብ ግን በፍጻሜው አደጋ ይፈጥራል። አዲስ አመለካከት የያዙ ሰዎችን፣ ላዩ ሲታይ ራእያችንን የሚቃወም የሚመስል አሳብ የያዙ ሰዎችን ፈጥነን መምታት እንፈልጋለን። ዓላማችን ሰዎችን ማትረፍ ከሆነ እነዚህንም ሰዎች ጥለን መግባት የለብንም። ልንሰማቸውና ገንዘብ ልናደርጋቸው ይገባናል።

የሚገርመው የራእይ መከፈል የሚገጥመው ራእይ ወደ ስኬት ሲቃረብ ነው። መልካም ድግስ ከዋዜማው ያስታውቃልና የድግሱ ማማር ሲታያቸው በዋዜማው ብዙዎች ጠላት ሆነው ይነሣሉ። ራእዩን እንደሚወዱት በመናገር ባለ ራእዩን ለማጥፋት ይነሣሣሉ። የውጭ ተቃዋሚዎች ራእዩን ሲቃወሙ የውስጥ ተቃዋሚዎች ደግሞ ባለ ራእዩን ይቃወማሉ። ነገር ግን ራእዩንና ባለ ራእዩን መለየት አይቻልምና የሁለቱም ዓላማ አንድ ነው። የሚያሳዝነው የውስጥ ተቃዋሚዎች ትላንት ይቃወሟቸው ከነበሩት ጋር በማበር ያደጉበትን ቤተ ራእይ ለማፍረስ ይነቃቃሉ። ራእይ የመከፈል አደጋ ቢገጥመውም አይጠፋም። ዛፍ በፍሬው በአንድ ግንድ ይመዘዛል። በመቆረጥ ግን በብዙ ቁጥቋጦ ይበዛል። የራእይ መከፈል ስሜትን ቢጐዳም የበለጠ ድል ግን እያየን የምንሄድበት፣ ዓይናችንን የጣልንባቸው ሰዎች ቀርተው የማንጠብቃቸውን ወገኖች አርዳታ የምናይበት፣ እግዚአብሔር የከፈተውን የሚዘጋ ኃይል እንደሌለ የምንገነዘብበት ነው።

የቤት ሠራተኛዋ አለአርስዋ ቤቱ ቤት የማይሆን እየመሰላት በልግመት ባለቤቶቿን አሰቃየቻቸው። ይባስ ብላ አልሠራም በማለት ጥላ ወጣች። ያለ እኔ ምን ይሆናሉ ብላ የሚሆኑትን ለማየት አፋፍ ላይ ቁጭ ብላ ስትጠባበቅ ባለቤቷ ባጭር ታጥቃ ወደ ኩሽናዋ ገብታ መሥራት ጀመረች። አፋፍ ላይ የተቀመጠችዋ ተመልካችም ጭሱን

ስታይ፡- «እኔም ወጥቼ ጭስ ይጨሳል ወይ?» አለች ይባላል። እንዲሁ እነርሱ ወጥተው ራእይ የሚቀጥል የማይመስላቸው፣ የእነርሱ ድርሻ አንዱ ሳይሆን ሁሉንም የሚጠቀልል እየመሰላቸው የሚያስቡ ሰዎች ከመቆየት ይልቅ በመሄድ ይማራሉ። «ለሚፈራሽ ታስፈሪያለሽ» እንዲሉ እነዚህ ሰዎች ምንም አስፈሪነት የሌላቸው ለሚፈራ ግን የሚያስፈሩ ናቸው። ባለ ራእዩ ግን ወደ ግቡ በመፍጠን፣ ከመሳደብ ይልቅ በመሥራት ብቻ እንደሚያሸንፍ ሊያስተውል ይገባዋል።

እናስተውል

- እግዚአብሔር ግን ካሰበልን ቦታ የሚያደርሰን እየገፋን ነው።
- እግዚአብሔር እንደ ጳውሎስ አይሥራባቸው እንጂ እንደ ፈርያን የሚሠራባቸው ገፊዎች ዛሬም አሉ።
- ክርስቲያን ግን ሁለት ደስታ ተመድቦለታል። ከመሆኑ በፊት በተስፋ፣ ከሆነ በኋላ በእምነት እንዲደሰት ከላይ ተፈቅዶለታልና ደስ ይበላችሁ!
- እኛ ምን እንደምንሆን ራሳችንን ከምናውቀው ይልቅ ጠላት በደንብ ያውቀዋል።
- እግዚአብሔር ክንድ ያልሆነለት የደካሞች ደካማ ነው።
- በመጨረሻ የሚያሸንፈው እውነት ብቻ ነው። የነገሥታት ጉልበት ያላሰረውን የወንጌል እውነት የተቃዋሚዎች ብዛት አያስረውም።
- እውነተኛው ሳይሆን ቀድሞ ያወራው እንደ እውነተኛ በሚታይበት ዓለም ባለ ራእዩ እንደ ጥፋተኛ ይቆጠራል።
- ራእይ ግን በጸጋ እንጂ በሙያ የሚሰምር አይደለም። ወረቀት የሚታይበት መሥሪያ ቤት ሳይሆን ሰማያዊ ቅባት ያለበት አምባሳደርነት ነው።
- በድምፅ ብልጫ የሚወደን በድምፅ ብልጫ ይጠላናል።
- ሌባ የሚያሳድደው ወርቅ የያዘውን ነው። ባዶ እጁን የሆነውን ሌባም አይፈልገውም።
- ድል መኖር ሳይሆን በጽናት ማለፍም ነው።
- ራእይ የመከፈል አደጋ ቢገጥመውም አይጠፋም። ዛፍ በፍሬው በአንድ ግንድ ይመዘዛል። በመቆረጥ ግን በብዙ ቁጥቋጦ ይበዛል።

ምዕራፍ ሃያ ስድስት

የመጨረሻው ሯጭ

ከስፖርት ዓይነቶች አንዱ የሆነው የዱላ ቅብብሎሽ የማይዘወተር የሩጫ ዓይነት ነው። ከሩጫ ስፖርቶች ወይም ውድድሮች ውስጥ የዱላ ቅብብሎሽ አንዱ ጀምሮ የማይጨርሰው በጎብረት ሩጫ የሚገኝ ድል ነው። ሯጮቹ በተወሰነ ርቀት መስመራቸው ላይ ቆመው ይጠብቃሉ። የሚጠብቁት ለእነርሱ እንዳይዘገይባቸው፣ እነርሱም ለሚጠብቃቸው እንዳይዘገዩ በመቀነጥነጥ ነው። የሚጠብቁት ሯጭ ቶሎ ዱላውን ካላስረከባቸው፣ እነርሱም ለሚጠብቃቸው ይዘገያሉ። ድሉ የሚመጣው ዱላውን በትክክል ጨብጦ በመፍጠን ነው። ያለ ዱላው የሚፈጥን ወይም ዱላውን ይዞ የሚያዘግም በዱላ ቅብብሎሽ ውድድር ባለ ድል አይሆንም። በትክክል ጨብጦ ለተረካቢው ዱላውን በትክክል ማስያዝ የስፖርቱ መመሪያ ነው። በየመስመሮቹ ላይ የሚቆሙ ተረካቢዎች ሲደለደሉ የመጨረሻው ሯጭ ፈጣን መሆን አለበት። የመጨረሻው ሯጭ ፈጣን ካልሆነ ድል የለም።

የሕይወትም ጉዞ በዱላ ቅብብሎሽ ቢመሰል ተገቢ ነው። በዱላ ቅብብሎሽ ራሱ ጀምሮ ራሱ የሚጨርስ ተወዳዳሪ የለም። በሕይወት ጉዞም እኛ ጀምረን፣ እኛ የምንጨርሰው ነገር የለም። የሕይወት ሩጫ ዛሬ አልተጀመረም። የሕይወት መንገድም የለማና የብዙ ሚሊየን ሕዝቦች የእግር ፈለግ/ዱካ/ ያለበት ነው። በሕይወት ጉዞ እኛ ጀምረን እኛ የምንጨርሰው ምንም ነገር የለም። እኛ ከጀመርን የሚጨርሱት ሌሎች ናቸው፤ እኛ ከጨረስንም የጀመሩት ሌሎች ናቸው። በሕይወት ጉዞ ራሳችን ጀምረን ራሳችን የምንጨርሰው ምንም ነገር የለም። ከእያንዳንዳችን የሚጠበቀው፣ ተገቢውን ርቀት አልፍ ማድረግ ነው። በሥነ ጽሑፍ፣ በሥነ ጥበብ፣ በፍልስፍና፣ በቴክኖሎጂ ... ራሱ ጀምሮ ራሱ የጨረሰ ትውልድ የለም። በሕይወት ውስጥ ድሉ የጋራ ነው። ሩጫውም የጎብረት ነው። የቀደሙት የራሳቸውን ሩጫ ሮጠው አለፉ። በታሪክ ፊት ይወደሳሉ ወይም ይወቀሳሉ። እኛም ለመመስገንም ሆነ ለመነቀፍ በታሪክ ፊት ነን። የቀደሙት ባረፈዱብን ነገር ዛሬ ዋጋ እየከፈልን ነው። የቀደሙትን ሥራ ስንሠራ ለቀጣዩ ትውልድ እያረፈድንበት ነው። የእኛ መዘግየትም ለቀጣዩ ትውልድ ብርቱ የቤት ሥራ ነው።

የሕይወት ሩጫ ከተጀመረ ብዙ ዘመናት አልፈዋል። ሩጫው ዋጋ የሚያገኝበት ፍጻሜ አለው። ሕይወት ምክንያት አልባ ዝርው፣ ማሰሪያ የሌላት ብትን ነዶ፣ ግብ የሌላት ከንቱ ሩጫ አይደለችም። የሕይወት ዋጋዋ ራሱ እግዚአብሔር ነው። በዱላ ቅብብሎሽ ስፖርት እያንዳንዱ ተወዳዳሪ መስመሩ ላይ ሆኖ ከኋላ ለመቀበል፣ ወደፊት ይዞ ለመሮጥ በሚያስችለው አቋቋም ዝግጁ ሆኖ ይጠብቃል። በሕይወት ላይ ከትላንት የምንቀበለው ለነገ የምናስተላልፈው ነገር አለ። ዛሬ ያለነው በትላንት ነው። ትላንትም የታወሰው በዛሬ ነው። ዛሬ መናቅ የለበትም። ትላንት እንዲታወስ እየፈለጉ ለዛሬ ግን ዋጋ የማይሰጡ ይኖራሉ። ነገር ግን ትላንት እንዲታወስ ፈልጎ ዛሬን ንቆ አይሆንም። በዛሬ ብቻ የተወሰኑና ትላንትን መርገም የሚፈልጉ በሌላኛው ጽንፍ ላይ ቆመዋል።

በዱላ ቅብብሎሽ ስፖርት ዱላውን አልሰጥም እኔ ይገዬ መጨረስ አለብኝ የሚል ተወዳዳሪ ሊኖር አይችልም፣ ቢልም ድል አይሰጠውም። የሚገጥመው ዕድል ከፊቱ ካሉት ጋር መጋጨት ብቻ ነው። በሕይወት ሩጫም የቀደሙት አባቶች ሰው ሁልጊዜ እንደማይበረታ መገንዘብ፣ በጊዜ የተገደቡ ፍጡራን መሆናቸውን በማስተዋል ለቀጣዩ ትውልድ ማስረከብ ይገባቸዋል። አልለቅም በተባለ ቁጥር በግድ መነጠቅና መዋረድ ይከሰታል። እንደ ባለ ራእይ ማስረከብ ግን ያስከብራል። ለምክርም ተፈላጊ ሰው ያደርጋል። ከመጋረጃ ኋላ ሆኖ የመምራትን ጸጋም ያጎናጽፋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ የሚያምኑ ከእርሱ የበለጠ እንዲሠሩ ፈቅዷል (ዮሐ. 14፥12)። ተረካቢዎቻችን ከእኛ ይልቅ እንዲሠሩ ስንፈቅድ ያን ጊዜ እውነተኛ ባለ ራእይ መሆናችን ይገለጻል። ይህ የተለመደ የሕይወት አሠራር ነው። ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን ከግብፅ አውጥቷል፣ ኢያሱ ግን አስገብቷል። ኤልሳዕ ከኤልያስ ይልቅ በእጥፍ ጸጋ አገልግሏል። ይህ ቅብብሎሽ በመልካም ሲፈጸም ብቻ አገርና ቤተ ክርስቲያን ከጥፋት ይድናሉ።

በዱላ ቅብብሎሽ ስፖርት ዱላውን ሳይዝ የሚሮጥ የለም። ቢገኝም ለውድድሩ መሰናክል እንጂ ድምቀት አይሆንም። በሕይወት ላይም የሕይወትን አደራ በደንብ ሳይጨብጡ የሚሮጡ ብዙ ችኮሎች አሉ። ሳያዳምጡ የሚናገሩ፣ ሳይመሩ የሚመሩ፣ ሳይሰበኩ የሚሰብኩ፣ ንስሓ ሳይገቡ ንስሓ የሚቀበሉ፣ ሳይወልዱ አባት የሚባሉ፣ ሳይቀደሱ የሚቀድሱ አሉ። እነዚህን ሰዎች እውነት እንዴት ትታዘባቸው ይሆን? በዱላ ቅብብሎሽ ስፖርት ዱላውን ይዞ የሚሮጠው መስመሩ ላይ መቆም፣ የኋላና የፊቱን ማማተር፣

ዱላውን በትክክል መጨበጥ፣ ፈጥኖ መሮጥ ይገባዋል። በሕይወት ሰልፍም እነዚህ ሕግጋት ቋሚ ናቸው።

- ሌላውን ጠልፎ ላለመጣል በመስመር ላይ መቆም፣
- የጠራ የሕይወት መረጃንና ራእይን መጨበጥ፣
- የጨበጡትን ለማድረስ መፍጠን፣
- ታሪክንና ነገን ማጤን ግድ ነው።

በዱላ ቅብብሎሽ ብዙ መሮጥ ቢፈልግ እንኳ ተወዳዳሪው ከተወሰነለት መስመር አያልፍምና ባለው ጥቂት ሩጫ ፈጣን መሆን አለበት። ዕድሜ የሚባል የማያሳልፍ መስመር አለ። ጉልበታችን እያለም ያ መስመር ይገታናል። ስለዚህ ጥቂት ጊዜ እንዳለን ተረድተን ፈጣን መሆን ይገባናል። ነቢዩ ዳዊት፡- «*የዘመኔን አነስተኛ ነት ንገረኝ*» እንዳለ (መዝ. 101÷23)። ነቢዩ፡- «የምኖረው ጥቂት ዘመን መሆኑን ተረድቼ እንድፈጥን ለውስጤ አሳስበኝ» ማለቱ ነው። አስተውሉ! ድል ያለው ዱላውን በመጨበጥና በመፍጠን ነው። በፍጥነት ብቻም ድል የለም። አንዳንዶች ዱላውን ጨብጠዋል ግን ተቀምጠዋል። ሌሎችም ዱላውን በትክክል ሳይጨብጡ ለመሮጥ ይፈጥናሉ።

በሕይወት ውስጥ ሳይገባቸው አም አም የሚሉ፣ ያልገባቸውንም ነገር ለማስተላለፍ የሚፈጥኑ፣ ለማደንቆር የሚሮጡ ብዙዎች ናቸው። ባዶ እጅ መፍጠን ጥቅም የለውም። ቅዱስ መጽሐፍ፡- «*ሰው ሁሉ ለመሰማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ይሁን*» (ያዕ. 1÷19) ይላል። ተፈጥሮአችንን እንኳ ብናጤነው ሁለት ጆሮ አንድ አፍ ነው ያለን። ብዙ እንድንሰማ፣ ጥቂት እንድንናገር ወይም ለመስማት ፈጣኖች ለመናገር የዘገየን እንድንሆን ያስገነዝበናል። ዛሬ በብዛት እያየን ያለነው አፍ እንጂ ጆሮ የተፈጠረላቸው የማይመስሉ ሰዎችን፣ በማስታወቂያ ኃይል፣ በደላላ አድማቂነት የከበሩትን፣ በአየር ላይ ቤት የሚሠሩትን፣ ገነው ለመጥፋት የሚሮጡትን ነው። መሠረት ያላቸውን፣ ወደሚቀጥለው ትውልድ የሚሻገር ሥራ ያላቸውን ባለ ራእዮች እያጣን ነው። ዕቃዎቻችን ሁሉ ተጠቅመን እንድንጥላቸው ሆነው ተዘጋጅተዋል፣ ራእዮቻችንም እንዲያ እንዳይሆኑ ያሰጋሉ። ዘመናችን ባልገባቸው ነገር ትንታኔ በሚያበዙ፣ በደፋር ፈጣኖች፣ በጮሌዎች የተሞላ በመሆኑ ይህችን ዓለም ባዶነት እያጠቃት ነው።

እግዚአብሔር የሚያስብልን የኑሮ ዘዴ እንዲገባን ሳይሆን የመኖር ዓላማ እንዲገባን ነው። እኛ ስለ ልዩ ልዩ ዓይነት ዘዴዎች እናስባለን፣ እግዚአብሔር ግን ስለ እውነት ያስብልናል። ዋናው

ረጅም ዘመን ማገልገል ሳይሆን የተቀበልነውን የእግዚአብሔር አደራ በትክክል መግለጥና ለሌሎች ማስተላለፍ ነው። ሙሴ ያገለገለው ዐርባ ዓመት ነው። 80 ዓመት ግን ለአገልግሎት ብቁ ለመሆን የተሠራበት ነው። ለ80 ዓመታት የሕይወት ምሥጢር አልገባውም ነበር። የሕይወት ምሥጢር የገባው ለኩራቱ ሲሞትና እግዚአብሔርን አዳምጦ መውጣት ሲጀምር ነው። ሙሴ ከእኔነቱ ነጻ ከወጣ በኋላ ሕዝቡን ነጻ ለማውጣት ተላከ። ከራሱ ነጻ ያልወጣ ሌላውን ነጻ ማውጣት አይችልም። ትልቅ ባርነት የፍላጎት አስረኛ፣ የራስ ወዳድነትና የትዕቢት ምርኮኛ መሆን ነው።

አም ትልቁ ነገር መሮጥ ሳይሆን ዱላውን /ዓላማውን/ መያዝ ነው። ትልቁ ነገር መሮጥ ሳይሆን አዳምጦ መሮጥ ነው። ሳያዳምጥ የሚሮጥ ቶሎ ይደርሳል። መልእክቱ ግን ይጠፋዋል። እንደገና እየሮጠ ይመለሳል። የሚተርፈው ግን ቀጣ፣ ድካም፣ ለዘለቂታው ተአማኒነትን ማጣት ነው። መቸኮል መዘግየት የሚሆንበት ጊዜ ብዙ ነው። የበረሩ መኪናዎች አደጋ ደርሰባቸው ለዘመናት በዚያ ቦታ ላይ ተገልብጠው ይታያሉ። በሩጫው መጀመሪያ የፈጠኑም የድሉ ዋዜማ ላይ አይታዩም። ዋናው መድረሱ ብቻ ሳይሆን በድል መድረስ ነው። ብዙዎች አዋቂ ሆኑ፣ ባለጠጋ ሆኑ፣ ባለሥልጣን ሆኑ ግን ዱላው የለምና የሚሠሩትን አያውቁም። እነዚህ ሁሉ መድረሻቸው ከመጠጥ ቤት አያልፍም። ከራእይ ያጡትንም ክብር ከአዝማሪ ለማግኘት የሌላቸውን ስም ለጥፋልኝ እያሉ እንቅልፍ አጥተው ያድራሉ። ራእይ የሌለበት ድል እንቅልፍ ይነሣል፣ እፎይ አያሰኝም። ከራእይ ይልቅ በቁሳቁስ መኩራትን ይመልዳል። ገንዘቡ ያለቀ ቀንም የአዝማሪዎችና የደላላዎች ምስጋና አብሮ ያልቃል። ባለ ራእይ ግን ዝም ብሎም ሲነሣ ይኖራል። በማግኘት በማጣትም ሳይለካ ከሁኔታዎች በላይ ይኖራል። ሁኔታዎችን ይስቅባቸዋል እንጂ አይስቁበትም። ባለጠግነትም ሆነ ድህነት ሁኔታ ነው፤ ራእይ ግን እውነታ ነው።

ጳውሎስ አዲስ ራእይ ተቀበለ። የፊተኛው ራእዩ ሌላውን በማጥፋት ላይ የተመሠረተ ነው። የአሁኑ ራእይ ግን ሌላው እንዲኖር ካስፈለገ መሞትን የሚጠይቅ ነው። ጳውሎስ ግን ወደ አዲሱ ራእይ ሲሸጋገር በቀጥታ ሩጫ አልጀመረም። በዓረብ በረሃ ላይ ቁጭ ብሎ ራእዩን ከራሱ ጋር አዋሐደ። ለማዋሐድ የፈጀበት ጊዜ ሦስት ዓመት ነው (ገላ. 1÷17)።

በዱላ ቅብብሎሽ ዱላውን የሚያስረክበው ወገን ለተረካቢው ካስረከበ በኋላ ጥቂት መንገድ አብሮት ይጓዛል። በትክክል ዱላውን እንዳስረከበ ካረጋገጠ በኋላ ይመለሳል። በሕይወት ሩጫም

ለተረካቢዎች ካስረከብን በኋላ ጥቂት ማለማመድ አለብን። ጌታችን ታላቁን አደራ ወንጌልን ስበኩ ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ከማዘዙ በፊት እርሱ እያለ በመላክ አለማምዷቸዋል (ሉቃ. 10፥1-20)። እግዚአብሔር በእኛ ላይ ያለውን ዓላማ በመልካም ለመጨረስና ለሌሎች ለማስተላለፍ ምን ያህል ቊርጠኞች ነን? ሰው ብቻ ሳይሆን ጊዜም እንደሚጋፋን የተገነዘብን ስንቶች ነን? ሕይወት እንደ ረጅም ርቀት ሩጫ አይደለችም፣ የረጅም ርቀት ሯጭ ራሱ ጀምሮ ራሱ ይጨርሳል። ሕይወት ግን የዱላ ቅብብሎሽ ናት። እስከ ክርስቶስ መምጣት ያለውን የዘር ሐረግ ስንመለከት ቅብብሎሽ እንደ ነበረና በዚህ ቅብብሎሽም ታላቁ መድኃኒት እንደ ተወለደ እንረዳለን (ማቴ. 1፥1-20)። አብርሃም ይስሐቅን፣ ይስሐቅ ያዕቆብን፣ ያዕቆብ ዮሴፍን በትክክል ተክተዋል። በሥጋ ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ተዋልደዋል።

አንድ የጥንት የግሪክ ፈላስፋ፡- «በደህና የመኖርና በደህና የመሞት ጥበብ አንድ ነው» ብሏል። አም መልካም ሞት የመልካም ኑሮ ውጤት ነው። አብርሃምን እንደ ሞተ አስበን ከማዘን ከሞቱ ማራኪ ነገር እንፈልጋለን። ኑሮው ውብ ስለ ነበር ሞቱም ተውቧል። ዱላውን ለጨበጡ ሰዎች ሕይወትና ሞት ውብ ነው። ማራኪ ቁመና ያለንና ፈጣን ሯጭ ልንሆን ብንችል፣ ዱላው ግን በእጃችን ከሌለ ሩጫው የሽንፈት ሩጫ ብቻ ነው። በዱላ ቅብብሎሽ የአንዱ ስህተት ሁሉንም ማስቀጣቱ አስገራሚ ነው። በሕይወትም ላይ የአንድ ሰው ስህተት ለብዙዎች ጉዳት ምክንያት ይሆናል። አንዱ አዳም ለሰው ዘር ሞት በር ነበረ፣ አንዱ ክርስቶስ ደግሞ የሕይወት ምክንያት ሆኗል። አም የአንዱ ስህተት ለብዙዎች ቅጣት ይሆናል። ትልቁ የሕይወት ክፍተት ያለው የእኔ ስህተት ለዓለም ምን ጉዳት ያመጣል? ብለን በማሰብ ላይ ነው። ግራ እግር ሲያነክስ ቀኙ ይዘገያል። እኛ ራእይ አልባ ስንሆንም ብዙዎችን ከግባቸው እናዘገያለን።

በዱላ ቅብብሎሽ ሩጫ ውድድሩ ሊሰረዝባቸው የሚችሉ ምክንያቶችን ብንጠቅስ፡-

1- ዱላውን መጣል
2- ያልተገባ የሆነ የዱላ አቀባበል
3- ጅምሩ ሳይፈቀድ መጀመር
4- ሌላውን ተወዳዳሪ አለአግባብ መቅደም
5- መንገድ በመዝጋት ሌላውን መጋፋት
6- በፈቃድም ሆነ ያለ ፈቃድ በሌላኛው መንገድ ውስጥ ገብቶ መሮጥ ከውድድር ውጭ ያደርጋል።

በሕይወት ውስጥም ከሕይወት መስመር የሚያወጡ ነገሮች፡-

1. ዓላማን መሳት
2. ከቀደሙት መልካሙን ሳይሆን ክፉውን መያዝ
3. ጊዜውን ለይቶ አለመውጣት
4. ያለ መንገዱ ክብረትን መፈለግ
5. ሌሎችን ሠውቶ የራስን ኑሮ ማደላደል
6. የሌሎችን መብትና ጥቅም መጋፋት

ከሕይወት መስመር አውጥቶ ከድሉ ይለያል። ፍጻሜንም ያበላሻል።

በዱላ ቅብብሎሽ ከመጀመሪያው ሰው ጀምሮ ወደፊት የሚደረደሩት ሯጮች የሩጫ ፍጥነታቸው እያደገ የሚሄድ ሯጮች ናቸው። መጀመሪያ ደህናውን፣ ከዚያ የተሻለውን፣ ከዚያ ላቅ ያለውን እንዲሰለፍ ሲደረግ፣ በመጨረሻ ግን የሚሰለፈው ፈጣኑ ነው። የመጨረሻው ሯጭ ፈጣን ካልሆነ ድል አይመጣምና የመጨረሻው ፈጣን መሆን አለበት። እኛም ያለነው በመጨረሻው ዘመን ላይ ነው። የመጨረሻው ሯጮች ነንና ፈጣን መሆን ይገባናል። ልብ አድርጉ! ዱላውን (የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳንና ራእይን) አጥብቀን መያዝ ከዚያም በፍጥነት ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ አለብን።

እናስተውል

- በሕይወት ውስጥ ድሉ የጋራ ነው።
- ሕይወት ምክንያት አልባ ዝርው፣ ማሰሪያ የሌላት ብትን ነዶ፣ ግብ የሌላት ከንቱ ሩጫ አይደለችም። የሕይወት ዋጋዋ ራሱ እግዚአብሔር ነው።
- በሕይወት ላይ ከተላንት የምንቀበለው ለነገ የምናስተላልፈው ነገር አለ።
- እግዚአብሔር የሚጨነቅልን የኑሮ ዘዴ እንዲገባን ሳይሆን የመኖር ዓላማ እንዲገባን ነው።
- ዋናው ረጅም ዘመን ማገልገል ሳይሆን የተቀበልነውን የእግዚአብሔር አደራ በትክክል መግለጥና ለሌሎች ማስተላለፍ ነው።

- ከራሱ ነጻ ያልወጣ ሌላውን ነጻ ማውጣት አይችልም። ትልቅ ባርነት የፍላጎት አስረኛ፣ የራስ ወዳድነትና የትዕቢት ምርኮኛ መሆን ነው።
- ራእይ የሌለበት ድል እንቅልፍ ይነሣል፣ እፎይ አያሰኝም።
- ባለጠግነትም ሆነ ድህነት ሁኔታ ነው፤ ራእይ ግን እውነታ ነው።
- በሕይወትም ላይ የአንድ ሰው ስህተት ለብዙዎች ጉዳት ምክንያት ይሆናል።
- ትልቁ የሕይወት ክፍተት ያለው የእኔ ስህተት ለዓለም ምን ጉዳት ያመጣል? ብለን በማሰብ ላይ ነው።

ማጠቃለያ

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከምናገኛቸው ቅዱሳንና ባለ ራእይ ወጣቶች አንዱ ዮሴፍ ነው። ወጣቱ ዮሴፍ በወንድሞቹ የተገፋ እግዚአብሔር ግን በባዕድ ምድር ላይ ተቀብሎ ያከበረው ሰው ነበር። ዮሴፍ ወንድሞቹ ቢሸጡትም የማያውቀው ንጉሥ ዙፋን የለቀቀለት፣ አገሩ ማቅ ሆኖበት የባዕድ ምድር የተደላደለለት ሰው ነበር። ወንድሞቹ ገና በጠዋቱ የጠሉት ሕልሙን ስለ ነገራቸውና ከእኛ በላይ ይሆናል ብለው ስለሰጉ ነው (ዘፍ. 37)። ዮሴፍ እንደ ዋዛ የነገራቸውን ሕልም እነርሱ እንደ ዋዛ አልሰሙትም። ሕልሙ እውን እንደሚሆን አመኑ።

ስለዚህ ይህንን ሕልመኛ በመሸጥ ሕልሙን ለማደናቀፍና የጎሊና ዕረፍትን ለማግኘት ለግብፅ ነጋዴዎች በገንዘብ ለወጡት። እነርሱ ሕልሙን ያዳፈኑ ሲመስላቸው በተቃራኒው ግን ወደ ሕልሙ ፍቺና ፍጻሜ አቀረቡት። እግዚአብሔር ያለው አይቀርምና ወንድሞቹ ለዮሴፍ ሰገዱለት (ዘፍ. 43÷26)። ዮሴፍም ሕልሙንና ፍችውን አስተዋለ። የተሸጠው ዮሴፍ ያለ አገሩ ወንድሞቹን ተቀበለ። ከረሀብ ዘመንም እንዲተርፉ ምክንያት ሆነላቸው። ሞት የፈረዱበት ሕይወታቸውን የሚታደግ ሆነ። ዮሴፍም የምድር ዘመኑን ፈጽሞ ሲጓዝ ጥቂት ሲቀረው፦ *«እኔ እሞታለሁ፤ እግዚአብሔርም መጐብኘትን ይጐበኛችኋል፥ ከዚህችም ምድር ያወጣችኋል፤ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም ወደ ማለላቸው ምድር ያደርሳችኋል። ዮሴፍም የእስራኤልን ልጆች፦ እግዚአብሔር ሲያስባችሁ አጥንቴን ከዚህ አንሥታችሁ ከእናንተ ጋር ውሰዱ ብሎ አማላቸው»* (ዘፍ. 50÷24-25)።

እነዚህ የእስራኤል ልጆች ወደ ግብፅ የመጡት ዮሴፍን ብለው ሳይሆን ረሀብ ገፍቷቸው ነው። በዚያ ቀን ታላቁን ባለ ራእይ ዮሴፍን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ አገኙት። የሸጡት ወንድማቸው በእግዚአብሔር ጥበብ ታዳጊያቸው ሆነ። የገፉት ሰው ሲቀበል፣ የገደሉት ሰው ሲያኖር ለገፊው የድንጋይ ሽክም፣ ለተገፋው ግን እጅን በአፍ ላይ የሚያስጭን ግርምት አለው። በግብፅ ምድር እንጀራ ለማግኘት የተቀመጠው ያ ወገን አንድ ቀን ባለ አገርና ባለ በረከት እንደሚሆን ዮሴፍ ራእዩን ተናገረ፦ *«እኔ እሞታለሁ፤ እግዚአብሔርም መጐብኘትን ይጐበኛችኋል፥ ከዚህችም ምድር ያወጣችኋል፤ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም ወደ ማለላቸው ምድር ያደርሳችኋል። ዮሴፍም የእስራኤልን ልጆች፦ እግዚአብሔር ሲያስባችሁ አጥንቴን ከዚህ አንሥታችሁ ከእናንተ ጋር ውሰዱ ብሎ አማላቸው»* (ዘፍ. 50÷24-25)። ዮሴፍ ሕይወቱ ነገን በብሩህ በሚያይ ራእይ የተሞላ ነበር።

ራእይ አሁን ከምናየው ነገር ባሻገር ያለውን ማየት ነው። ከባርነት ጀርባ ያለውን ነጻነት፣ ከድህነት ጀርባ ያለውን እንጀራ መመልከት ነው። እኛስ በትውልዳችን ላይ የምናየው ምንድነው? እግዚአብሔር የሚያወርሰን ያየነውን ነውና። የሚታየንን ብሩህ ነገር እናውጀው። ለዋዘኞች የእብደት ቃል ቢመስልም የነገ እውነት ነውና በእምነት እንዝራው። ፍሬው ለከርሞ ይደርሳል። ዮሴፍ ራእዩ እንደ ተጨበጠ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፦ *«የእስራኤልም ልጆች ከግብፅ ምድር ተሰልፈው ወጡ። ዮሴፍም፦ እግዚአብሔር ሳይጐበኛችሁ አይቀርም፥ አጥንቶቼንም ከዚህ ከእናንተ ጋር ታወጣላችሁ ብሎ የእስራኤልን ልጆች አምሎአቸው ነበርና ሙሴ የእርሱን አጥንቶች ከእርሱ ጋር ወሰደ»* (ዘፀ. 13÷18-19) ይለናል። የራእይ ቃሎች ነፋስ ወስዷቸው የሚቀሩ አይደሉም። አንድ ቀን ይፈጸማሉ።

ወደ ራእይ ያልገባን ሰዎች ወደ ራእያችን ለመግባት፦

- በዓላማ እንደ ተፈጠርን እንመን።
- ራእዬ ይህ ነው ብለን ራእያችንን ለይተን እናውጣ።
- ራእያችንን ዳር ለማድረስ ቃል ኪዳን እንፈጽም።
- ለራእያችን አሁን ባለን ነገር እንንቀሳቀስ።
- እግዚአብሔርን ብቻ ተስፋ አድርገን እንኑር።
- ጊዜያችንን እንስጥ።
- ተቃውሞን በጽናት እናስተናግድ።
- ለተተኪዎች ስፍራ ለመልቀቅ ሁልጊዜ ዝግጅት እናድርግ።

በራእይ ጎዳና ላይ ያለን ሰዎችም ራእያችንን የምንገመግምበት የጊዜ መለኪያ፣ ራእያችንን የምንተገብርበት የእቅድ ገበታ ያስፈልገናል። ራእያችንን በደስታና በተስፋ ጀምረን ለይሉኝታ ብቻ ወደፊት እየገሰገስን ሊሆን ይችላል። የይሉኝታ ጉዞ አድካሚ ነውና የቀደመውን ተስፋችንን በማደስ እንደገና በኃይል እንነሣ!

አም ራእይ ያለው ትውልድ ማን እንደ ፈጠረው በማወቅ ለምን እንደሚኖር የተገነዘበ ወዴትም እንደሚሄድ የለየ ነው። ማን እንደ ፈጠረው የማያውቅ ለምን እንደሚኖር ምክንያት እያጣ ወዴትም እንደሚሄድ ግራ እየተጋባ ይጨነቃል። ራእይ ያለው ትውልድ መሠረቱ እግዚአብሔርን ማወቅና ማምለክ ነው።

ጸሎት

አቤቱ አምላኬ ሆይ እኔን በራእይ ለማክበር ማንም አልጠቆመህም፣ ራስህ ጠርተኸኛልና አመሰግንሃለሁ። የተመኘህልኝ ተግባር የሌለበትን ከበሬታ ሳይሆን የራእይን ክብር ነውና ከባዶ ክብር እንድድን ስለረዳኸኝ አመሰግንሃለሁ። ዛሬ ብዬ የምጠራትን ቀን የሌላ ሰው እንደሆነች እያሰብኩ የእኔ የምላትን ቀን እጠብቃለሁና እባክህ ቀኔ ሳያልቅ ለተፈጠርኩበት ዓላማ አኑረኝ። ምቹ ልብ እንጂ ምቹ ጊዜ ሥራ አይሠራምና ለራእይ የሚቃጠል መንፈስን ስጠኝ። ሕይወቴ ያልታሠረ ነዶ ሆኖ ፍሬው እየባከነብኝ፣ ሩጫዬ በዝቶ ደስታው እያነሰብኝ ተቸግሬአለሁና ጌታዬ ሆይ ራእይን ስጠኝ። ትልቅ ሥራ በትልቅ ነገር የሚሠራ እየመሰለኝ ትልቅ ነገር ስጠብቅ ዓመታት አልፈዋል። ጌታዬ ሆይ አንተ በበትር ባሕርን የምትከፍል፣ እጅ በምታህል ደመና ምድርን የምታረሰርስ፣ በአንድ ሰው አእላፋትን የምትጠቅም መሆንህን አሳውቀኝ። ለመጀመር አስብና ቀና የሚለውን በብረት በትራቸው ለመምታት የሚጠባበቁትን የመቃብር ጠባቂዎች እፈራለሁና እባክህ የእምነትን ድፍረት ስጠኝ። ሁልጊዜ አልበረታምና ለሌሎች ቦታ መልቀቅን አስተምረኝ። ጌታዬ ሆይ ይቻልሃልና እንዳልደከመ አድርገህ አበርታኝ፣ እንዳላዘነ አድርገህ አጽናናኝ፣ እንዳልታመመ አድርገህ ፈውሰኝ። ሰጥተህ ከማያልቅብህ፣ ሁሉ ከሚገኝብህ ካንተ ለምኜ አሳጣሁምና ለዘላለሙ አሜን!!